**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 84/2016**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

**ገፅ-----------------------------**

**አዋጅ ቁጥር 84/2016**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

የከተማው አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት እና በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 (እንደተሻሻለ) የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በእኩልነት፣ በግልጽነትና በፍትሃዊነት መርህ መሠረት ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና መወሰን በማስፈለጉ፤

በሀገራችን ብሎም በከተማችን እየተካሄደ ያለውን ለውጥ ውጤታማ፣ ዘላቂና ተቋማዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ) መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 84/2016 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "**ቻርተር**" ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 (እንደተሻሻለ) ነው፤
2. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

3. "**የከተማ አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
4. "**ከንቲባ**" ማለት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ (3) የተመለከተውና በቻርተር አዋጁ አንቀፅ 21 የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ያሉት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፤
5. "**ካቢኔ**" ማለት በከንቲባው አቅራቢነት በከተማው ምክር ቤት የሚሾሙ አባላት ያሉት አስፈጻሚ አካል ነው፤
6. "**የከተማ ሥራ አስኪያጅ**" ማለት በቻርተሩ አንቀፅ ፳፬ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ያሉት ሥራ አስኪያጅ ነው፤
7. "**ክፍለ ከተማ**" ማለት በቻርተሩ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ (5) የተመለከተው የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤
8. "**የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ የክፍለ ከተማ ካቢኔ እና የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ** "ማለት እንደቅደም ተከተላቸው በቻርተሩ አንቀጽ 34 ፣ 36 እና 37 የተመለከቱት አካላት ናቸው፤
9. "**ወረዳ**" ማለት የክፍለ ከተማ አካል የሆነ የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤
10. "**የወረዳ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ የወረዳ ካቢኔ፣ የወረዳ ሥራ አስኪያጅ**" ማለት በቻርተሩ አንቀፅ 38 ንዑስ አንቀፅ (2) የተመለከቱት አካላት ናቸው፤
11. "**የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ ካቢኔ**" ማለት በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ደረጃ በዋና ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ምክር ቤት የሚሾሙ አባላት ያሉት የከተማ አስተዳደሩን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ህጎችና እቅዶችን የሚያስፈጽም በቻርተሩ የተመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ነው፤
12. "**ቢሮ**" ማለት የመንግሥት የፖለቲካ አቅጣጫ የሚሰጥበት፣ ህግና ስታንዳርድ የሚወጣበት ሥራ የሚሰራ፣ አዳዲስ አሰራሮች፣ ሀሳቦች እና ፖሊሲዎች የሚያስተዋውቅ፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚከታተል፤ የሚቆጣጠር፤ የሚተገብር፤ አጠቃላይ የዘርፍ ሥራዎች የሚሰራ ተቋም ነው፤
13. "**ኮሚሽን**" ማለት አንድን የተወሰነ ተግባር ወይም ግዴታ ወይም የተሰጠውን ሥልጣን ለማከናወን ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው፤
14. "**ባለሥልጣን**" ማለት በመንግሥት እና በግል ተቋማት ለሚሰጡ አገልግሎቶች ፈቃድ የመስጠት፣ የመሰረዝ፣ የመቆጣጠር፣ ትዕዛዝ የመስጠት፣ ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድ ወይም እንዲወሰድ የማድረግ ሥልጣን ያለው ተቋም ነው፤

15. **"ኤጀንሲ"** ማለት በመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት የተወሰነ አገልግሎት የመስጠት፤ የተወሰነ የተቆጣጣሪነትና የልማት ሥራዎች የሚሰራ ተቋም ነው፤
16. **"ኮርፖሬሽን" ማለት** የመንግስት የልማትና ዕድገት ሥራ ለማፋጠን፣ ፖሊሲዎች ለመተግበር፣ የህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ አትራፊ ያልሆነ ተቋም ነው፤
17. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱ ቃላት ወይም ሐረጎች እንደአስፈላጊነታቸው ካቢኔው በሚያወጣቸው የተቋማት የአሰራርና የአደረጃጀት ደንቦች ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡

3. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ አስፈፃሚ አካላት</u>

### <u>ዘርፍ አንድ</u>

### <u>ስለአደረጃጀት</u>

4. <u>አደረጃጀት</u>

በቻርተሩ የተደነገገው አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማውን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕጎች የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት፡-

1. ከንቲባ፤
2. ምክትል ከንቲባ፤
3. ካቢኔ፤
4. የከተማ ሥራ አስኪያጅ፤
5. ሌሎች አስፈጻሚ አካላት፤
6. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤
7. የክፍለ ከተማ ካቢኔ፤
8. የወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤
9. የወረዳ ካቢኔ፤

ናቸው ፡፡

## ዘርፍ ሁለት

## ስለከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ ካቢኔ፣ የከተማ ሥራ አስኪያጅ

5. የከንቲባ ሥልጣንና ተግባር

በቻርተሩ አንቀጽ 21 እንደተደነገገው ከንቲባው፡-

1. ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለእርሱ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ይመራል፤ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
2. በከተማው ምክር ቤት የሚወሰኑትን ውሳኔዎች፣ የሚወጡትን ሕጎች፣ የሚጸድቁትን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያስፈጽማል፤
3. ለሥራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣኑ በከፊል ለምክትል ከንቲባ፣ በቀጥታ ለራሱ ተጠሪ ለሆነ ኃላፊ ወይም አስፈፃሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
4. በአስፈፃሚ አካላት ወይም በኃላፊዎቻቸው የተሰጡ ውሳኔዎች፣ የወጡ መመሪያዎችና የተሰጡ ትእዛዞች ህግን የሚፃረሩ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ይሽራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲስተካከሉ መመሪያ ይሰጣል፤
5. የካቢኔ አባላትን መርጦ ሹመታቸውን በምክር ቤቱ ያጸድቃል፤ ካቢኔውን ይመራል፤
6. የከተማውን የፀጥታ ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤
7. የከተማውን ሕግና ሥርዓት ያስከብራል፤
8. ሹመታቸው በከተማው ምክር ቤት መጽደቅ ያለበትን ሳይጨምር የከተማውን አስፈጻሚ አካላት የበላይ ኃላፊዎች ይሾማል፤ ለከተማው የልማት ድርጅቶችና ሌሎች አካላት የቦርድ ሰብሳቢዎችና አባላትን ይሰይማል፤
9. ሌሎች በቻርተሩ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

6. የምክትል ከንቲባ ሥልጣንና ተግባር

በቻርተሩ አንቀፅ 22 እንደተደነገገው ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ፡-

1. ከንቲባው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፤
2. በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

7. የካቢኔ ሥልጣንና ተግባር

በቻርተሩ አንቀጽ 23 እንደተደነገገው፡-

1. የካቢኔው ተጠሪነት ለከንቲባው እና በጋራ ለሚወስነው ውሳኔ ለከተማው ምክር ቤት ይሆናል፤
2. በፌደራል መንግስትና በከተማው ምክር ቤት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ውሳኔዎችና ደረጃዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

3. ምክር ቤቱ ያወጣቸው ፖሊሲዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
4. ከተማ አቀፍ ፖሊሲና የአዋጅና የደንብ ረቂቅ ያመነጫል፤
5. በከተማው ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ላይ ይመክራል፤
6. የከተማውን አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ይወስናል፤
7. በምክር ቤቱ በሚወጡ አዋጆች ላይ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፤
8. በከንቲባውና በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 8. ስለካቢኔ አባላት

የካቢኔው አባላት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ከንቲባ፣
2. ምክትል ከንቲባ፣
3. የከተማ ሥራ አስኪያጅ፤
4. የሥራና ክህሎት ቢሮ፤
5. የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፤
6. የፋይናንስ ቢሮ፤
7. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ፤
8. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፤
9. የሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ፤
10. የባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፤
11. የፍትህ ቢሮ፤
12. የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፤
13. የትራንስፖርት ቢሮ፤
14. የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ፤
15. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ
16. የጤና ቢሮ፤
17. የንግድ ቢሮ፤
18. የትምህርት ቢሮ፤
19. የሴቶች፣ ሕጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤
20. የገቢዎች ቢሮ፤
21. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፤
22. የኮሙኒኬሽን ቢሮ፤

23. የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፤
24. የፕላንና ልማት ቢሮ፤
25. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤
26. የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን፤
27. የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን፤
28. የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤
29. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን፤
30. እንደ አስፈላጊነቱ በከንቲባ የሚሰየሙ ሌሎች የካቢኔ አባላት፤ይኖሩታል፡፡

## 9. ስለካቢኔ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

የካቢኔው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፡፡

## 10. የከተማ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

በቻርተሩ አንቀጽ 24 እንደተደነገገው የከተማው ሥራ አስኪያጅ ፡-

1. ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ አስፈጻሚ አካላትን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
2. ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት እንዲቋቋሙ ወይም ሌሎች የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለከንቲባው ሀሳብ ያቀርባል፤
3. ከተማ አቀፍ እና ክፍለ ከተማ ዘለል የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ ዕቅድና በጀት ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናቀር ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. ስሉጥ፣ ግልጽና ፍትሃዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መሰጠቱትን ያረጋግጣል፤
6. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት የፖሊሲ ሀሳብ እና የህግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባው ያቀርባል፤
7. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤
8. ለሥራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣኑ በከፊል ለምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ ለራሱ ተጠሪ ለሆነ ኃላፊ ወይም አስፈፃሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
9. በቻርተሩ የተሰጡትን ሌሎች ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም በከንቲባው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለአስፈፃሚ አካላት መቋቋምና ተጠሪነት

### 11. የአስፈፃሚ አካላት መቋቋም

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁመዋል፤

1. የከንቲባ ጽህፈት ቤት፤
2. የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፤
3. የሥራና ክህሎት ቢሮ፤
4. የፋይናንስ ቢሮ፤
5. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ፤
6. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፤
7. የሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ፤
8. የባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፤
9. የፍትህ ቢሮ፤
10. የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፤
11. የትራንስፖርት ቢሮ፤
12. የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ፤
13. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ
14. የጤና ቢሮ፤
15. የንግድ ቢሮ፤
16. የትምህርት ቢሮ፤
17. የሴቶች፣ ሕጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤
18. የገቢዎች ቢሮ፤
19. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፤
20. የኮሙኒኬሽን ቢሮ
21. የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፤
22. የፕላንና ልማት ቢሮ፤
23. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤
24. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን፤
25. የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፤
26. የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን
27. የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፤

28. የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን፤
29. የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፤
30. የህብረት ሥራ ኮሚሽን፤
31. የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን፤
32. የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን፤
33. የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤
34. የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን፤
35. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፤
36. የመንገዶች ባለስልጣን፤
37. የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤
38. የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን፤
39. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን፤
40. የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤
41. የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፤
42. የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ፤
43. የምገባ ኤጀንሲ፤
44. የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ፤
45. የመንግስት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት፤
46. የማህበራዊ ትረስት ፈንድ፤
47. ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል፤
48. የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ፤

12. <u>የአስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት</u>

1. የካቢኔ አባላት እና የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለከንቲባ ይሆናል፡-
   ሀ) የከንቲባ ጽህፈት ቤት፤
   ለ) የህብረት ሥራ ኮሚሽን፤
   ሐ) የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን፤
   መ) የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን፤
   ሠ) የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፤
   ረ) የመንገዶች ባለስልጣን፤
   ሰ) የውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፤
   ሸ) የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፤

በ) የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤

ተ) የምገባ ኤጀንሲ፤

ኘ) የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ፤

ቸ) የማህበራዊ ትረስት ፈንድ፤

ኀ) የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ፤

2. ለከተማ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት፡-

ሀ) የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፤

ለ) የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፤

ሐ) የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ፤

3. የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ተጠሪነት ለሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፤

4. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ተጠሪነት ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፤

5. የመንግስት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጠሪነት ለፋይናንስ ቢሮ ይሆናል፤

6. ለትራንስፖርት ቢሮ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት፡-

ሀ) የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን፣

ለ) የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣

ሐ) የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት፤

መ) አዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገግልግሎት ድድርጅት፤

7. የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ተጠሪነት ለከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፡፡

13. <u>**የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ከክፍለ ከተማ ጋር ያላቸው ተዋረዳዊ ግንኙነት፡-**</u>

1. የእያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል ኃላፊ፣ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊ ወይም ኃላፊዎች፣ ሌሎች አግባብ ያላቸው የሥራ ክፍሎችና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሰራተኞች የሚኖረው ሆኖ ይደራጃል፤

2. አንድ አስፈፃሚ አካል ከሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ደጋፊ ሥራ ሂደት አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ ካቢኔው በሚያጸድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በከንቲባው በሚወጣ መመርያ ይወሰናል፤

3. የክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ወይም የሌላ አስፈጻሚ የሥራ ክፍል፡-

ሀ) ከከተማው ቢሮ ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር በእቅድ ዝግጅት፣ ክዋኔ ክትትልና ግምገማ እና በሌሎች ቴክኒካዊና ሙያዊ ጉዳዮች ላይ ቀጥተኛና መደበኛ ግንኙነት በማድረግ በቅንጅትና በትስስር ይሰራል፣

ለ) እንደየአግባቡ የሰራተኛ የውስጥ ዝውውር፣ የደረጃ ዕድገት፣ አመዳደብ  በከተማው በሥራው መስክ ከተደራጀው አስፈጻሚ አካል ጋር ቀጥተኛና መደበኛ ግንኙነት በማድረግ ይሰራል፡፡

14. <u>**የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት**</u>

1. እያንዳንዱ የካቢኔ አባል፦
   ሀ) ተጠሪነቱ ለከንቲባው ይሆናል፣
   ለ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣
   ሐ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣
   መ) ኃላፊ የሆነበትን አስፈፃሚ አካል ይመራል፤ ይወክላል፤
   ሠ) የሚመራውን ተቋም ስትራቴጂክ የፖሊሲ ሀሳቦች ያመነጫል፤ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ተቀባይነት ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፤
   ረ) በከንቲባው እና በካቢኔው የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና የሚሰጡ ትዕዛዞችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
   ሰ) የሚመራውን ተቋም የሥራ ዕቅድ  እና የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለከንቲባ ያቀርባል፤
2. የእያንዳንዱ ሌላ አስፈፃሚ አካል ኃላፊ፦
   ሀ) የሚመራውን አስፈጻሚ አካል ስለሚመለከቱ ሥራዎች፣ፕሮግራሞችና ህጎች አፈጻጸም ተጠሪነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ለተመለከተው አስፈጻሚ አካል ወይም የስልጣን አካል ይሆናል፣
   ለ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈጻሚ አካል የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣
   ሐ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣
   መ) ኃላፊ የሆነበትን አስፈጻሚ አካል ይመራል፤ ይወክላል፤
3. ከከንቲባው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

15. **<u>በቢሮ ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል እና በተጠሪ ተቋም መካከል ስለሚኖር ግንኙነት</u>**

1. ለቢሮ ወይም ለሌላ አስፈፃሚ አካል ተጠሪ የሆነ ተቋም በሕግ የተቋቋመ እና ራሱን የቻለ ተቋም በመሆኑ ቢሮው ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል የተጠሪ ተቋሙን ሥራዎች ከማስተባበር፣ ከመደገፍና ስትራቴጂክ አመራር በመስጠት፣ ውጪ በእለት እለት እንቅስቃሴው ላይ ጣልቃ አይገባም፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ  አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የቢሮው ወይም የሌላው አስፈፃሚ አካል እቅድና ሪፖርት የተጠሪ ተቋሙንም የያዘ መሆን ይኖርበታል፤
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም «ማስተባበር፣ መደገፍና ስትራቴጂክ አመራር መስጠት ማለት»፡-

   ሀ) የተጠሪ ተቋማትን እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት  አጠቃላይ አፈፃፀም መከታተልን፣

   ለ) አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የልማት ሥራ ፕሮግራሞቻቸውን፣ ፕሮጀክቶቻቸውንና በጀቶቻቸውን በተመለከተ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

   ሐ) በሕግ የተሰጧቸውን ተግባርና ኃላፊነቶችን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ መደገፍንና ማብቃትን፤

   ይጨምራል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር</u>

16. **<u>የወል ሥልጣንና ተግባር</u>**

እያንዳንዱ አስፈጻሚ አካል፡-

1. እቅድን በሚመለከት፡-

   ሀ) በሚደርሰው መመሪያ መሰረት ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር እቅዶችን ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

   ለ) የሚመለከቱትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሥራ ላይ ያውላል፣

   ሐ) ለዕቅዱ አተገባበር አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት በወቅቱ ይፈፀማል፤ ያስፈጽማል፤

   መ) የስታትስቲክስ መረጃዎች ያሰባስባል፤ ያቀነባብራል፤

2. በሥራው መስክ፤-

   ሀ) ፖሊሲ ወይም የህግ ረቂቅ ያመነጫል፤ መስርያ ቤቱን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመርያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

   ለ) በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

   ሐ) ጥናት ያጠናል፤ ተገቢውን ስልጠና ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

   መ) በህግ መሰረት ውሎችንና ስምምነቶችን ያደርጋል፣

ሠ) በህግ መሰረት መመርያዎችን ያወጣል፤ በሥራ ላይ ያውላል፣

ረ) ከሌሎች ተቋማት ጋር ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ትስስርና ትብብር ያደርጋል፤

3. ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጡን በቀጣይነት ያዘምናል፤ ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ውጤታማነታቸን ያረጋግጣል፤
4. ስለሥራው ክንዋኔ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤
5. የመስሪያ ቤቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት አግባብ ላለው አካል አቅርቦ ያፀድቃል፤
6. የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
7. የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በደማቸው ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለባቸው ሰዎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል እድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
8. አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያዘዋውራል፤ ይመድባል፤ ያሰናብታል፤ ያስተዳድራል፤
9. ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈፃሚ አካላት አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ አደረጃጀቶቻቸውን፣ የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን እና በጀቶቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
10. ለሚሰጠው አገልግሎት በህግ ሲፈቀድለት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤
11. እንደየሥራ ባህሪያቸው የህብረተሰብ ተሳትፎን በማጎልበት ተጠቃሚ ያደርጋል፤ ከአስተዳደሩ አካላትና ከሌሎች አስፈፃሚ አካላት ጋር አግባብነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ በቅንጅትና በትብብር ሥራዎችን ማከናወን ይኖርበታል፤
12. የዘላቂ ልማት፣ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ሥራዎችን ለማበረታታት ሲፈቀድ ፈንድ ሊያቋቁም ይችላል፤
13. በከንቲባው ወይም አግባብ ባለው ተጠሪ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል፤
14. በዚህ አዋጅ የተመለከቱትንና ሌሎች በህግ የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤
15. ለሥራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ አስፈፃሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 17. <u>የከንቲባ ጽህፈት ቤት</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለካቢኔ ስብሰባ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን ለይቶ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሚመለከታቸዉ አካላት ያሳዉቃል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤ በአፈፃፀም በሚከሰቱ ክፍተቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
2. የካቢኔ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎችና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶች በጥራዝ እና በሶፍት ኮፒ በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
3. ስትራቴጂያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከንቲባውን ያማክራል፤ ለከንቲባ ለሚቀርቡ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እና ቅሬታዎች ምላሽ ይሰጣል፤ በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈታ ይመራል፣ የከንቲባ ውሳኔ ለሚሹ ጉዳዮች የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣
4. የከንቲባውን የዕለት ተዕለት መርሀ ግብሮችን ይከታተላል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለከንቲባ መቅረብ ያለባቸው ጉዳዮች ቀጠሮ እንዲያዝላቸው ያደርጋል፤
5. ከንቲባው ለሚካፈልባቸው ብሔራዊና አለም አቀፍ ስብሰባዎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፤ ጽሁፎች እና መግለጫዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ተሟልተው መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤
6. ከአዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ውጪ በተሰጠ የአገልግሎት አሰጣጥ ምክንያት በከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ ተቋማት ፣ በኃላፊ እና በሠራተኛ ላይ የሚቀርብለትን ጥቆማ፣ አቤቱታ ወይም ቅሬታ ይቀበላል፤ ያጣራል፤ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሣኔውን ለአቤቱታ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ያሣውቃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
7. በመልካም አስተዳደር መርሆች መሰረት ተግባራት መፈፀማቸውን ይከታተላል፤ የከተማ መልካም አስተዳደር አመላካቾችን ተጠቅሞ አገልግሎት አሰጣጥን ያጠናል ወይም እንዲጠና ያደርጋል፤ የጥናቱን ውጤት ያሰራጫል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
8. ለከተማው ምክር ቤት እና ለፌደራል መንግሥት ሊቀርቡ የሚገባቸውን ዕቅዶችና ሪፖርቶች ከከተማ ተቋማት እና ከክፍለ ከተሞች ወቅታቸውን ጠብቀው መቅረባቸውን ይከታተላል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤
9. በጽህፈት ቤቱና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የቅንጅት ሥራዎች ያስተባብራል፤ የመግባቢያና የፕሮቶኮል ስምምነት ሰነዶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ አፈፃጸማቸውን ይከታተላል፤

10. ከንቲባው በሚሰጠው ውክልና ወይም የሥራ አቅጣጫ መሠረት፡-

ሀ) ከፌደራል መንግስት ጋር ተዋረዳዊ ትስስር ይፈጥራል፤ በሴክተር መስሪያ ቤቶች መካከል የሥራ ትስስር እና ቅንጅት መኖሩን ይከታተላል፤ ክፍተት ሲፈጠር ገምግሞ ያቀናጃል፤ ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ለ) የከተማ አስተዳደሩን የሥራ እንቅስቃሴና በየደረጃው የሚከናወኑ ጉዳዮችን መረጃ ያሰራጫል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ መረጃው ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል፤

ሐ) ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ከተሞች፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነቶችን ይፈጥራል፣ ሂደቱን ያስተባብራል፤ ከክልሎችና ከክልል ዋና ዋና ከተሞች ጋር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ በትብብር ይሰራል፤

መ) ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸውን ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይከታተላል፤ ሪፖርት ለከንቲባ ያቀርባል፤

11. ለከንቲባና የከንቲባ የክብር እንግዶች እንዲሁም በከንቲባዉ ለተፈቀደላቸዉ እና ለሚፈቀድላቸው የከተማ አስተዳደሩ ባለሥልጣናት የፕሮቶኮል አገልግሎት ይሰጣል፤ መሰጠቱን ይከታተላል፤ የከንቲባን የእንግዳ መስተንግዶ እና የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጉዞ ዝግጅቶች አፈፃፀምን ይከታተላል፤

12. በከንቲባው የሚሾሙ ወይም የሚሸለሙ ዕጩዎችን የሹመትና የሽልማት ደብዳቤ ያዘጋጃል፤ የሹመት ወይም የሽልማት ሂደቱን ተከታትሎ ያስፈጽማል፤

13. የሠላማዊ ሠልፍ ጥያቄዎችን ተቀብሎ ተገቢነታቸዉን እና ወቅታዊነታቸውን በማጤን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲስተናገዱ ያደርጋል፤

14. ተጠሪነታቸው ለከንቲባ የሆኑ አስፈጻሚ አካላትን ከከንቲባው በሚሰጥ ውክልና መሰረት ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ አፈፃፀማቸዉን በሚመለከት ለከንቲባው ሪፖርት ያቀርባል፤

15. የህዝብ በዓልን፤ ክብረ በዓልን ወይም ኮንፎንሽን አከባበርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፤ ተከታትሎ ያስፈጽማል፤

16. የዕቅድ ክንውን ግምገማዎች በወቅቱ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ በሱፐርቪዥንና ክትትል የተደገፈ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ አዘጋጅቶ ለከንቲባ ያቀርባል፤

17. የከተማ አስተዳደሩን ብራንድ ያስጠናል፤ የጥናቱን ውጤት ለከንቲባ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ይፈጽማል፤ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

18. ከሕዝብ የሚቀርብለትን ጥቆማ ይቀበላል፤ ያጣራል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
19. በከተማው ሀብት ወይም ደህንነት ዙሪያ የሚያገኘውን መረጃ መነሻ በማድረግ ወይም በራሱ አነሳሽነት ምርመራና ትንተና ያደርጋል፤ የግኝቱንም ሪፖርት ለከንቲባ ያቀርባል፤
20. በከንቲባ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 18. <u>የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ተቋማዊ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ፕሮጀክቶችን፣ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ መመሪያዎችንና እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. በከተማው ውስጥ ለሚገኙ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ለግል አምራች ኢንዱስትሪዎች ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ ተደራጅተው ሥራ ላይ ያሉ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከሥራና ክህሎት ቢሮ ተረክቦ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
3. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊ የሆነ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል እና የግብዓት አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማበረታታት በጥናት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ፣ የዕውቅና እና ሽልማት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከጥናትና ምርምር ተቋማት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
6. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመረጃና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤
7. የአምራች ኢንዱትሪዎችን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የአቅም ክፍተታቸውን በጥናት በመለየት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤ ተፈጻሚነቱንና ውጤታማነቱን ይከታተላል፤
8. አምራች ኢንዱስትሪዎች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ የመረጃ ማጥራት ሥራ ይሰራል፣ ብቁ ለሆኑት የእድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

9. አምራች ኢንዱስትሪዎች ለተወዳዳሪነታቸው እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ለይቶ ያጠናል፣ ይቀምራል፣ ያሸጋግራል፣ ያስተገብራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤
10. አምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ የሚያደርጉ የኢንኩቤሽን እና አክስለሬሽን የምርታማነት ማሻሻያ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የምርምርና የቴክኒክ አቅም ግንባታ ማዕከላት እንዲሆኑ ይሰራል፣ ያስተባብራል፤
11. የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ በውጭ ሀገር በሚካሄዱ ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
12. መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ እና የግል ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤
13. የአምራች ኢንዱስትሪዎች እርስ በእርስ በግብዓት አቅርቦት፣ በምርትና በቴክኖሎጂ ትስስር እንዲፈጥሩ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
14. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመረጃ፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ የድርድርና የኮሚሽኒንግ ድጋፍ ይሰጣል፤ ውጤቱንም ይገመግማል፤
15. የአምራች ኢንዱስትሪዎች የምርት ደረጃ እና የጥራት ሰርቲፊኬሽን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፣ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተባብራል፤
16. አምራች ኢንዱስትሪዎችን በዘርፍ ማህበራት እንዲደራጁ ያበረታታል፣ ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤
17. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃና የአረንጓዴ ልማት የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻቸል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤ ክፍተት ያለባቸውን አምራች ኢንዱስትሪዎች ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤
18. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የንግድ ልማት አገልግሎት እና በአመራረት ሂደት ላይ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል እንዲሁም ምርታማነትና የማምረት አቅም አጠቃቀማቸዉን ይለካል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤
19. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የተሰማሩበትን የሥራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የብድር፣ የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ፣ የመስሪያ ቦታና መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉላቸዉ ያመቻቻል፣ አገልግሎትን ስለማግኘታቸዉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ ተፈፃሚነቱን

ያረጋግጣል፣ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ ውሎ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

20. ተኪ ምርት የሚያመርቱና ኤክስፖርት የሚያደርጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ድርሻ እና ምርታማነት እንዲያድግ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

21. አዲስ የመስሪያ ቦታና ማስፋፊያ የሚሰጣቸው አምራች ኢንዱስትሪዎችን ይመለምላል፤ የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ያመቻቻል፤ የተለዩ አምራች ኢንዱስትሪዎች መሥሪያ ቦታ ማግኘታቸውን ክትትል ያርጋል፤ የመሥሪያ ቦታ ያገኙ አምራች ኢንዱስትዎች ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲጨምር ይደግፋል ይከታተላል፤

22. ደረጃቸውን የጠበቁ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ክላስተር ግንባታዎች ተገንብተው በሚጠናቀቁበት ጊዜ ከመሥሪያ ቦታ ውስጥም ሆነ ውጭ ያሉ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ፓርኩ እንዲገቡ ይመለምላል፤ የመሥሪያ ቦታ እንዲያገኙ ያመቻቻል፤ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ወይም ክላስተር የገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

23. በአምራች ኢንዱስትሪዎች የካይዘን ፍልስፍናን በማስተግበር አሰራራቸዉን አዘምነዉ ቀልጣፋና ዉጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ እና ምርትና ምርታማነትን እንዲያሳድጉ የሚያስችል የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፣ የካይዘን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተገብራል፤ ውጤታማነቱን ይለካል፡፡

19. <u>**የሥራና ክህሎት ቢሮ**</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኮሌጆችን፣ ማዕከላትንና ተቋማትን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ አመራሮችን በውድድር ይመድባል፤
2. የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ስትራቴጂ ተፈፃሚ ለማድረግ በሥልጠና ዘርፍ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው መንግታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤
3. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን፣ የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ምርምርና ሽግግር፣ የኢንኩቤሽን፣ የክህሎት፣ የብየዳ፣ ማዕከላትን ያደራጃል፤ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ እንዲያሟሉ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና የምርምር ማዕከላት እንዲሆኑ ይሰራል፤ ያስተባብራል፤
4. የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ጥራት፣ ተደራሽነት፣ አግባብነትና ፍትሃዊነት እንዲረጋገጥ ይሰራል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

5. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ትኩረት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በዚህ ረገድ የሚቀየሱ አገር አቀፍ ሥርዓቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
6. የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የውስጥ ገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ያስተገብራል፤ ክትትል ያደርጋል፤
7. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞችና አመራሮች ሙያዊ ብቃታቸውን የሚያሻሽሉበት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. የማሰልጠኛ ወርክሾፖች ከሥልጠናው ባሻገር የማምረቻ ማዕከላት እንዲሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትስስርና የትግበራ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤
9. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት አግባብ ባለው ሕግና አሰራር መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ከአገር ውጪ ከሚገኙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤
10. በመንግስትና በግል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ለሚሰማሩ ወይም በሥራ ላይ ያሉና ፕሮግራም ለሚያስፋፉ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤
11. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የግንዛቤ ማሰጨበጫ መድረኮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ ያስተባብራል፤ ሥልጠና ይሰጣል፣
12. በመደበኛና በአጫጭር ጊዜ ሥልጠና መርሐ ግብር ሥልጠና የሚሰጥበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ማቀብ፣ ማሸጋገር እና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤
14. አገር በቀል እውቀትና ክህሎት የሚበለፅግበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይተገብራል፤
15. የኢንኩቤሽን አገልግሎት ተደራሽ የሚሆንበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
16. የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት፣ ኢንተርፕራይዞች፣ ለኢንተርፕሩነሮች ቴክኖሎጂ የሚያለሙ አሰልጣኞች፣ ሰልጣኞች እና የግል የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ለማበረታታት የዕውቅና ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
17. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የሙያ ደረጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤ በከተማ አስተዳደሩ በፍላጎት ጥናት መሰረት አዲስ ሙያዎች የሙያ ደረጃ እንዲቀረፅላቸው ያደርጋል፤

18. የውጤት ተኮር ስልጠና ሥርዓት ከማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች ወይም ድርጅቶች ጋር ተሳስሮ የሚሰጥበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በየጊዜው እያጠና እንዲሻሻል ያደርጋል፤

19. የከተማ አስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት በሥራ አመራር ቦርድ እንዲመሩ እና አደረጃጀትና አስተዳደራቸውን እያጠና እንዲሻሻል ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ በውስጥ አሰራር በተጠያቂነት እንዲመሩ ያደርጋል፤

20. በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ነዋሪዎች አምራች ዜጋ ለማድረግ የሥራ ገበያውን መነሻ ያደረገ አዳዲስ የሥራ ዕድል አማራጮች ያቀርባል፣ ፕሮጀክት ይቀርጻል፣ የአዋጭነት ጥናቶችን ያጠናል፣ ይተገብራል፣ ያስተገብራል፤

21. የኢንተርፕራይዞች የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤ ምርታቸውንና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበት፣ የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበት አውደ ርዕዮች እና ባዛሮችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ በውጭ ሀገር በሚካሄዱ ዐውደ ርዕዮችና ባዛሮች እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

22. ለኢንተርፕራይዞች የመረጃ፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ የድርድርና የኮሚሽኒንግ ድጋፍ ይሰጣል፤ ውጤቱንም ይገመግማል፤ በዘርፍ ማህበራት እንዲደራጁ ያደርጋል፤ ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ለይቶ ይቀምራል፣ ያስፋፋል፤

23. ለኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ የንግድ ልማት አገልግሎት፣ የማምረት አቅም በመለካት ምርታማነታቸውን የሚያሳድግ ድጋፍ ይሰጣል፤ የፋይናንስ ድጋፍ ፣የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ፣ የመሰሪያ ቦታና መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉላቸዉ ያመቻቻል፤ ይከታተላል፤ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

24. ለአምራች ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እስከ ጥቃቅን መብቃት ድረስ ያለውን የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ይሰጣል፤ ብቁ ሆነው ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩትን ለኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ያስረክባል፤

25. ከአምራች ኢንተርፕራይዞች ውጪ ላሉ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እንዲሁም ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ የመረጃ ማጥራት ወይም ኦዲት ያደርጋል፤ ብቁ ለሆኑ የእድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

26. መሥራት እየቻሉ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ሥራ ሳይኖራቸው በከፋ ድህነት ላይ የሚኖሩ የከተማ ነዋሪዎችን መረጃ ይመዘግባል፤ ይለያል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ሲፈቀድለትም በአካባቢ ልማት ሥራዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

27. ከአካባቢ ልማት ሥራዎች የተጠቃሚነት ጊዜያቸው ሲያበቃ የማስመረቅ ሥራ ይሰራል፤ በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
28. የሥራ ገበያ ፍላጎት እንዲጠና ያደርጋል፤ መረጃ ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
29. በከተማ አስተዳደሩ ነዋሪ የሆኑ ሥራ ፈላጊዎችን ይመዘገባል፤ መረጃዉን ይተነትናል በሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂ፣ አሰራርና የድጋፍ ማዕቀፎች፣ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ወደ ሥራ ያስገባል፤ አፈፃፀሙን እየተከታተለ ድጋፍ ያደርጋል፤
30. ሥራ ፈላጊዎችን አግባብ ባለው ሌላ ህግ መሰረት ያደራጃል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ለኢንተርፕራይዞችና ሥራ ፈላጊዎች የመረጃና የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤
31. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤
32. ሥራና ሠራተኛ ለሚያገናኙ ኤጀንሲዎች የብቃት ማረጋገጫ በህግ መሰረት ይሰጣል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል ይሰርዛል፤
33. የከተማው ነዋሪ ስለውጭ አገር ሥራ ስምሪት እና ህገ ወጥ ዝውውር ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኝ የመገናኛ ብዙኃንንና ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ቀጣይነት ያለው ከተማ አቀፍ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራዎችን ያከናውናል፤
34. ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ስለተቀባይ አገር ሁኔታ፣ በሚሰማሩበት የሥራ መስክ ሊኖራቸው ስለሚገባ ክህሎት፣ስለመብታቸው፣ ኃላፊነታቸው እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች የቅድመ-ስምሪትና የቅድመ ጉዞ ግንዛቤ ማሰደጊያ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
35. የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ሊያሳድጉ የሚችሉ የሰራተኞች የሥራ ላይ ደህንነት፤ የአካባቢ ጥበቃና የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የሚያስጠብቁ ተግባራትን ያከናውናል፤
36. በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን ያደርጋል፤ የወል የሥራ ክርክሮች እና የኅብረት ስምምነት ድርድር ልዩነቶች በመግባባት እልባት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የህብረት ስምምነቶችንና ማሻሻያዎቻቸውን ይመዘግባል፤
37. የወል ሥራ ክርክሮችን በተቀላጠፈ ሁኔታ በመቀበል መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ እንዲሁም የተሰጡ ውሳኔዎችን ያስፈጽማል፤
38. በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፣ የሙያ ምክር አገልግሎት ስለሚስፋፋበት፣ ሥራና ሠራተኛ ስለሚገናኙበት ዘዴ ይቀይሳል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

39. በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ በተደነገገው መሰረት በከተማው ውስጥ የሚደራጁ የአሰሪና ሰራተኛ የሙያ ማህበራትን ይመዘግባል፤ የመደራጀትና የኅብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤ ሲፈርሱ ምዝገባውን ይሰርዛል፤

40. አሰሪዎች የሥራ ሁኔታን፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነትን እና የሥራ አካባቢን ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ ማዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

41. የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትን፣ የሥራ ሥምሪት አገልግሎትና የሥራ አፈጻጸም እያጠና ምክር የሚሰጠው የመንግሥት፣ የአሠሪዎች ማህበራትና የሠራተኛ ማህበራት ተወካዮችን ያካተተ ቋሚ የሆነ አማካሪ ቦርድ ሊያቋቁም ይችላል፤

42. በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ መሰረት የከተማው አስተዳደር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ እና አማካሪ ቦርድ አባሎችን ይሰይማል፤ ያሰናብታል፤ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ይከታተላል፤

43. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ሥራ" ማለት አግባብ ባለው ሕግ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት፣ የሙያ ደህንነት ጤንነትና የሥራ አካባቢ፣ የሠራተኛና የአሰሪዎች ማህበር፣ ማህበራዊ ምክክር ሥርዓት፣ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና መሠረታዊ የሥራ ላይ መብቶችና ግዴታዎችን አካትቶ የያዘ ነው::

44. ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወጣቶች ያላቸውን የእውቀት፣ የክህሎት ወይም የአመለካከት ችግር ለመቀረፍ ሥልጣና በመስጠት በቀጣሪ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ያመቻቻል፤ ልምድ ባደረጉባቸው ቀጣሪ ድርጅቶች ውስጥ በቅጥር ሥራ እንዲያኙ የማስተሳሰር ተግባር ያከናውናል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

20. **<u>የፋይናንስ ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመንግስት የግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ያስተባብራል፤ በበላይነት ይመራል፤ ይደግፋል፤
2. በከተማው አስተዳደር አካላት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የበጀት ጥያቄ እና የክፍለ ከተሞችን የበጀት ድልድል መርምሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በህግ መሰረት ያስተዳድራል፤
3. የፊሲካል ፖሊሲ ያጠናል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ ውጤቱንም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
4. ባልተማከለ የበጀት አስተዳደር ሥርዓት መሠረት የክፍለ ከተሞችን የበጀት ድልድል ቀመር አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለክፍለ ከተሞች የሚሰጠውን የበጀት ድጎማ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

5. በገቢዎች ቢሮ የሚሰበሰበውን፣ በብድርና በእርዳታ የሚገኝ ገቢ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎችን ያስተዳድራል፤ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
6. የግብር እና የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ የታሪፍ ማሻሻያ እንዲሁም አዳዲስ የገቢ ምንጭ ጥናት በማዘጋጀት እና/ወይም እንዲዘጋጅ በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
7. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች በከተማ አስተዳደሩ ስም ይበደራል፤
8. የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፍ ከዕርዳታ ሰጪ አገሮች ወይም ከተሞች እና ድርጅቶች ያፈላልጋል፤ ያስተባብራል፤ ውል ይፈርማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
9. የከተማውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
10. ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብና ገቢ ደረሰኞች፣ ቅጻቅፆች፣ መዛግብቶች ያሳትማል፤ እንዲታተም ያደርጋል፤
11. ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት በአግባቡ መፈጸሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤
12. ከከተማው አጠቃላይ ሃብት ጋር የተጣጣመ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶችን ተቀብሎ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያበለጽጋል፤ ያፀድቃል፤ ውል ይፈራረማል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
14. የከተማው አስተዳደር ዓመታዊ ሒሳብ አጠቃልሎ ይይዛል፤ በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ያስመረምራል፤ በግኝቱ ላይ ተመስርቶ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤
15. የከተማው የግዥና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤
16. የውስጥ ኦዲት በሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ በክፍለ ከተሞችና በወረዳዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
17. የውስጥ ኦዲት መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርቶችን ተቀብሎ ይገመግማል፤ የተገኙ ድክመቶች እንዲታረሙ ያደርጋል፤
18. የከተማው አስተዳደር አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፤ ይጠብቃል፡፡

21. <u>የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽንን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ይደግፋል፤
2. አገራዊ የቤቶች ልማትና አስተዳደርን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ዝርዝር የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም ስታንዳርድ በከተማዋ ተፈጻሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ የማሻሻያ ግብዓቶች ያሰባስባል፤ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፤
3. በመንግስት አስተባባሪነት፣ በመንግስትና በግል አጋርነት፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት፣ የግል ቤት አልሚዎች እና ሪል ስቴቶችን እና በሌሎች አማራጭ የቤት ልማት ፕሮግራሞችን ለማከናወን እና አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችል ጥናቶችን ያጠናል፤ ያስጠናል፤ ስልትና ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
4. የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ይይዛል፤ የመኖሪያ ቤት ዓይነቶችን መደብና ደረጃ ያወጣል፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፤
5. በጋራ መኖሪያ ቤት ማህበራት እንዲመሰረቱና በህግ አግባብ ተልዕኳቸውን እንዲወጡ ያበረታታል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ችግሮቹ እንዲወገዱ ያደርጋል፤
6. በአነስተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ነዋሪዎች በተለይም ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በቤት ልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
7. የቤት ልማቱ ሥራ ከድህነት ቅነሳ እና ከሥራ እድል ፈጠራ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
8. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ነዋሪው ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲሠራ በመንግሥትና በግል ባለሀብቶች አጋርነት እና በሌሎች የቤት ልማት አማራጮችን በመጠቀም የቤት ልማት ማካሄድ የሚችሉበት አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
9. በቤት ልማት ዘርፍ የሚሰማሩ አካላት ተቀናጅተው የሚሰሩበትን አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤
10. ከቤት ሽያጭ፣ ኪራይና የመሳሰሉት ተግባራት ላይ ጤናማ የገበያ ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችል ጥናቶችን ያጠናል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
11. በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወቅታዊ የቤት ፍላጎትና አቅርቦት፣ አጠቃላይ የተመዝጋቢዎች እና የቤት መረጃ በዝርዝር ይይዛል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ለዕጣ ብቁ የሆኑ ቆጣቢዎችን በመለየት መረጃውን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አዲስ ቤት ፈላጊዎችን ይመዘግባል፤

12. የቤት ፍላጎትና አቅርቦት መለየት የሚያስችል ዝርዝር ጥናት ያከናውናል፤ የቤት አቅርቦት ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሔ ሀሳቦችን ያመነጫል፤ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ያስወስናል፤ ይተገብራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
13. ቤቶች በልማት ወይም በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት በሚፈርሱበት ወቅት አስፈላጊው መረጃ ከሚመለከተው አካል ጋር ይለያል፤ ያጣራል፤ ያደራጃል፤ ቤት ለፈረሰባቸው አካላት ምትክ ቤት እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አካል መረጃዎችን ያስተላልፋል፤
14. የከተማ አስተዳደሩ ንብረት የሆኑ የመኖሪያ፣ ንግድ፣ ለኪራይ አገልግሎት የተገነቡ ቤቶች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በፍትሐዊነት ያስተዳድራል፤ ያከራያል፤ እንዲጠገን ያደርጋል፤
15. የከተማ አስተዳሩ ንብረት የሆኑ የመኖሪያ፣ ንግድ ቤቶች፣ ለኪራይ አገልግሎት ተገነቡ ቤቶች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች በህገ-ወጥ መንገድ ከያዙት አካላት ያስለቅቃል፤
16. የቤት አልሚ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፣ ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው አካል ያሰራጫል፡፡

## 22. <u>የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የተቋም አቅም ግንባታ ሥራን የሚያሳልጡ ዘመናዊ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን በመለየት በከተማ አስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊዉን የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
2. በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች የሰዉ ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚዉልበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ይተገብራል ፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤
3. የተቋማት አደረጃጀት ጥናት ላይ አስፈላጊዉን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያማክራል፤ አግባብነቱን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤
4. የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባራትንበተመለከተ ጥናት ያካሂዳል፤ ውጤቱን ለካቢኔ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተገቢዉን ይፈጽማል፤
5. በከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገቢዉ ስታንዳርድ መኖሩን ያረጋግጣል፤ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤ ያጸድቃል፤ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤
6. በከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻፀም ይከታተላል፣ የተገልጋዩን እርካታ ጥናት ያካሂዳል፣ የጥናቱን ውጤት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

7. የመንግስት ሰራተኞች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለዉ መንገድ መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ዉጤታማነቱን ያረጋግጣል፤
8. ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓትን ለማጠናከር የሚያስችል የማስፈጸም አቅም ግንባታ ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
9. የመንግስት ሰራተኞችን ወቅታዊ አፈፃፀም ምዘና የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤
10. የመንግስት ሰራተኛ በብቃትና በአፈጻፀም ላይ የተመሰረተ የምደባ፣ የደረጃ ዕድገትና የእርከን ጭማሪ፣ የጥቅማጥቅምና የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲተገበር ያደርጋል፤ ዉጤታማነቱን ይገመግማል፣ አስፈላጊዉን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፤
11. አግባብ ያላው የፌደራል ሕግ እንደተጠበቀ ሆኖ ለመንግስት ሰራተኛዉ የሚያስፈልጉ የሥራ መደቦች፣ የትምህርት የስልጠናና የሥራ ልምድ አጠቃላይ መመዘኛዎች ያወጣል፤
12. የመንግስት ሰራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ የደረጃ እድገት፣ ዝዉዉር፣ አበልና ጥቅማ ጥቅም፣ ስልጠናና የዲሲፕሊን አፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፤ በህግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
13. በህግ መሰረት የከተማ አስተዳደሩን የመንግስት ሰራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ለማቆየት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ዉሳኔ ይሰጣል፤
14. የከተማ አስተዳደሩን የሰዉ ሀብት መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ያደራጃል፤
15. የህዝብ አገልጋይነት አስተሳሰብ ያለዉ አመራርና ፈጻሚ ይገነባል እንዲገነባ ይሰራል፣ የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይደግፋል፤ ያረጋግጣል፤
16. በሚዘረጋቸው አዳዲስ አሰራሮች፤ አደረጃጀቶችና ማኑዋሎች ዙሪያ አጫጭር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
17. ሁሉም ተቋማት ዉጤታማ  አፈጻፀም እንዲኖራቸዉ የሚያደርጋቸዉን አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች ከራሳቸዉ ባህርይ አንጻር አጥንተው እንዲያቀርቡ ያበረታታል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
18. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሪፎርምና አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ውጤታማነት ይመራል፣ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ደረጃ ያወጣል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ይልካል፤
19. ከተማ አስተዳደሩ ተቋማት ላይ የሠራተኛ አፈጻጸም ምዘና ተግባራዊ እንዲሆን ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን በመፈተሽ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ የምዘና ሂደቱ በበላይነት ያስተባብራል፣ ያረጋግጣል፡፡

## 23. <u>የሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የደንብ ማስከበር ባለሥልጣንን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ይደግፋል፤
2. የብሔራዊ የፀጥታና የሰላም ፖሊሲን መሠረት በማድረግ የከተማውን የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳይ ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ከተማ አቀፍ ፖሊሲ ይቀርፃል፤ ስትራቴጂ ይነድፋል፤ ህግ ያመነጫል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤
3. በፀጥታ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና የፀጥታ አማካሪ ሆኖ ይሰራል፤ ለፀጥታና ሰላም አስጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተገቢ የሆነ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እንደ አግባብነቱ ራሱ ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የእርምት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
4. የግጭት መንስዔዎችን በጥናት ይለያል፣ ግጭት እንዳይከሰት ይከላከላል፤ ሲከሰትም ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ይፈታል፤
5. በከተማው ልዩ ልዩ ሀይማኖትና ቤተ-እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብነት ካላቸዉ የፌደራልም ሆነ የከተማው አስተዳደር አካላት፣ የኃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤
6. በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታት፣ በነዋሪው ደህንነት፣ ሰላም እና ፀጥታ አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ አግባብነት ካላቸው የፌደራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር እና ሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤ እንደአግባብነቱ ችግሮችን በተናጠል ወይም በጋራ ይፈታል፤
7. ህግና ሥርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
8. ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለማፍረስና በስውር የነዋሪውንና የመንግስትን ጥቅም ጉዳት ላይ ለመጣል የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ድርጅቶችን በመከታተል ነዋሪውንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤
9. ከጸጥታ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታ እና አቤቱታዎችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ እንዳግባብነቱ ራሱ ወይም በተጠሪ ተቋም ወይም በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት ቅሬታዎቹና አቤቱታዎቹ መልስ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
10. በፌደራል መንግስት የተመዘገቡ እና ፈቃድና እድሳት የተሰጣቸውን የሀይማኖት ተቋማት እና የብዙሀን ማህበራት ለመረጃነት ይመዘግባል፤ መረጃ ያደራጃል፤ ህገ-መንግስቱንና

ሌሎች ህጎችን አክብረው ስለመሥራታቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፣

11. ለህግ አስከባሪ አካላት እና ለነዋሪዎች በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት የህዝብ አገልጋይነት ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፣

12. የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎችና አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነው የጦር መሳሪያ ፈቃድ በሚመለከት የትብብር ደብዳቤ ይሰጣል፣ መረጃ ያደራጃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

13. በከተማው የጦር መሣሪያ አጠቃቀምና አያያዝ በተመለከተ የምዝገባ አፈጻጸምን ይከታተላል፣

14. የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ወንጀል፣ የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የማስተባበር ሥራዎችን ይሰራል፣ ተፈጽሞ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

15. የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት በህብረተሰብ ተሳትፎ እና በመስፈርቱ መሰረት ስለመከናወኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

16. የፀጥታ አስተዳደር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

17. የፀጥታ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

18. የመንግስትና የግል ተቋማትን እና ነዋሪውን በአካባቢያቸው የፀጥታ፣ ሰላም እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፉበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተቋማዊ አደረጃጀት ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣

19. በከተማው ክልል ውስጥ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ወቅት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የጉዳቱ መጠን እንዳይባባስ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣ በአደጋው ክልል ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰብ አካላት የህይወትና የንብረት ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፣

20. ስለሰላማዊ ሰልፍ፣ በአደባባይ ላይ ስለሚከናወኑ የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ስብሰባዎች ከንቲባውን ያማክራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

21. የመንግስትና የግል ተቋማት እንዲሁም የአካባቢ ቅጥር ጥበቃ በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፣

22. የሰላም እና የፀጥታ ምክር ቤት አደረጃጀትና አሰራር አጥንቶ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

24. <u>የባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ያጠናል፤ በሕግ መሠረት ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፤ የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ያደርጋል፤ የባህል ሙዝየሞችን ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፎች እንዲዳብሩ ያደርጋል፤
2. በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ ዕድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ተግባሮችን ያከናውናል፤
3. የባህል ዘርፍ ልማዳዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብ እና የፈጠራ ችሎታ በከተማው ውስጥ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግብረ-ገባዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን የሚያራምዱና የሚያስፋፉ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤
4. በከተማው አስተዳደር ሥር የሚገኙ ቤተ መጽሐፍትን፤ ቤተመዛግብትና አብያተ-መዘክርን ያስተዳድራል፣ ይመራል፤ እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ በባህል ዘርፍ የህዝብን ተሳትፎ መሠረት ለማስያዝ ሌሎች የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያድርጋል፤
5. የከተማውን የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽታ ለሀገር ውስጥና ለውጪ እህት ከተሞች የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፤
6. የከተማው የቱሪስት መስህቦችና መዳረሻዎችን ተለይተው እንዲታወቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፤ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የከተማው ነዋሪም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፍይ እንዲሆን ያድርጋል፤
7. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
8. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃዎችን ይወስናል፤ ተፈፃሚነቱን ይቆጣጠራል፤
9. በቱሪዝም የሰመረ አገልግሎት እንዲኖርና የቱሪስቶችም ደህንነት እንዲረጋገጥ ከሚመለከታቸው ጋር ይሠራል፤
10. የቱሪዝም ሴክተር የማስፈፀም አቅም ይገነባል፤
11. የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤
12. በከተማው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኪነ ጥበብና የቱሪዝም ተቋማትን፣ ማህበራትን፣ ክበባትን፣ ሞያተኞችን በሕግ መሠረት ይመዘግባል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

25. <u>የፍትህ ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሕግ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና አማካሪና ተወካይ ሆኖ ይሠራል፤
2. የከተማውን የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ያቅዳል፤ ያስተባብራል፤ በእቅዱ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ ክፍተቶችን እየለየ ድጋፍ ያደርጋል፤
3. የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብር ይተገብራል፤ አስፈፃሚ አካላት በዋና ዕቅዳቸው ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ ይደግፋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤
4. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል ፕሮግራም ይቀርፃል፤ ዕቅድ ይነድፋል፤በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይመራል፤ ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
5. የከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የአስተዳደሩና የነዋሪው መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል፣ ያስከብራል፣ የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
6. የከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያደርጉትን ውል ይመረምራል፤ ሕጋዊነታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል ወይም ይወስዳል፤
7. የከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤትንና የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በመወከል ወይም የከተማ አስተዳደሩንና የነዋሪውን መብትና ጥቅም ለማስከበር በስሙ በማንኛውም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባኤ በመቅረብ ክስ ይመሰርታል፣ መልስ ይሰጣል፣ የጣልቃ ገብ፣ የመቃወም እና የይግባኝ አቤቱታ ያቀርባል፤
8. የከተማ አስተዳደሩንና የነዋሪውን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባኤ በመቅረብ በስሙ ክስ ይመሠረታል፤ መልስ ይሰጣል፤ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ያቀርባል፤ ይግባኝ ይጠይቃል፤
9. የተሰጠው ውሣኔ የህዝብንና የመንግስትን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ካገኘው የመቃወም አቤቱታ ያቀርባል፤ ይከራከራል፤
10. የአስተዳደሩ ተቋማት ከአሰሪና ሰራተኛ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ የክርክር ጉዳዮችን ወክሎ ይከራከራል፤ ያስወስናል፤ ያስፈጽማል፤

11. በከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በእርሳቸው ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ ባለ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድ እንዲወሰን ውሣኔ ይሰጣል፤ በውሣኔ መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፤
12. በካቢኔው በሚፀድቅ ወይም በፀደቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት የራሳቸው የሕግ አገልግሎት እንዲኖራቸው የተፈቀደላቸው አካላትን የህግ አገልግሎቶች በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤ ሥራቸውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
13. በሌሎች ሕጐች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት የተያዙ ወይም ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት የማያዋጡ ወይም ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳርጉ ጉዳዮችን በአማራጭ ክርክር መፍቻ ዘዴዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤
14. በከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን ስር በሚወድቁ የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ነዋሪዎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን ፣ አረጋውያንን እና የመሳሰሉትን ወክሎ ክስ ያቀርባል፤ ይከራከራል፤
15. የገንዘብ አቅም የሌላቸው በከተማው ፍርድ ቤቶች በወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ስር በሚወድቁ የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ተበዳዮች እንዲካሱ፣ መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲሁም ከጉዳቱ ጋር የተያያዙ የፍትሐ ብሔር ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እነሱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ያቀርባል ወይም ይደራደራል፤
16. የሕግ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ የከተማው አስተዳደር ያወጣቸው ሕጎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይጠብቃል፤ የሕግ ወይም የውል ረቂቅ ያዘጋጃል፤
17. በካቢኔ የጸደቀ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ያሳትማል፤ የከተማው ሕጎችን መሰብሰብ ማደራጀት መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይፈጽማል፤
18. ነዋሪው በሕገ መንግስቱና በቻርተሩ የተሰጡትን መብቶችና ነጻነቶች እንዲያውቅና እንዲጠቀም ተገቢውን የሕግ ስልጠና ይሰጣል፤
19. ለከተማው አስተዳደር አመራሮችና ሰራተኞች እንዲሁም ለነዋሪው የንቃተ ሕግ ግንዛቤ ይሰጣል፤
20. በቻርተሩ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል የፈጸመ ሰው በሚመለከት ወንጀል ምርመራ በከተማው ፖሊስ ኮሚሽን

ተጣርቶ ሲቀርብለት ወይም እንዲቀርብለት በማድረግ በህግ መሠረት ቀርቦ ተገቢውን ውሳኔ እንዲያገኙ ክስ ያቀርባል፣ ይከራከራል፣

21. የተጀመረ ምርመራ በህግ መሠረት እንዲቆም ያዛል፣ ክስ ያነሳል ወይም የወንጀል ምርመራ በህግ መሠረት ይዘጋል፣ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

22. በፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር በውክልና የሚሰጡትን የወንጀል ጉዳዮች ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፤

23. በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወንጀል ጉዳዮችን በከተማው ፖሊስ ተጣርቶ ሲቀርብለት ወይም እንዲቀርብለት በማድረግ ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፤ የተጀመረ ምርመራ በሕግ መሠረት እንዲቆም ያዛል፤ ክስ ያነሣል ወይም የምርመራ መዝገቡ በሕጉ መሠረት ይዘጋል፤ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፤

24. በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የሚጣሉ የደንብ መተላለፍ ቅጣቶችን ያስፈፅማል፤ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

25. የከተማው አስተዳደር የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሣኔዎች ከሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ምክር ይሰጣል፤

26. በዐቃብያን ሕግ የሚሰጡ ውሣኔዎች በሕግ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

27. የቢሮው ዐቃብያነ ሕግ ካቢኔው በሚያወጣው መተዳደሪያ ደንብ ይተዳደራሉ፡፡

26. <u>የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ መዋቅራዊ ፕላን እና ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላኖች መሰረት በማድረግ ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ የመሬት ልማትና አቅርቦት እንዲሁም የከተማ ማደስ ጥናት ሥራዎችን ያከናውናል፤ እንዲከናወን ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

2. የልማት ቅደም ተከተል በማውጣት የመልሶ ማልማት ፕሮጀክት ጥናት፣ መርሀ ግብሮች፣ ጥቅል ዓላማዎች፣ ግቦች፣ የኢንቨስትመንት ዕቅዶች፣ በጀት፣ የዓላማ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችና የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

3. ለመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊው መሰረተ ልማት እንዲጠና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤ መጠናቱን ያረጋግጣል፤ ከገንቢዎች በሚገኝ ግብዓት የግንባታ ቅንጅት እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ያስገነባል፤

4. የመሬት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዲችል የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. ለልማት የተመረጡ አካባቢዎች በአካባቢ ልማት ፕላን መሰረት የተቀናጀ የከተማ ንድፍ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የሚውል መሬት ወሰን ያስከብራል፤ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤
7. በከተማው ውስጥ የተጎዱና ያረጁ አካባቢዎችን ለማደስ እንዲቻል የካሳ ክፍያ ሥርዓት ጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያከናውናል፤ በየጊዜውም እንዲሻሻል ያደርጋል፤ የነዋሪዎቹን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ ስታንዳርዱን ጠብቆ መልሶ ማልማት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
8. ለግንባታ ተረፈ ምርት መድፊያነት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን አስመልክቶ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
9. የልማት ተነሺዎች የምትክ ቤት ፍላጎት ያጠናል፤ የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤ ሲፈቀድም ለተነሽዎች ምትክ ቤት ድልድል በማድረግ እንዲሰጣቸው ለቤቶች ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፤ የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
10. ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬት፣ በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን፣ ባንክ የተደረጉ ክፍት መሬቶችን ወይም ይዞታዎችን ይመዘግባል፤ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል፤ የቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፤ የቦታዎቹን ዝርዝር መረጃ ለደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ያስተላለፋል፤ ከባለሥልጣኑ ጋር በመተባበር ለሕገወጥነት እንዳይጋለጡ ያደርጋል፤
11. በከተማው አስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ ያለውን የመሬት ሃብት ኦዲት ያደርጋል፤ በኦዲት ግኝቱ መሠረት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
12. የይዞታ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመመዝገብ ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እስኪተላለፍ ድረስ ጥበቃ ያደርጋል፤ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
13. በካርታ በተደገፈ መልኩ የከተማ ቦታ ደረጃ፣ የሊዝ መነሻ ዋጋ እና አማካይ የሊዝ ዋጋ ጥናት ያካሂዳል፤ ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

14. በከተማ ክልል ወስጥ ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬትን በመመዝገብ ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር ይሰጣል፤ በጨረታ እና በምደባ የሚተላለፉ ቦታዎችን ይለያል፤ ቦታው ለተጠቃሚ እስከሚተላለፍ ድረስ ከደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት የመከላከልና የመጠበቅ ሥራ ያከናውናል፤

15. መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው የተዘጋጁ የከተማ ቦታዎች ለአልሚዎች የሚተላለፉበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት መሬት ለባለመብት ያስተላልፋል፤ ቦታውን በመስክ ያስረክባል፤ በሊዝ ህግና ዉል መሠረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፤

16. አግባብ ባለው ህግና የሊዝ ውል መሠረት ግንባታ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ በሕግና በውል በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ መሬቱ መልማቱን ያረጋግጣል፤ መሬቱ ካለማ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

17. ለጊዜያዊ መጠቀሚያነት አገልገሎት የሚሰጡ ቦታዎችን በጊዜያዊ የሊዝ ውል ያስተላልፋል፤ የውል ጊዜያቸው ወይም አገልግሎታቸው ሲያበቃ ቦታውን በመረከብ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

18. ለልማት ይዞታቸውን የሚለቁ ባለይዞታዎች ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የይዞታ ማስለቀቅ ሂደቱን ይተገብራል፤ የተነሽ አርሶ አደሮችን ዝርዝር እና መረጃ ለአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ያስተላልፋል፤

19. የልማት ተነሺዎች ይዞታቸውን ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የምትክ ቦታ፣ ቤት፣ ተመጣጣኝ የንብረት ካሳ እና ሌሎች ክፍያዎች የሚያኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለልማት በሚለቀቀው መሬት ላይ ላለው ንብረት በህግ መሠረት ካሳ ይተምናል፤ እንዲተመን ያደርጋል፤ የንብረት ካሳና ሌሎች ክፍያዎችን ይፈጽማል፤ ምትክ ቦታ ያዘጋጃል፤ ምትክ ቦታ ያስተላልፋል፤

20. ለመሠረተ ልማት አውታር፤ ለመናፈሻ፣ ለአረንጓዴ ልማት እና ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች በመዋቅራዊ ፕላኑ መሠረት ቦታ ያዘጋጃል፤ ያስተላልፋል፤ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

21. ለልዩ ልዩ የግንባታ ሥራዎች ሊያገለግሉ የሚችሉ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች በመዋቅራዊ ፕላኑ መሠረት ከልሎ ይይዛል፤ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተሰጠ የማዕድን ማዉጫ ፈቃድ መሠረት በጊዜያዊ የሊዝ ውል መሬቱን ያስተላልፋል፤ የማእድን ማውጣት ሥራው ሲጠናቀቅ ወይም ፈቃዱ ሲሰረዝ ወይም የሊዝ ውሉ ጊዜ ሲያበቃ መሬቱን በመረከብ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

22. የመሬት ይዞታ እና የቤት አጠቃቀም ዓይነትና የባለይዞታዎች መረጃ ይይዛል፤ ይጠብቃል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለህጋዊ ባለይዞታዎች የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
23. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የነባር ቦታ ኪራይና የቤት ግብር ተመን አስልቶ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤
24. ከካሳ ጉዳይ በስተቀር ለግብር ሰብሳቢ ተቋማት፣ ለፍርድ ቤቶችና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት የማይንቀሳቀስ ንብረት ግምት አገልግሎት ይሰጣል፤
25. መደበኛ የይዞታ አገልግሎቶችን ያከናውናል፤ ህጋዊ ያልሆነ የይዞታ አስተዳደር አፈፃፀም ሲከሰት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
26. አግባብ ባለው ሕግና አሰራር መሠረት ለሰነድ አልባ ባለይዞታዎች በቋሚ መዝገብ በመመዝገብ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ማህደራቸውን ያደራጃል፤ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዘ ቦታ ወይም የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ቦታውን ያስለቅቃል፤ ምስክር ወረቀቱን ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤
27. ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺዎችን መልሰው በዘላቂነት ያቋቁማል፤ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ፡-
    ሀ) የማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይቀርጻል፤ ለከንቲባ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
    ለ) የልማት ሥራው በሚሰራበት ወቅት ተነሺዎች በተቻለ መጠን የሥራ እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፤
    ሐ) የተነሺዎችን የኢንቨስትመንት ሼር ባለቤትነት መብት ያስከብራል፤ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤
    መ) የልማት ተነሺዎች የኢንቨስትመንት ባለቤት የሚሆኑበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
    ሠ) ሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች የተገለጹትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይፈጽማል፤
28. የቦታ ይዞታ እና/ወይም የቤት ይዞታ ካርታ ኮፒዎችን እና ተጓዳኝ ይዞታ ሰነዶችን በማደራጀት ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ያስተላልፋል፤
29. በየደረጃው ያለውን የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት አመራር እና ፈጻሚን ህግና አሰራርን ተከትሎ እንደአግባቡ ያሾማል ወይም ይመድባል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል እና/ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ሠራተኞችን ያስተዳድራል፤

27. <u>የትራንስፖርት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን እና የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣንን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤
2. የትራንስፖርት አስተዳደር ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ለአገልግሎቱ ሥልጠት የሚያግዝ ስልት ይቀይሳል፤ ይተገብራል፤
3. የከተማ የትራንስፖርት ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፤ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ፍላጎት ያጠናል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
4. የከተማዋን ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ማለትም ዲፖዎችን፣ መናኃሪያዎችን፣ ተርሚናሎችን፣ ፌርማታዎችን፣ መጋዘኖችን ይገነባል፣ ያስፋፋል፣ ይጠግናል፣ ያስተዳድራል፤ እንዲሁም የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችን አስገንብቶ ለሚያስተዳድረው አካል ያስተላልፋል፤
5. የተቀናጀ የህዝብና ደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር የሚያግዙ የከተማ ትራንስፖርት ደንብ፣ መመሪያ፣ ደረጃዎች፣ መመዘኛዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች ያዘጋጃል፤ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
6. የአየር ብክለት የሚቀንሱና ለአየር ንብረት ምቹ የሚሆኑ የትራንስፖርት ዓይነቶች መጠቀምን ለማበረታታት የወጡ ህጎች ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
7. የከተማውን የትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጎት በመለየት፤ የህዝብና ደረቅ ጭነት ተሽከርካሪዎች ስምሪት ሥርዓት ይዘረጋል፤ አዳዲስ የትራንስፖርት መስመሮችን ይከፍታል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
8. የከተማውን የተማከለ የብዙሃን፣ የጭነትና ሌሎች የትራንስፖርት አገልግሎቶች የኦፕሬሽን ሥርዓታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤ ይመራል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያግዳል፤ የሥምሪት ድልድል ያዘጋጃል፤ ታሪፍ አጥንቶ ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. ለሕብረተሰቡ ተደራሽ የሆነ የትራንስፖርት መረጃ አገልግሎት ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤ የከተማው የትራንስፖርት አገልግሎት በቅንጅት እንዲመራ ዕቅድ ያወጣል፤
10. በትራንስፖርት አገልግሎቱ ውስጥ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ የሚያበረታታ ሥርዓት ይዘረጋል፤ የትራንስፖርት ማህበራትን ያደራጃል፤ ያሉትም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤
11. የከተማውን የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት መመዘኛ መስፈርቶች፣ ማንዋሎችና ደረጃዎች ያወጣል፤ ተፈጻሚ ያደርጋል፤ ተፈጻሚ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

12. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በብዙሃንና በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰሩ ኦፕሬተሮች፣ ማኅበራት፣ ድርጅቶችና ግለሰቦችን ያደራጃል፤ እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤ ለከተማው ትራንስፖርት ቅልጥፍናና ደህንነት መሥራታቸውንም ያረጋግጣል፤
13. የትራንስፖርት ደንቦች መከበራቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ ህግና ደንብ የሚተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
14. የህዝብን ደህንነት የሚጎዱ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በመከታተል ያግዳል፡፡

28. <u>የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. ከየተቋማቱ የሚቀርበውን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የሚገነቡ የመንግስት ህንጻዎች የስትራቴጂያዊና ዓመታዊ የፊሲካልና የፋይናንሻል ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በውይይት ያዳብራል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የሚገነቡ ህንጻዎች የታይፖሎጂ ዲዛይንና ዝርዝር ዲዛይን እንዲሁም ስፔስፊኬሽን እና የሥራ ዝርዝር ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ የተዘጋጁ ዲዛይኖችን ከግንባታ ሳይቶች ጋር የማጣጣም ሥራ ይሰራል ወይም እንዲሰራ ያደርጋል፤
3. በሥልጣን ክልሉ ውስጥ የግንባታ ፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፣ በሕግ አግባብ ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. የፕላን ስምምነትና የግንባታ ፈቃድ ከሚመለከተው አካል ያወጣል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. የሥራ ተቋራጭ፣ የዲዛይንና የግንባታ ሱፐርቭዥን አማካሪ ጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ጨረታውን ያወጣል፤ አሸናፊውን ይለያል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. የመንግስት ህንጻ ግንባታ በተገባው ውል መሠረት የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል፤
7. የከተማ አስተዳደሩን ወክሎ የህንጻና ተመሳሳይ የግንባታ ሥራዎችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ውል ይፈጽማል፤የኮንትራት ውል ያስተዳድራል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም በውሉ መሰረት መከናወኑን አረጋግጦ ይረከባል፤ ህንጻው ወይም ግንባታው ለተከናወነለት ተቋም በሰነድ ያስረክባል፤
8. ለግንባታና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚያስፈልገው መሠረተ-ልማት እንዲሟላ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ መሟላቱንም ያረጋግጣል፤

9. ግንባታው ሲጠናቀቅ ለሚመለከተው አካል የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀርባል፤ ፈቃዱን ይረከባል፤
10. በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚሰሩ ግንባታዎች ዲዛይን በአግባቡ መሰራታቸውን ይፈትሻል፤ ያረጋግጣል፤ በዲዛይናቸው እና በውላቸው መሰረት ስለመገንባታቸው ምርመራ ያደርጋል፤ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
11. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኮንስትራክሽን ገበያ አመላካቾችን እና የግንባታ ሞዴል ዋጋዎችን ያዘጋጃል፤ የግምት ቀመሮችን ያወጣል፤ ያጸድቃል፤ ይቆጣጠራል፤
12. በግንባታው ዘርፍ የተሰማሩ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን አቅም ይገነባል፤
13. የግንባታ ግብአት ናሙናዎችን በመውሰድ በላቦራቶሪ ጥራታቸውን ያረጋግጣል፤ ችግር በታየባቸው ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ ከሌሎች ተቋማትና ግለሰቦች አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል የግንባታ ግብዓት የጥራት ምርመራ ያካሂዳል፤ ውጤቱን ያሳውቃል፤
14. የግንባታውን ኢንዱስትሪ ለማዘመን የሚያስችሉ በዲዛይን፣ በኮንስትራክሽን ግብዓትና ግንባታ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን ያጠናል፤ ሲፈቀድም ይተገብራል፤
15. በውሉ መሰረት ባልተፈጸሙ፣ በሚታዩ ጉድለቶችና ጥፋቶች ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

29. <u>የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ አስተዳደሩን ተልዕኮ ሊያሳኩ የሚያስችል የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፣ ከተማ አቀፍ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮግራሞችን ያካሄዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ያስተዋውቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የከተማ አስተዳዳሩን የኢኖቬሽን፣ የስማርት ቴክኖሎጂ ፣ የአዳጊ ቴክኖሎጂ ፣ ከተማ አቀፍ የፖሊሲ ማሻሻያዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች እና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. በከተማ አስተዳደሩ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የተቀናጀ ለማድረግ ተገቢውን መረጃ ማሰባሰብ፣ መተንተን የሚያስችል ከተማ አቀፍ የመረጃ ቋት ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤ ቀጣይነቱን ያረጋግጣል፤

4. የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የኮምፒውተር መረቦች፣ አፕሊኬሽኖች፣ የኔትዎርክ ኮኔክትቪቲ እንዲቀናጁና እንዲናበቡ ያደርጋል፤
5. ለከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የሶፍትዌር ሲስተም ያለማል፣ እንዲለማም ያደርጋል፤ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
6. በከተማው አስተዳደር ተቋማት የሚለሙና የሚተገበሩ የጂኦ-ኢንፎርሜሽን ሲስተም በተመለከተ የተቋማትንና የከተማ አስተዳደሩን ፍላጎት መሠረት አድርጎ በጋራ ይሰራል፤
7. ለከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ያለማል፣ እንዲለማም ያደርጋል፤ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
8. በኮምፒውተር መረብ ዝርጋታ፣ በሶፍትዌር ሲሰተም ልማት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ዘርፍ ማማከር ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ተቋማት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤
9. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት፣ አስተዳደር እንዲሁም አጠቃቀም በተመለከተ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ያስተባብራል፤
10. የአስተዳደሩ የግዥና ንብረት አስተዳደር እና ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎችን ይለያል፤ ተለይተው አገልግሎት መስጠት የሚችሉትን ይጠግናል ወይም እንዲጠገኑ ያደርጋል፤ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትን በውስጣቸው መረጃ ያለመኖሩን አረጋግጦ እንዲወገዱ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤
11. የከተማ አስተዳደሩን መረጃዎች እና ሲሰተሞች ደህንነት ይቆጣጠራል፣ የደህንነት መቆጣጠሪያ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሲስተሞችና በመሰረተ ልማቶች ላይ የደህንነት ኦዲት ያደርጋል፤
12. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢዝነስ ሀሳብ ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ወይም ግለሰቦች ወደ ሥራ ማስገባት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. ለከተማው አስተዳደር ተቋማት የክላውድ ዳታ ሴንተርና የክላውድ አገልግሎት ተግባራዊ ያደርጋል፤ የክላውድ አገልግሎት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
14. የአስፈፃሚ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ያደርጋል፤ በከተማ አስተዳደሩ የለሙ መሰረተ ልማቶችና ሲስተሞችን ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤ ይመራል፤
15. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል ያደራጃል፣ በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤
16. የከተማውን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኦዲት በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤

17. የኢኖቬሽንና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ  የጥገና ፣ የቤተ ሙከራ ሰርቶ ማሳያ  እና የስልጠና ማእከል  ያደራጃል ፣ ያሰለጥናል፣ በበላይነትም ይመራል፤
18. ሀገር-በቀል ቴክኖሎጂዎችን  ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል ፣ ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
19. የከተማ  አስተዳደሩን    ሥርዓተ-ትምህርት  ከኢኖቬሽንና  ቴክኖሎጂ  ልማት  አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የትምህርት ተቋማት   ጋር በትብብር ይሰራል፤
20. የከተማ አስተዳደሩን የኢ-ገቨርናንስ ልማት እና የዲጂታላይዜሽን ሥርዓቶች  ለማስተግበር የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት  ይዘረጋል ፣ ተግባራዊ  ያደርጋል፤
21. በከተማ አስተዳደሩ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች ዕድገት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

30. <u>የጤና ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ጤና ተቋማትን እና የህክምና ማሰልጠኛ ተቋማትን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤
2. የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ደረጃ በማገናዘብ የከተማውን የጤና አገልግሎት ደረጃ ያወጣል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤ በጤና ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስፋፊያ ትምህርት ለነዋሪው አመቺ በሆነ ዘዴ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤
3. አጠቃላይ የሆነ የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ቅኝት ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤ ይከላከላል፤ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ወረርሽኝ ሲነሳ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይከላከላል፤
4. የእናቶችና ህፃናት ጤና ክብካቤ አገልግሎት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤
5. ከፌደራል መንግሥት እና ከዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ለተለያዩ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚሰጡ መድኃኒቶችንና የሕክምና መሳሪያዎችን ያሰራጫል፤ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
6. የባህል ህክምና ከዘመናዊ ህክምና ጎን ተጠናክሮ የሚሄድበትን ስልት ይቀይሳል፤
7. የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞችን ከሚያካሂዱ መንግሥታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ሕጋዊ ስምምነቶችና ውሎች ይፈጽማል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

8. የኤች.አይ.ቪ. ኤድስና ሌሎች በሽታዎች ቁጥጥር መረጃ ያጠናቅራል፣ ስርጭትን ለመግታት የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሰራል፤ በደማቸው ቫይረሱ ያለባቸው ወገኖች ድጋፍና ክብካቤ ያደርጋል፤ መረጃዎችን በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤
9. በከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ውስጥ የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዕቅድ መካተቱን ይከታተላል፤
10. የኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ አካላትን ያስተባብራል፤ የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
11. የጤና አጠባበቅ የምክርና የመረጃ አገልግሎት ያደራጃል፤ ይሰጣል፤
12. የጤና አግልግሎቱን ለማስፋት ከመንግስት፣ መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት እና ከግለሰቦች ጋር በአጋርነት የሚሰራበትን ሥልት ይቀይሳል፣ ይተገብራል፤
13. መንግስታዊ ጤና ተቋማት የሚሰጡትን የሕክምና መረጃዎች ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ እንደ አስፈላጊነቱም እርምጃ ይወስዳል፤
14. በምግባ ኤጀንሲ የምገባ አገልግሎት የሚያገኙ የጤና እክል ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የጤንነት ሁኔታ ይከታተላል፤ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤
15. በከተማው አስተዳደር ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አገልግሎት የሚስፋፋበትን አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል::

31. <u>**የንግድ ቢሮ**</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የንግድና ገበያ ልማት ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ከተማ አቀፍ ፖሊሲዎችን ይቀርፃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የከተማው የምርት ውጤቶች እንዲታወቁ ያደርጋል፤ አውደ-ርዕይ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ይሳተፋል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤
3. የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በከተማው ውስጥ በንግድና ገበያ ልማት ሥራ ላይ በሰፊው እንዲሰማሩ ያበረታታል፤ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ በንግድ ሥራ ለሚሰማሩና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለሚያቋቁሙ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች የንግድ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤
4. በከተማው ውስጥ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እንዲቋቋም ያበረታታል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤

5. የከተማውን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፤ የንግድ ስም ምዝገባ ያከናውናል፤ ያስተዳድራል፤ የንግድ ማህበራትን በህግ መሠረት በመመዝገብ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤
6. የገበያ ማዕከላት ያለማል፤ ደረጃ ያወጣል፤ ደረጃቸውን የጠበቁ የገበያ ማዕከላት መገንባታቸውን ይቆጣጠራል፤ የሚስፋፉበትንና የሚያድጉበትን ስልት ይቀይሳል፤
7. በሕግ ለሌላ አካል የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው ውስጥ የመሠረታዊ ንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት የገበያ ህግና ሥርዓትን መከተሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
8. ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ ጊዜ ያለፈባቸው ምርቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፤
9. የፍጆታ ምርቶችን የአገልግሎት ዘመንና የተዘጋጁባቸውን ንጥረ-ነገሮች ይዘት ሸማቹ ማወቅ በሚችልበት ሁኔታ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
10. በገበያው ውስጥ በቂ አቅርቦት መኖሩንና ግዥና ሽያጩ በተረጋጋ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለነጻ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ የከተማውን ነዋሪዎች ጥቅም ያስጠብቃል፤
11. የገበያ ዋጋ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተን እና የማቀነባበር ተግባራትን ያከናውናል፤ እንዳስፈላጊነቱ በጥቅም ላይ ያውላል፤
12. .የልኬት መሳሪያዎችንና መስፈሪያዎችን ትክክለኛነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ትክክለኛ ሆነው ያልተገኙ የልኬት መሳሪያዎችንና መስፈሪያዎችን እንዲወገዱ ያደርጋል፤
13. ለገበያ አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ቦታዎችን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤ የአገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤
14. ኢ-መደበኛ ንግድ ወደ መደበኛ ሥርዓት የሚገባበትን አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
15. ሕገ-ወጥ ንግድን ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## 32. <u>የትምህርት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ እንዲቻል ትምህርት ቤቶችን ያስፋፋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲጠገኑ እና መሰረተ ልማታቸው በአግባቡ እንዲሟላ ያደርጋል፤
2. የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ደረጃ በመጠበቅ የከተማውን አስተዳደር ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ መደበኛ ያልሆኑ፣ ቅድመ መደበኛ እና መጀመርያ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፤ መጻህፍት ያሳትማል፤ የትምህርት ግብዓት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
3. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች ደረጃ እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
4. የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን የአቅም ግንባታ ሥራ ያከናውናል፤
5. በከተማው ውስጥ አገር አቀፍ ፈተናዎችን ያስፈፅማል፤ በከተማው ውስጥ በሚገኙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተዘጋጅተው የሚሠጡ ፈተናዎችንና የምስክር ወረቀቶችን ህጋዊነት ያረጋግጣል፤
6. ከተማ አቀፍ የሆኑ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፤
7. በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፉ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሰጡ ያደርጋል፤ መደበኛና ኢ-መደበኛ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
8. ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለጎልማሶችና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
9. በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጡ የብቃት መመዘኛዎች መሠረት መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
10. ትምህርት ቤቶችን ማቋቋምና ማስፋፋት ለሚፈልጉ አካላት የመረጃ አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፤
11. በከተማው ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች የመማርና ማስተማር ሂደት በበላይነት ይመራል፤ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
12. በመንግሥት ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ፣ የደንብ ልብስ እና የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ከሚመለከተው አካል ይረከባል፤ ያሰራጫል፤

13. በመንግሥት ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና እንደአስፈሊጊነቱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

33. **<u>የሴቶች፣ ሕጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለማህበራዊ ችግር የተጋለጡ እና የወጣት ጥፋተኞች ማቆያና የተሃድሶ ማዕከላትን ያስተዳድራል፣ የማዕከላቱ ተገልጋዮች የሚመሩበትን የሥነ-ምግባር አሰራር ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. በሁሉም አስፈፃሚ አካላት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሌሎች የአስተዳደሩ አካላት የስርዓተ ፆታንና ህጻናት ጉዳይ በዕቅዳቸው ላይ ማካተታቸውን ይከታተላል፣ በስርዓተ ፆታ እኩልነት ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ይደረጋል፣
3. ሴቶች በከተማው አስተዳደር የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥምረት ይሰራል፣
4. በከተማ አስተዳደሩ የሚተገበሩ ህጎች የሴቶች፣ የአረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ደህንነት የሚያስከብሩ መሆናቸውን ይከታተላል፣
5. የሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶች ስለመጣሳቸው መረጃ ሲደርሰው ከሚመለከተው አካል ጋር ጉዳዩን በማጣራት ውጤቱን ለሚመለከተው የፍትህ አካል ያስተላልፋል፣ ይከታተላል፣
6. የሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ህጻናት፣ አረጋውያን እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣
7. ለሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህጻናት ፣ነዳና ተደዳደሪዎች እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብት፣ ደህንነትና ጥቅም የሚሰሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣
8. ሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በሚመለከት ከልማት ስትራቴጂ አኳያ ተቃኝቶ በወጣ ፕሮጀክት ላይ በከተማው ውስጥ ከሚሰሩ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ይመሰርታል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፣
9. የሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በሁሉም የጋራ ጥረት መፍትሄ እንዲያገኝ ያስተባብራል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣

10. ለሴቶች፣ ህጻናትና አካል ጉዳተኛ ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የልማት ሥራዎች ውስጥ ፍላጎቶቻቸው እንዲካተት ለማድረግ ከተለያየ ጥቃት መከላከል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ለማስከበር ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤
11. ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የኑሮ ሁኔታ የሚሻሻልበትን፤ በማህበራት የሚደራጁበትን እና የብድርና የቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያጠናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፤
12. በየደረጃው ያሉ የሕፃናት አደረጃጀቶችን አቅም በማጎልበት የሕፃናት ተሳትፎ እንዲያድግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
13. የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር የነዋሪዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት እና ዋስትና የሚሻሻሉባቸውና የሚጠበቁባቸው አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
14. የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ በማድረግ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በማህበረሰብ አቀፍ የተሀድሶ አገልገሎት እንዲታቀፉ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤
15. በማህበረሰብ አቀፍ ሊታቀፉና ሊደገፉ ያልቻሉ፣ በወንጀል ነክ ድርጊት ውስጥ የተሳተፉ እና ለሱስ ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት፣ ጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሰርቶ ለማደር አቅም የሌላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በአስተዳደሩና መንግስታዊ ባልሆኑ ማዕከላት ውስጥ ክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
16. የከፋ የምግብ ችግር ያለባቸው ህጻናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የአዕምሮ ህመምተኞች እና መሰል የህብረተሰብ ክፍሎች ይለያል፣ ይመዘግባል፣ ለምገባ ኤጀንሲ መረጃውን ያስተላልፋል፤
17. የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ሁኔታ ክትትል በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የተቋቋሙት ከምገባ ፕሮግራሙ እንዲወጡ ዝርዝራቸውን ለምገባ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤
18. በቢሮው ስር ያሉ የቀዳማይ ልጅነት እና የክብካቤ መስጫ ማዕከላትን ያስተዳድራል፤ ያስፋፋል፣ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
19. በከተማው አስተዳደር ተቋማት ውስጥ የህጻናት ማቆያ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤
20. የተለያዩ መንግስታዊ አገልግሎቶችን በነፃ ለማግኘት ለሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን አጣርቶ የድህነት ማረጋገጫ ማስረጃ ይሰጣል፤
21. የማህበራዊ ልማት ፈንድ የሚያስገኝ ፕሮጀክት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

22. መሥራት የማይችሉና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በሴፍቲኔት ቀጥታ ድጋፍ ማዕቀፍ ውስጥ ተጠቃሚ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣

23. በዘላቂ ማረፊያ ቦታ የሚፈፀሙ የባይተዋር ቀብሮችን መረጃ ይይዛል፣ ያጠናቅራል፣ የቀብር ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በበጎ አድራጎት ማህበር ወይም ድርጅት ውስጥ ቆይተው በሞት የተለዩ እና ሌሎች የባይተዋር ቀብር ያስፈፅማል፣

24. .በከተማው ውስጥ ያሉ መሠረታዊ እድር እና በየደረጃው የሚገኙት የእድር ምክር ቤቶችን ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ባህላዊና ታሪካዊ እሴታቸው ጠብቀው እንዲሄዱ ድጋፍ ያደርጋል፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያጠናክሩ ያበረታታል፣

25. የወጣቶች የሱስ ማገገሚያ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

## 34. <u>የገቢዎች ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፣ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሃብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነጻ መብቶች በህግ አግባብ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፣ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፣
3. ታክስ ከፋዮች በፈቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. የታክስ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል እና ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣
5. ለግብር እና ለልዩ ልዩ ገቢዎች አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፣
6. በከተማ የሚሰበሰቡ ገቢዎችን ወስኖ፣ ውሳኔዎችን ለግብር ከፋዮች በጽሁፍ ያሳውቃል፣ ብቃት ባለው መልኩ ለማከናወን የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎችን በመቀየስ ገቢ ይሰበስባል፣
7. በተዋረድ ባሉ የቢሮው አደረጃጀት የሚሰበሰቡ ገቢዎች ለፋይናንስ ቢሮ በወቅቱ ፈሰስ ያደረጋል፣
8. ግብር ከፋዮች ደረሰኝ እንዲያሳትሙ ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፣ አግባብ ባለው ህግ መሰረት የታክስ ህጎችን ያስከብራል፣
9. የቀን ገቢ ግምት ጥናት አግባብ ባለው ህግ መሰረት ያከናውናል፣ ይተገብራል፣

10. አግባብነት ካላቸው አካላትና የከተማ ነዋሪዎች እና ግብር ከፋዮች ጋር በአጋርነት ለመሥራት የሚያስችል ስልቶች በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤
11. የቢሮው ሠራተኞች ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

35. <u>**የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ**</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ አስተዳደሩን የስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላትን፣ የስፖርት ማዘወተሪያዎች፣ የስፖርት ልህቀት ማዕከላት እና የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን ያስተዳድራል፤ እንዲስፋፉና አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፤
2. በከተማው አስተዳደር የሚወጡ ሕጎች ሲዘጋጁ የወጣቶችን ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም የሚጠብቁ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ሁሉም አስፈፃሚ አካላት የወጣቶችን ጉዳይ በዕቅዳቸው ማካተታቸውን ይከታተላል፤ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
3. ለወጣቶች መብት፣ ጥቅም እና ደህንነት የሚሰሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ የወጣት መብት መጣሱን መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን ከሚመለከተው አካል ጋር በማጥናትና በማጥራት የህግ ከለላ ማግኘት እንዲችሉና ተገቢው መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
4. የወጣቶችን አቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ ያመቻቻል፤ ይሰጣል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት በተለያዩ በኪነ-ጥበብ፣ በቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ያበረታታል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤
5. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባባር ወጣቶች በማህበር እንዲደራጁ፣ የመስሪያ ቦታ እንዲመቻችላቸው፣ የማምረቻ መሳሪያ አቅርቦት፣ የብድርና የቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
6. ወጣቶች በከተማው አስተዳደር የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥምረት ይሰራል፤
7. ወጣቱን በመልካም ሥነ-ምግባር ለማነጽና የሀገር ፍቅር ስሜቱን ለማጎልበት የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣ተግባራዊ ያደርጋል
8. ወጣቶችን በሚመለከት ከልማት ስትራቴጂ አኳያ ተቃኝቶ በወጣ ፕሮጀክት ላይ በከተማው ውስጥ ከሚሰሩ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ይመሰርታል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

9. የአካል ጉዳትና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ወጣቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ፣ ከተለያዩ ጥቃቶች መከላከል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ለማስከበር ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤
10. ነዋሪው በስፖርት ለሁሉምና በባህላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
11. ለስፖርት ተግባራት የሚውሉ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች አቅርቦት የሚሟላበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል፤
12. አግባብ ባለው ህግ የስፖርት ህክምና አገልግሎት መደራጀቱን፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
13. የስፖርት ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትን እና ባለሀብቱ በስፖርት ኢንቨስት የሚያደርግበትን ስልት ይቀይሳል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
14. የስፖርት ማህበራት ያደራጃል፤ የማዘውተሪያ ስፍራ አጠቃቀም የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የስፖርት ማህበራትንና ክለቦችን እንዲሁም ጅምናዚየሞችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
15. የስፖርት ማህበራቱ በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤ ገቢያቸው ለአላማቸው ማስፈጸሚያ ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፤
16. በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የስፖርት ማሰልጠኛ ዘዴዎችን በማዘጋጀት ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞች የስፖርት ዳኞችና የመሳሰሉት እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤
17. የከተማውን ነዋሪ የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበት ያቅዳል፤ የስፖርት ውድድሮችንና የመዝናኛ ትርዒቶችን ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ ከሚመለከተው ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፤
18. የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በስፖርት ያላቸው ተሳትፎ እንዲጎለብት አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
19. የስፖርት ምክር ቤት በየደረጃው እንዲቋቋም ሕግ ያመነጫል፡ ሲጸድቅ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤
20. የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ከታችኛው የእድሜ እርከን የሚጀምርበት ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
21. በከተማ ደረጃ የብዙሃን የአካል እንቅስቃሴ እና የስፖርት መዝናኛ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፡፡

36. <u>የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ አስተዳደሩ ቃል አቀባይ በመሆን እና የአስተዳደሩ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን ይሰራል፣ በከተማ አስተዳደሩ ጉዳዮች ላይ የአስተዳደሩን አቋም ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣ በየደረጃው ያለው የመረጃና የመረጃ ልውውጥ መዋቅር ለየተመደበበት የአስተዳደሩ አደረጃጀት በቃል አቀባይነት ኃላፊነቱን የሚወጣበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
2. ለከተማው አስተዳደር የመረጃና የመረጃ ልውውጥ ወይም ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ሥራ አመራር ይሰጣል፣ በመስኩም በየደረጃው የተሳለጠ አፈፃፀም የሚኖርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ በየደረጃው ለሚከናወነው የከተማው አስተዳደር መረጃ ሥርዓትና ልውውጥ ሥራ ያስተባብራል፣
3. የከተማ አስተዳደሩን በተመለከተ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለሃገር ውስጥ ወይም ለውጪ ሚዲያ አካላት መግለጫ ይሰጣል፣ ከሚዲያዎች ጋር የተሳለጠ ተግባቦት እንዲኖር ያደርጋል፣ የከተማዉን ገፅታ ለመገንባት እና ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የትኛውንም ሚዲያ እና ድህረ ገጽ ይጠቀማል፣
4. በተቋማት ውስጥ ያሉ የኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተሮች በከተማ አስተዳደሩ በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት በሜሪት እንዲመደቡ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣
5. የድህረ ገፅና ማህበራዊ ሚዲያ ለማልማት ሥራዎችን ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ አሠራሮችን ይቀምራል፣ ይዘቶችን ይተነትናል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ግንኙነቶችን ያጠናክራል፣ ተደራሽነታቸውን ያሰፋል፣ በየመሥሪያ ቤቱ የሚከናወኑ የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት፣ ስርጭትና ክትትል ወጥና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
6. ለከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች፣ አመራሮችና ኮሚኒኬተሮች በየደረጃው ካለ መንግስታዊ መዋቅር ጋር ጠንካራ የግንኙነት ሥርዓት በመዘርጋት የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ይሰጣል፣ በመስኩ መልካም አፈፃፀም የሚመዘገብበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
7. የብዙሐን መገናኛ የዕለት ተዕለት ዘገባ ቅኝት እና መረጃዎችን በመሰብሰብ ይተነትናል፣ ጥናታዊ ሥራዎችን በማከናወን ለሚመለከታቸው አካላት ያሠራጫል፣
8. በከተማው ላይ የሚነሱ የተሳሳቱ መረጃዎች በመነሳት ህብረተሰቡ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኝ ያደርጋል፣ የሚመለከታቸው ተቋማትም ጉዳዩን በተመለከተ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጡ ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፣
9. የተለያዩ ሃገራዊ እና ከተማዊ ሁነቶችን መሠረት በማድረግ ከሚሰበሰቡ የህዝብ አስተያየት ጥናቶች በመነሳት በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን

በማዘጋጀት አመራሩ ህብረተሰቡን በአካል አግኝተው እንዲያነጋግሩ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ መድረክ ይፈጥራል፤ ተግባራዊና ውጤታማ መሆናቸውንም ይከታተላል፤

10. በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ወቅታዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ ይተነትናል፤ ያስተነትናል፤ የኮሙኒኬሽን ሥራ መነሻ ያደርጋል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፤
11. ልዩ ልዩ የህትመትና የኦዲዮ እና አውዲዮ ቪዝዋል ዉጤቶችን ያዘጋጃል፤ የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች የፎቶ ግራፍ፣ የኦዲዮ ቀረፃና የዓርማ እና የህትመት ዲዛይን ፖለቲካዊ፤ ህጋዊና ማህበረሰባዊ የሞራል ጥያቄ የማያስነሱ መሆናቸውን እና ከተቀመጠለት ዓላማ የተገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
12. .በኮሙዩኒኬሽን ሥራ ዙሪያ በሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላትና በዙሪያው የዳበረ እውቀትና የካበተ ልምድ ያላቸው ግለሰቦች መካከል በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የአጋርነት ሥርዓት ይዘረጋል፤
13. በሥራው ልዩ ባህሪ ምክንያት የተለየ ሙያ ያለው የሰው ሀይል በልዩ ሁኔታ መቅጠር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅጥሩን ለከንቲባ በማቅረብ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም ያስፈፅማል፤
14. በከተማው አስተዳደር የመረጃ ስርጭትና የመረጃ ልውውጥ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ የህዝብ አስተያየት ቅኝትና ጥናት ያከናውናል፤ በኮሙዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
15. በከተማው አስተዳደር ውስጥ የሚዲያ መሰረተ ልማት የሚጠናከርበትን፣ የሚስፋፋበትን ፣ በተገቢው ቴክኖሎጂና ብቃት ባለው የሰለጠነ ባለሙያ የሚደራጅበትን ሥርዓት ይቀይሳል፤
16. የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ለመሥራት ለሚፈልጉ ማንኛውም ሰው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤
17. አግባብ ባለው ሕግ ስለውጭ ማስታወቂያ መልካም ሥነ-ምግባር፣ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች የሚያከብር፣ የአገርን ክብርና ጥቅም የሚያስጠብቅ ይዘትና አቀራረብ ያለው መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## 37. <u>የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፤

1. በፕላኑ የተመላከቱ አረንጓዴ አካባቢዎችን ይለያል፤ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ሊወጣላቸው የሚችሉትን በሚመለከተው አካል በስሙ በማስመዝገብ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያወጣል፤
2. ተፋሰሶችን እና አረንጓዴ አካባቢዎችን ያስከብራል፤ ይጠብቃል፤ በተፋሰሶች እና በአረንጓዴ አካባቢዎች በፕላንና በዲዛይን ያልተደገፈ ልማት እንዳይካሄድ ይከላከላል፤ ተፈጽሞ ከተገኘ በሕግ መሰረት እንዲወገድ ያደርጋል፤
3. በከተማዋ መዋቅራዊ ፕላን መሰረት አዲስ የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች እና ፓርኮችን ያለማል፤ የነባር የህዝብ መዝናኛ ቦታዎችና ፓርኮችን ደረጃ ያሻሽላል፣ የለሙትን እና ደረጃቸው የተሻሻሉትን ለህዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፤
4. የተፋሰሶችን እና የአረንጓዴ አካባቢዎችን ቅደም ተከተል በማውጣት የልማት ወይም መልሶ የማልማት ዝርዝር ፕሮጀክት ያዘጋጃል፤ የተቀናጀ የአረንጓዴ ልማት ቦታ አቀማመጥ ዲዛይን በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ይተገብራል ወይም እንዲተገበር ያደርጋል፤
5. በአረንጓዴ ሽፋን ምጣኔ መሰረት የልማት ደረጃ ጠብቆ ወይም አስጠብቆ አረንጓዴ ቦታዎችን ያለማል፤ ወይም እንዲለማ ያደርጋል፤ ለወንዝና ለደን ስፍራነት መዋል የሚገባቸው ተጨማሪ ቦታዎች በማጥናት ያቀርባል፤ ሲወሰንም እንዲለሙ ያደርጋል፤ የለሙ ደኖችን ያስተዳድራል፤
6. ነባርና አዳዲስ ዘላቂ ማረፊያ ቦታዎችን ያለማል፤ የማስዋብ ሥራ ያከናውናል፤ ያስተዳድራል፤
7. በዘላቂ ማረፊያ የሚፈፀሙ መደበኛ ቀብሮችን መረጃ ይይዛል፤ ያጠናቅራል፤ የቀብር ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የአፅም ዝውውር ፈቃድ ይሰጣል፤
8. የመንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ግንባታ ዲዛይን አካል አድርጎ በሚያዘጋጃቸው የመትከያ ስፍራዎች ዲዛይን መሰረት በዋና እና በመለስተኛ መንገዶች ግራና ቀኝ ዳርቻዎች፣ አካፋዮች እና አደባባዮች ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አግባብ ያላቸውን የጥላ ዛፎች እንዲተከሉ ያደርጋል፤ ይተክላል፤ ይንከባከባል፤ ይጠብቃል፤
9. የአሽከርካሪዎችን የርቀት እይታ የሚጋርዱ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳር፣ አካፋይ እና የአደባባይ ዕጽዋት እንደአስፈላጊነቱ ያስወግዳል ወይም ይመለምላል፤
10. የከተማውን አየር ሚዛን የሚጠብቁ እንዲሁም ለከተማው ውበትና መናፈሻ ልማት የሚውሉ የእፅዋት ችግኝ ጣቢያዎችን ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤ ችግኞችን ለተጠቃሚዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያቀርባል፤

11. አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድለት በከተማው ውስጥ መልማት ያለባቸው ውጤታማ የሆኑና ያልታወቁ ወይም ያልተሞከሩ የውጭ እና ሀገር በቀል የዕፅዋት ዝርያዎችን እንዲለሙ ያደርጋል፤
12. በአዲስ የሚለሙና ነባር የለሙ ተፋሰሶችንና አረንጓዴ አካባቢዎችን ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤ እንዳግባብነቱ ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር በማቀናጀት እንዲፈፀም ያደርጋል፣
13. በአካባቢ ልማት ፕላን መሰረት የሠፈር ቁርጥራጭ ክፍት ቦታዎች በሠፈሩ ነዋሪዎችና እንደየአግባቡ በሌሎች ባለድርሻዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ የከተማው አረንጓዴ ልማት አካል ሆነው እንዲለሙ ያደርጋል፤ ይንከባከባል፤ ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፤
14. በተፋሰስና በአረንጓዴ አካባቢዎች ልማትና አገልግሎት ዘርፎች መሠማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ነዋሪዎች ወይም ሌሎች አካላት በየበኩላቸው የሚያቀርቡትን ጥያቄና የልማት ዕቅድ መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
15. የከተማውን ውበት የሚያሳድጉ አዳዲስ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ይተገብራል፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፣
16. በመንግድ ዳርና ዳር፣ ለከርብ ስቶን፣ በመሸጋገሪያ ድልድይ ግድግዳዎች፣ የባቡር ድልድዮች፣ አደባባዮች ለከተማው ውበት የሚጨምሩ ተገቢነት ያላቸው ቀለሞች በመቀባት እንዲዋቡ ያደርጋል፣ እንዲቀቡ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በመንገድ ዳርና ዳር መቀመጫ ወንበሮች ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣
17. በከተማው ውስጥ ያረጁና የከተማውን ውበት የሚያበላሹ  አጥሮች ቀለም እንዲቀቡ ወይንም በአዲስ  እንዲተኩ ያርጋል፣ያስጠግናል፣ ያስወግዳል፤ ባለቤት የሌላቸው፣ጊዜያቸው ያለፈ እንዲሁም ህጋዊ ያልሆኑ ማስታወቂያዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲወገዱ ያደርጋል፣ያስወግዳል፣
18. የዝናብ ውሃ በተፋሰስ መነሻ ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲሰርግ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤ ይተገብራል፤
19. የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፤ ያለማል፤ ያስተዳድራል፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግል ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ያበረታታል፤
20. የተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ሥራዎች ከአካባቢዉ ሥነ ምህዳር የሚስማሙ፣ የአገራችንን ሥነ ምህዳር የሚወክሉና ከአካባቢ ጥበቃ ዓላማዎች ጋር እንዲስማሙ አድርጎ ይፈጽማል፡፡

38. <u>የፕላንና ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ አስተዳደሩን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ተቋማትን ዕቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፤ ግብረ መልስ ይሰጣል፤ ይገመግማል፤ ይመዝናል፤ ደረጃ ያወጣል፣ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
2. የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. የአካባቢ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ ያፀድቃል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
5. የፕላን ዝግጅትና አተገባበር የጥናትና ምርምር ሥራዎች ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፤ ያሰራጫል፤
6. በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት የሕዝብ ተግባቦትና ስርፀት ሥራዎችን ያከናውናል፤ ተደራሽ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ስነድና ስርጭት ቋት ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤
7. የከተማው አስተዳደር ከተማ ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤
8. በሚያመነጫቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ከተማ ፕላን፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ የሴቶችንና የወጣቶች ጉዳዮች እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
9. የከተማ ፕላን በሚጥስ ማናቸውም አካል ላይ በሕግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፤ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
10. ከተማ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል መሠረታዊ የከተማ ካርታ ከሳተላይት ምስሎች ከሀገሪቱ ጂኦዴቲክ ካርታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤
11. የፀደቀ ፕላን በሕግ መሠረት  እንደየአግባቡ ያሻሽላል፤ ያጣጥማል፤
12. የፕላን፣ የዲዛይንና የግንባታ ፈቃድ ደረጃዎችን አፈፃፀም የሚመለከቱ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት እንዲያቀርቡና የመስክ ምልከታ እና ጥናት በማድረግ ሪፖርት ያቀርባል፤
13. የከተማውን ዝርዝር የሥነ ህዝብ ጥናትና ትንበያ ያካሂዳል፣ ውጤቱንም ለከተማው አስተዳደር አካላትና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤ የስነህዝብ ፖሊሲ በከተማው ውስጥ ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፤

14. የከተማውን አመታዊ አጠቃላይ የምርት እድገት ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት እድገት መነሻዎችን ይገምታል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤
15. የከተማውን የምርት እድገት ግቦች የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንትና የወጪና የገቢ ንግድ ከተማ አቀፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
16. ከአጠቃላይ ከተማ አቀፍ ምርት የኢንዱስትሪ፣ የአገልግሎት ዘርፎችና የከተማ ግብርና የተናጠል ድርሻን ይለያል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤
17. የከተማውን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤
18. ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎችን የሚዘረዝር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
19. ተዋረዳዊ አደረጃጀት ያላቸው የከተማው አስተዳደር አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ በየበኩላቸው የሚፈፅሟቸውን ተግባራት የሚያሳይ የተቀናጀ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን አፈፃፀም መርሀ ግብር ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
20. በጸደቀው ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት በአስፈጻሚ ተቋማት የሚከናወኑ ነባርና አዲስ የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፡፡

39. <u>የኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኢንቨስትመንት አመችነትን ያጠናል፤ ያስተዋውቃል፤ ያስተባብራል፤ ያስፋፋል፤ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
2. የእርስ በእርስ ቁጥጥርን ለማረጋገጥ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ይገመግማል፤ ለሚመለከተው አካል በማቅርብ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤

3. የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ሲቀርቡለት በህግ መሰረት መርምሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት የሚገባቸውን በማረጋገጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማግኘት እንዲችሉ አግባብ ላለው አካል ያስተላልፋል፤
4. ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች፣ የፋይናንስና የብድር አገልግሎቶች፣ የጥሬ ዕቃና የማምረቻ መሳሪያዎች የማግኘት ዕድልና የተለያዩ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚሟሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5. ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት እንዲሁም የከተማውን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚረዱ የማስተዋወቅ ሥራዎችን ይሰራል፤ ጽሑፎችን ያዘጋጃል፤ ያሠራጫል፤ ዓውደ ርዕዮችን፣ ዓውደ ጥናቶችንና ሴሚናሮችን ያዘጋጃል፤
6. ኢንቨስትመንትን ለማስፋት በባለሀብቶች፣ በመንግስታዊ መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤
7. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፤ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤ ከህግ አግባብ ውጪ ሆነው ሲገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ይሰርዛል፤ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
8. የድህረ-ኢንቨስትመንት የድጋፍና ክትትል ሥራን ለዚህ ዓላማ ከተቋቋሙ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
9. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላወጡ ባለሀብቶች የአንድ መስኮት አገልገሎት የሚያገኙበትን አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
10. እንደ ኢንቨስትመንቱ ዓይነት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የመሬት ፍላጎት ገምግሞ የመሬት ዝግጅት እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤ አግባብ ካለው አካል ጋር በመቀናጀት ለከተማው አስተዳደር አቅርቦ ያስወስናል፤ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይከታተላል፤ ስለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ከባለሃብቱ ጋር ይዋዋላል፤ ከህግ አግባብ ውጪ ሆነው ሲገኙ ይሰርዛል፡፡

40. **<u>የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን፤</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅቶችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ ለተመላከቱ አስፈጻሚ አካላት ተጠሪ የተደረጉ የአስተዳደሩ ልማት ድርጅቶች ተጠሪ በተደረጉላቸው አስፈጻሚ አካላት ይተዳደራሉ፤

3. የልማት ድርጅቶችን ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶቹን ያፀድቃል፣ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
4. የልማት ድርጅቶችን የኦዲት ሪፖርቶች ያፀድቃል፣ በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፤
5. የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ለማድረግ፣ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን ይዘረጋል፤
6. የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ችሎታ፣ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
7. አዳዲስ የኢንቨስትመንት መስኮችን እና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በማጥናት እንዲፈቀድ ለካቢኔ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
8. የልማት ድርጅቶች እንዲፈርሱ፣ እንዲዋሃዱ ወይም እንዲከፋፈሉ ለካቢኔ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. በከንቲባው አመራርና አቅጣጫ በመመራት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወር ለካቢኔ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲወሰንም አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
10. የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ ያዘጋጃል፣ በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለአስተዳደሩ ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ ለከንቲባው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
11. የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ መሰረዝን በሚመለከት ለከንባ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
12. የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም እና ሁኔታ የሚያሳይ የመረጃ ሥርዓት ያደራጃል፣ የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን፣ የብድር አወሳሰድና አመላለሳቸውን በቅርበት በመከታተል የተጠቃለለ የአፈጻጸም ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤
13. የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ማዕከላዊ አስቀማጭ ሆኖ ያገለግላል፣ የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም የሚመለከቱ የወል መረጃዎች ያሳውቃል፤
14. የአስተዳደሩ የልማት ድርጅት ቦርድ የሚያቀርበውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ቅጥርና ስንብት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡
15. የልማት ድርጅቶች ተሞክሮ የሚለዋወጡበትን መድረክ ያዘጋጃል፣ የድርጅቶቹን የአመራር አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
16. ተጠሪ የተደረጉትን የልማት ድርጅቶች በሚመለከት አግባብ ባለው በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ሕግ መሠረት ለአስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

17. በልማት ድርጅቶች እና በአክሲዮን ማህበራት ውስጥ አስተዳሩ ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤
18. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ይዞታ" ማለት ለባለሥልጣኑ ተጠሪ የሆኑ የአስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እና የአስተዳደሩን የአክሲዮን ድርሻ የሚመለከት ነው፡፡

41. <u>**የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን**</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. የኮንስትራክሽን ሥራ ዘመናዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በዲዛይን፣ በኮንትራት ይዘትና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራትና ቁጥጥር ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት እንዲሰፍን ያደርጋል፤
2. አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤
3. በኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚሳተፉ አካላት የሥራ ውል ዝግጅትና አፈጻጸም ወጥነት ኖሮት እንዲፈጸም ለማድርግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤
4. በኮንስትራክሽን ሥራ የሚኖሩ የሙያ ደረጃዎች እንዲዘጋጁ እና እንዲሻሻሉ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ አፈጻጸማቸውን ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል፤
5. አግባብ ባለው አካል ደረጃ የተሰጣቸውን የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ይመዘግባል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤
6. የግንባታ ህጎች፣ ኮዶችና ደረጃዎች እንዲዘጋጁ እና እንዲሻሻሉ ያደርጋል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊነቱን ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤
7. የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እና ግብዓቶች ደረጃ በወጣው ስታንዳርድ መሰረት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
8. በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣ የድርጅቶቹን አፈጻጸም መረጃ ይይዛል፤ ወቅታዊ የእርምት ሥራ እንዲያከናውን ያደርጋል እርምጃ ይወስዳል፤
9. የኮንስትራክሽን ሥራዎችን እና ግንባታዎችን ደህንነት በመከታተል ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጉዳቶችን ይለያል፤ ጉዳቶችን ለማስተካከል እንደአግባብነቱ የእርምት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
10. በኮንስትራክሽን ሥራዎች እና ግንባታዎች ላይ የሚፈጠሩ የአደጋ አጋጣሚዎች እና ጉዳቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይፈትሻል፤ ሪፖርት ያቀርባል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

11. የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ ደህንነት፣ በሰራተኞችና በህብረተሰቡ ጤንነት እና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፤
12. በግንባታና ዲዛይን እና የግንባታ ግብአት ማምረት ላይ የሚሳተፉ የሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ ግብዓት አምራችና አቅራቢዎችን፣ የግንባታ መሳሪያ አከራዮችን ይመዘግባል፤ የሙያና የብቃት ማረገገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይሰርዛል፤ ዕድሳት ያደርጋል፤ ህጋዊ ፈቃድ ይዘው መሥራታቸውን ያረጋግጣል፤
13. የኮንስትራክሽን ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር ያደርጋል፤ መረጃዎችን ይመዘግባል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤
14. የመሠረተ-ልማት ግንባታ ሥራዎችን በቅንጅት ለመሥራት፣ ዲዛይን ለማዘጋጀት፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል፦
    ሀ) የግንባታ ዕቅድና የዲዛይን ማቅረቢያ መመሪያ ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤ ስለአጠቃቀሙም ስልጠና ይሰጣል፣
    ለ) የግንባታ ሥራዎች ቅንጅት ለማጎልበት የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤ ግንባታ የሚያካሂዱ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤
15. በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሠረት የፕላን ስምምነት መረጃ በጽሁፍ ይሰጣል፤ የማይሰጥበት ሕጋዊ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ በህግ መሠረት ውሳኔውን ለባለጉዳዩ በጽሁፍ ያሳውቃል፤
16. አግባብ ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውንም ግንባታዎች አዲስ ግንባታ፣ የግንባታ ማሻሻያ ወይም እድሳት ፈቃድ፣ ለህዝብ ግልጋሎት ለሚውል የተጠናቀቀ ግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሁም ግንባታ የማፍረስ ፈቃድ በሕግ መሠረት ይሰጣል፣ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
17. የግንባታ ዲዛይን በከተማው መዋቅራዊ ፕላን፣ በሕግና በሕንጻ ደረጃ መሠረት በመመርመር ያጸድቃል፤
18. የመኖሪያ ግንባታን ከመኖሪያ ውጪ ወደ ሆነ ሌላ አገልግሎት መቀየር የሚፈልግ ሰው በጽሁፍ ሲጠይቅ እና የግንባታው ዲዛይን ለተለወጠው አገልግሎት መዋል የሚችል ሆኖ ሲገኝ፣ ንግድ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የመጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤
19. የውጭ ማስታወቂያ የሚተከልባቸውንና የሚለጠፍባቸውን ቦታዎች፣ ግንባታዎችና ሌሎች ቋሚ ነገሮች ደረጃ አውጥቶ ይወስናል፤
20. የውጭ ማስታወቂያ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ አግባብ ባለው ሕግና በማስታወቂያ ደረጃ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ የተፈቀደው ጊዜ ሲያበቃ መነሳቱን ያረጋግጣል፤

21. ፈቃድ የሚሰጥባቸው ማናቸውም ተግባራት በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በሥራ ላይ ስለመዋላቸው ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በፈቃዱ መሰረት ባልተከናወነ ሥራ ላይ በህግ መሠረት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ያደርጋል፤
22. የሰጣቸው ፈቃዶችን፣ የግንባታ ዲዛይኖችንና በከተማው ውስጥ የሚገኙ ግንባታዎችን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይይዛል፤ ያደራጃል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
23. የመሠረተ-ልማት ቅንጅትን፣ የግንባታ፣ የእድሳት፣ የመጠቀሚያ ወይም ማፍረስ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን የሚመለከቱ የፌደራል መንግስት ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ደረጃዎች እና ስልቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
24. ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኞችና ለሌሎችም ተጠቃሚዎች ተደራሽ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ተገቢው እርምት እንዲደረግ ያደርጋል፡፡

42. <u>የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ህንጻና ንብረት አስተዳደር ላይ ለከተማው አስተዳደር የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያማክራል፤
2. ስልጣኑ በህግ ለሌላ አካል ወይም ለሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ካልተሰጠ በቀር የከተማውን አስተዳደር ህንፃዎችንና ቋሚ ንብረቶችን ይመዘግባል፤ በበላይነት ያስተዳድራል፤ ያድሳል፤ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች በመለየት እንዲጠገኑ ያደርጋል፤
3. የህንጻና ንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀም ዘመናዊ ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ምድረ ግቢን ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
4. የመንግስት ህንፃዎች አጠቃቀም፣ ለተጠቃሚው ያላቸው ተደራሽነት እና ከወጪ አንፃር ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
5. የተቋማትን ፍላጎት፣ የሥራ ባህሪይ እና የተገልጋይ ሁኔታን በማጥናት የተቋማትንና የሥራ ክፍሎችን የሥራ ቦታ ይደለድላል፤
6. የከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች የኪራይ ደረጃ አጥንቶ ይወስናል፤ ለመንግስት አገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፤
7. በከተማው ውስጥ ባለቤት የሌላቸው ህንጻና ንብረቶችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተረክቦ ያስተዳድራል፤

8. የመንግስት ህንፃዎች ወጥ የሆነ ስታንዳርድ እና ዲዛይን እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤ ያስገነባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
9. የህንጻ አስተዳደር ሥራዎች የተቀላጠፉና ውጤታማ እንዲሆኑ የውስጥ አደረጃጀት እና የቢሮ ቁሳቁስ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤
10. በመንግስት የንብረት አያያዝ ሥርዓት መሰረት የመንግስት ንብረቶች በአግባቡ ስለመያዛቸው እና ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የንብረት ኦዲት ያደርጋል፤
11. በባለስልጣኑ የህንጻና የንብረት ኦዲት ውጤት መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ያልወሰዱ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለይቶ ተጠሪ ለሆነለት ቢሮና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤
12. አግባብ ባለው ህግ ቋሚ ንብረቶች ዋጋ እንዲወጣላቸው እና በየዓመቱ የዕልቀት ዋጋ እንዲሰላላቸው በማድረግ መንግስት የቋሚ ንብረቶች የያዙትን ዋጋ እንዲያውቅ ያደርጋል፤
13. ባለስልጣኑ በሚያስተዳድራቸው ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶችን ይከላከላል፤ ተፈጽሞም ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
14. የመንግስት ህንፃዎች የሚገነቡበት ቦታ ያስፈቅዳል፤ ይመዘግባል፤ ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይጠብቃል፤
15. የመንግስት ህንፃዎች የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ የጽዳትና ውበት፣ የጥበቃ፣ የመጀመሪያ ህክምና፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፣ የመኪና እጥበት እና የህፃናት ማቆያ አገልግሎቶች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

43. <u>የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማ ግብርና ምርት በጥራት የሚመረትበት፣ ለገበያ የሚቀርብበትን እና የከተማ ግብርና ልማት የሚጎለብትበት ስልት ይቀይሳል፤ ያስፈጽማል፤
2. ነዋሪዎች በከተማ ግብርና እንዲሳተፉ ያበረታታል፤ በተለያዩ የግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ምርትና ምርታማነታቸዉ እንዲጨምር ዘመናዊ የግብርና ግብዓት እንዲቀርብላቸው ሙያዊ ድጋፍና ምክር እንያገኙ ያደርጋል፤
3. የእንስሳት በሽታዎች ስርጭትን ያጠናል፤ በበሽታ ስርጭት የተነሳ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለመንግስትና ለአርቢዎች ያሳውቃል፤ ለእንስሳት አርቢዎች የእንስሳት ህክምናና የክትባት አገልግሎት ይሰጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የዕብድ ውሻ በሽታ መከላከያ ክትባት ይሰጣል፤ ታክመው መዳን የማይችሉ እና ባለቤት የሌላቸውን እንስሳት ያስወግዳል፤

4. ለእንስሳት አርቢዎች የማዳቀል አገልግሎት ይሰጣል፤ የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ለአርሶ አደር እንዲዳረስ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ይከታተላል፤ ለአርሶ አደሮች ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤
5. የእንስሳት እና የዕጽዋት ማራቢያና ማባዣ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤
6. የእንስሳትና የእጽዋት የኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል፤ በከተማው ውስጥ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና የአገልግሎት ዘመናቸው ያላለቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መድሃኒቶችን ለሚያስወግድ አካል ያሳውቃል፤
7. በመዋቅራዊ ፕላኑ ለእንስሳት፣ ለሰብል፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ገበያዎችና ለከተማ ግብርና የተከለሉ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት እንዲዘጋጁና በዘመናዊ መንገድ እንዲለሙ ያደርጋል፤
8. በግል የሚቋቋሙትን የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች፣ ላብራቶሪዎች፣ የቆዳና ሌጦ መጋዘኖች፣ ጸረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖችና መሸጫ መደብሮች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ደረጃና ጥራት ጠብቀው መሥራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
9. በህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት እና በግል ቄራ ድርጅቶች የእርድ እንስሳትና የሥጋ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ሕገወጥ የእንስሳት እርድና በሕገወጥ መንገድ የታረዱ ስጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣
10. ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮች ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር በመቀናጀት የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የመኖሪያ ቤቱ እስኪዘጋጅ ድረስ የቤት ኪራይ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
11. .በልማት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተነሱ ተነሺ አርሶ አደሮችን ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ፈጠራ ፕሮግራሞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በተሰጣቸው የክህሎት ሥልጠና መሠረት በአካባቢው በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ቅድሚያ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤
12. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ በዘላቂነት ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤ ለፕሮጀክቱ የሚያገለግሉ የማምረቻ እና የመሸጫ ማእከላትን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

13. ኑሯቸዉ በግብርና ሥራ ላይ የተመሠረተ አርሶ አደሮች የያዙት መሬት መጠን ልኬት እንዲወሰድና የባለይዞታነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፤
14. አርሶ አደሮች ባላቸው ይዞታ ላይ በግላቸው፤ ከአርሶ አደር ጋር በመደራጀት ወይም ከባለሀብት ጋር በመጣመር እንዲያለሙ አሰራር ይዘረጋል፤ ያስተባብራል፤ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤
15. ምንም ገቢ የሌላቸዉና መሥራት የማይችሉ አርሶ አደሮች ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማህበራዊና የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
16. ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮች የተሰጣቸውን ካሳ አቀናጅተው ወደ ተሻለ ልማትና የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤
17. ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ የልማት ተነሽዎችን መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤
18. የተሻለ ልምድና ሀብት ያላቸዉ ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦችን በመለየት አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ በግል ይዞታቸው ወይም ተደራጅተዉ የሚሰማሩበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግበራዊ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤
19. በልማት ይዞታቸውን የሚለቁ ባለይዞታዎች ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የይዞታ ማስለቀቅ ሂደት መተግበሩን ይከታተላል፤
20. በልማት ሥራዎች እና መልሶ ማልማት ተነሽ ለሆኑ አርሶ አደሮች ተገቢውን የካሳ ግምት መተመኑን፤ የካሳ ክፍያ መፈጸሙን፤ ምትክ ቦታ መዘጋጀቱን፤ መሸንሸኑን፤ የምትክ ቤት ማግኘታቸውንና መቀበያ ሰርተፊኬት መሰጠቱን ይከታተላል፡፡

44. <u>የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ብሎክን ማዕከል አድርጎ የተደራጀውን ሕብረተሰብ እና የህብረተሰብ ተሳትፎ ካውንስል አደረጃጀትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ያደራጃል፣ ያጠናክራል፣ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣ ክፍተቶች ሲኖሩ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
2. በህብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩ ተግባራትን ይለያል፤ ተሳትፎ የሚጎለብትበትን ስልት ይቀይሳል፤ ስለህብረተሰብ ተሳትፎ አደረጃጀትና ጠቀሜታ ለህብረተሰቡ ያስተዋውቃል፤ ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤

3. የተቀናጀ የህብረተሰብ ተሳትፎ ውጤታማ እንዲሆን መመሪያዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች ያዘጋጃል፤ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
4. ህብረተሰቡ የብሎኩን የልማት ፍላጎት እንዲመለስ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል፣ የሠላምና ፀጥታ፣ የሥራ አጥነት እና የማህበራዊ ችግሮች ለማስወገድ ነዋሪው በባለቤትነት እና በፍላጎት እንዲደራጅ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
5. አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በመፈለግ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድ የአካባቢውን ህብረተሰብ የልማት ሥራ ያግዛል፤ ከህብረተሰቡ የሚሰበሰቡ የቁሳቁስ፤ የጉልበትና፤ የገንዘብ መዋጮዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
6. በብሎክ ነዋሪዎች የተለዩ ፍላጎቶች የሚሟሉበትን እና የተለዩ ችግሮች የሚፈቱበትን ዕቅድ ከብሎክ ካውንስል ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያስፀድቃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
7. ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት በብሎክ የተደራጁ ማህበረሰብ አቀፍ የህብረተሰብ ተሳትፎ ካውንስሎችን ችግሮቻቸው የሚፈቱበት እና ጥያቄዎቻቸው ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ ያመቻቻል፤ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም በየደረጃው ላሉት አስተባባሪ ካውንስሎች ከመፍትሔ ሀሳብ ጋር ያቀርባል፤ ያስወስናል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
8. በብሎክ ውስጥ የተሰሩ ማንኛውም የልማት ሥራዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ከብሎክ ካውንስል ጋር በመሆን ክትትል ያደርጋል፤ የማስተካከያ ሥራዎችን ያከናውናል፤
9. በብሎክ በተምሳሌትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሁለገብ የህብረተሰብ ተሳትፎ ያደረጉ እና የልማት ሥራዎችን ያከናወኑ ካውንስሎችን በመለየት እውቅና ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ልምዳቸውን ቀምሮ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
10. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በራስ መልካም ፈቃድ፣ ተነሳሽነት እና ያለማንም አስገዳጅነት ለሚሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤
11. በበጐ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰማሩ ወጣቶች፣ የሞያ ማህበራት፣ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ያስተባብራል፣ የእውቅና እና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያበረታታል፤
12. ህብረተሰቡ ያለውን እውቀትና ችሎታ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ላይ እንዲያውልና ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችለውን የበጎ ፈቃድ ባህል እንዲያጎለብት ያበረታታል፤

13. በከተማው የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በእቅዶቻቸውና በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አካትተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
14. በከተማው ዘላቂ የበጐ ፍቃድ ፍኖተ ካርታ ያዘጋጃል፣ ምክር ቤት እንዲደራጅ ያደርጋል፣ ምክር ቤቱ የሚሳተፍበትን የአገልግሎት መስኮች ይለያል፣ ስልጠና ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
15. የከተማውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማቃለል የከተማ ነዋሪ፣ የንግድ ድርጅቶች እና መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እና የማህበራዊ አገልግሎት ግዴታቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

45. <u>የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል በማቋቋም ከአደጋ በፊትም ሆነ በአደጋ ጊዜ እና በኃላ የተማከለ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ በከተማ ደረጃ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
2. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች መንስኤና የተጋላጭነት ደረጃና ትንተና መረጃ ያሰባስባል፤ የቅድመ አደጋ ጠቋሚ ጥናቶችን በማካሄድ አስፈላጊውን የቅድመ ማስጠንቀቂያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤
3. በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ ሊከሰት የሚችል አደጋን የመከላከል እና የአደጋ ጉዳት ቅነሳና የማጣጣም ሥራን ይሰራል፤ ሌሎች ተቋማትም እንዲሰሩ ያደርጋል፤
4. በከተማዋ የሚገኙ ተቋማት የአደጋ ስጋት ቅነሳ እቅድን በልማት እቅዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ያደርጋል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይከታተላል፤
5. የተቋሙ ባለሙያዎች፣ ልዩ ልዩ ተቋማትና ህብረተሰቡ ስለ አደጋ ሥራ አመራር ስልጠና የሚያገኙበት የስልጠና ማእከል ያደራጃል፤
6. በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች ያከናውናል፤ እንዲከናወኑም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በአደጋ ምላሽ እቅድ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤እንዲወሰድ ያደርጋል፤
7. የአደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን፣ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ደረጃዎች፣ የእሳትና የጭስ፣ የነበልባል እና ሌሎች አደጋ ጠቋሚ መሳሪያዎች በአገልግሎት መስጫ ልዩ ልዩ ተቋማት መተከላቸውንና በአግባቡ መሥራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

8. ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለህዝቡ ለማድረስ ሁሉን አቀፍ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ለህብረተሰቡ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን፣ በአደጋ ወቅት መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች እና የደረሰውን አደጋ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን የማሰራጨት ተግባር ያከናውናል፤
9. በአደጋ የተጎዱና የተፈናቀሉ አካላት የአጠቃላይ የጉዳት መጠን፣ ክስረትና ፍላጎት መረጃ በማሰባሰብ ይተነትናል፤ ያደራጃል፤ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተከታትሎ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤
10. በከተማው የአደጋ ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች ወቅታዊና ተደራሽ የሆነ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ሥራ አመራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
11. በተከሰቱ አደጋዎች ምክንያት የተፈጠሩ ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች መጠን የአፋጣኝ መረጃ ትንተና መሰረት በማድረግ በከተማ ደረጃ የአደጋ ጊዜ አስቸኳይ አዋጅ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
12. በአደጋ ክስተት ወቅት የሚመለከታቸውን መስሪያ ቤቶችና ነዋሪዎችን በማስተባበር የነፍስ አድን እርዳታን ጨምሮ ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፤ ለድንገተኛ አደጋዎች የቅድመ ሆስፒታል ህክምና እና አምቡላንስ አገልግሎት ይሰጣል፤
13. መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ድርጅቶችን እንዲሁም ሌሎች በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦትና መልሶ ማቋቋም ተግባራት ላይ ሚና ያላቸው ተቋማት ያስተባብራል፤
14. የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር መሰረተ ልማቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
15. በአደጋ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ጊዜያዊ ድጋፍና መልሶ የማቋቋም ተግባር ያከናውናል፤
16. ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦት ምላሽ ሥራ ብቻ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ በመጠባበቂያነት ይይዛል፤ ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰራጫል፤
17. አደጋ ስጋት ቅነሳ ሥራዎች እና በአደጋ ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽና እርዳታ አቅርቦት አገልግሎቶች ላይ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞችን ሙያዊ ስልጠናዎች በመስጠት የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ተግባራት ላይ ተባባሪ እንዲሆኑ ይሰራል፣
18. በአደጋ ሥራ አመራር ሥርዓት ውስጥ ተሳታፊ በሚሆኑ ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለማስፈንና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የጋራ መድረኮች ይመሰርታል፣ ያስተባብራል፤

19. አደጋ በይፋ መገለጹን ተከትሎ ሲወሰን ከተለያዩ አካላት ለምላሽ ሥራ የሚውል ሀብት ያሰባስባል ፤

20. የኮሚሽኑን ፓራ ሚሊተሪ ሰራተኞችን ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

## 46. የህብረት ሥራ ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አግባብ ባለው ህግ መሰረት የህብረት ሥራ ማህበራትንና የጋራ ህንፃ ባለቤቶች ማህበራትን ያደራጃል፤ ይመዘግባል፤ ያስፋፋል፤ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ማህበሩ ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰርዛል፤
2. የህብረት ሥራ ማህበራት በዩኒየንና በፌዴሬሽን ደረጃ እንዲደራጁ ያበረታታል፤ የህብረት ሥራ ማህበራት ባንክ የሚቋቋምበትን መንገድ ያጠናል፤
3. ለገንዘብና ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁትን አባላት ቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና ቁጠባ ድርሻቸውን ከፍ በማድረግ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡበትን አሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
4. ባህላዊና አገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት ወደ ዘመናዊ የህብረት ሥራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ የጥናቱንም ውጤት ያስተዋውቃል፤ ያሰራጫል፤ ለተግባራዊነቱም ይሰራል፤
5. የህብረት ሥራ ማህበራት ሥራ አመራርና የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ አሰራርን እንዲከተል አስፈላጊውን የስልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ይሰጣል፤
6. የህብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ ይመረምራል፤ ሂሳብ አጣሪም ይመድባል፤ ሲፈርሱም ከመዝገብ ይሰርዛል፤ አግባብ ባለው ህግ የህብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉትን የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ሥርዓት ይከታተላል፤
7. የህብረት ሥራ ማህበራት የገበያ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ እና ሌሎች መሰል ተቋማት አስተዳደርና አጠቃቀምን በሚመለከት አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ችግሮቻቸው የሚፈቱበትን አግባብ ያመቻቻል፤ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
8. የህብረት ሥራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ በአገር ውስጥ ሸማቹና አምራቹ በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. በከተማዋ የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት ወይም ዋጋ እንዲኖራቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እና የእጅ ጥበብ ምርቶች እንዲያድጉ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

10. የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚረዳ የገበያ ጥናት በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ ያሰራጫል፤ አግባብ ባለው ህግ ለህብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡ ማበረታቻዎችን ያጠናል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤
11. የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ እና ለህብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚበጁ ልዩ ልዩ የፕሮጀክት ሃሳብን በማመንጨት፣ አዋጭነታቸውን በማጥናት እና በማዘጋጀት ማህበራት እንዲሰማሩባቸው ያበረታታል፤
12. የህብረት ሥራ ማህበራት ሞዴል የመተዳደሪያ ደንቦችን ያዘጋጃል፤
13. የኅብረት ሥራ ማህበራት በተመለከተ የኢንስፔክሽን ሥራ ያከናውናል፤ የኦዲትና የህግ ምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
14. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ብቃት ይመዝናል፤ እውቅና እና ማበረታቻ ይሰጣል፤
15. የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደጋ ስጋት ለመቀነስና ለመከላከል የሚያስችል የአነስተኛ መድን ዋስትና አገልግሎት እንዲስፋፋ ሊያደርግ ይችላል፤
16. በጋራ መኖሪያ ቤቶች ህብረተሰቡን የሚያውኩ እና ህገ-ወጥ ተግባራትን የሚፈጽሙ አካላትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ቁጥጥር ያደርጋል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

47. <u>**የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን**</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአጠቃላይ ትምህርት እና በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ከሀገሪቱና ከከተማ አስተዳደሩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ሥርዓተ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳል፤
2. አጠቃላይ የትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በህግ የተቀመጠውን የትምህርትና ስልጠና ስታንዳርድ፣ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት ማሟላታቸውን፤ አግባብነቱና ጥራቱ ደረጃውን ጠብቆ ስለመፈፀሙ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
3. አጠቃላይ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤ ለሰልጣኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ይሰጣል፤ ብቁ ሆኖ ለተገኘ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
4. አጠቃላይ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማትን እና የሙያ ብቃትን መረጃ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤
5. የአጠቃላይ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ብቃት እና ምዘና መከታተያና መገምገሚያ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

6. ፍቃድ ያላቸው የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጥራታቸው ከስታንዳርድ በታች በሆኑ ተቋማት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ከሰረዘ ከንግድ ሥራ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ለንግድ ቢሮ በጽሁፍ ያሳውቃል፤

7. በሕገ ወጥ መንገድ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ያገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ላይ የሙያ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፣ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ እንዲጠየቁ ስልጣን ላለው አካል ያሳውቃል፤

8. የሙያ ብቃት ፍቃድ እያላቸው አግባብ ያለው ህግ በሚጥሱ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

9. የሙያ ብቃት ፍቃድ ሳያገኙ ወይም በሌሎች ተቋማት የሙያ ብቃት ፈቃድ የሚሰሩ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማትን አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ እንዲጠየቁ ሥልጣን ላለው አካል ያሳውቃል፤

10. ለትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ዕውቅና ይሰጣል እውቅና አግኝተው የሚሠሩ ትምህርት ቤቶች በሀገር ደረጃም ሆነ በከተማ ደረጃ በሚወጡ ህጎች የተቀመጡ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

11. በትምህርት ተቋማት የህብረተሰቡን ተሳትፎ ሊያረጋግጡ የሚችሉ አደረጃጀቶች፣ የወላጅ፣ የተማሪ፣ የመምህራን ፎረም፣ የተማሪ ክበባት ስለመኖራቸው ያረጋግጣል፤ እንዲሁም የትምህርት አገልግሎት ክፍያዎች የወላጆችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ከተቋማቱ ጋር ይመክራል፤

12. ከሥራ ዓለምና ከተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና ወስደው ብቁ ሆነው ለተገኙ ተመዛኞች የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

13. በምዘና ጣቢያነት አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ኢንዱስትሪዎችን ይለያል፤ ለምዘና ምቹ ሆነው እንዲደራጁ ያደርጋል፤ የምዘና ሥራ ይከታተላል፤ በበላይነት ይመራል፤

14. ከባለስልጣኑ ውጭ በከተማው አስተዳደር ከሚገኙ ተቋማት ወይም ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የምዘና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ አካላትን በመምረጥ ዕውቅና ይሰጣል፤

15. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት፣ የኢንዱስትሪ መዛኞች እና ሱፐርቫይዘሮች አሰራር ለመከታተል የሚያስችሉ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

16. መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ብቃት ያላቸው ሰራተኞች በሚፈለጉበት ወቅት የሙያ ብቃት ምዘና በመስጠት ብቃታቸውን ያረጋግጣል፡፡

48. <u>የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም፣ የህክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሰራር፣ የኃይጅን፣ የአካባቢ ጤናን እና የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት የቁጥጥር ደረጃዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
2. ለጤና ተቋማት፣ የመድኃኒት አከፋፋዮችና ማከማቻዎች፣ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤
3. ለጤና ነክ ተቋማት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ የንጽህናና የጤና ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
4. የህጻናት ማቆያዎችን የሙያ ደረጃ ፈቃድ ይሰጣል፣ የንጽህና፣ የጤንነትና ተስማሚነት ደረጃዎችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
5. የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
6. በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ ሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎች በመውሰድ ምንነታቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ እርምጃ ይወስዳል፤
7. አግባብ ባለው ህግ መሰረት የባህል መድሀኒት አዋቂዎች በባህል ህክምና ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፤ የባህል መድሀኒቱ ምን አይነት ይዘት እንዳለው በላብራቶሪ እንዲመረመር ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤
8. በደረጃው የተፈቀደለት የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል ይሰርዛል፤ የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና ጎን ተጠናክሮ የሚሄድበትን ሥልት ይቀይሳል፤
9. በባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ላይ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎች በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤
10. ሕገወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችና፣ የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
11. አስተዳደሩ በሚቆጣጠራቸው የጤና ተቋማት አበረታች መድሀኒቶች፣ የናርኮቲክ መድኃኒት፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች እና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣ አጠቃቀምን፣ መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሲሆን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤
12. በከተማው አስተዳደር ሥር ያሉ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

13. የስነምግባር ግድፈት በሚያሳዩ የጤና ባለሙያዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤
14. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ ያደራጃል፤ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ያስከፍላል፤
15. የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ጥሰት እና የህክምና ስህተት በመፈጸሙ አቤቱታ ወይም ጥቆማ ሲቀርብ ይመረምራል፤ እንደአግባብነቱ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
16. የጤና ሙያ ሥነ ምግባር ኮሚቴ አሰራርና አደረጃጀት ደንብ አዘጋጅቶ ለከንቲባ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

49. <u>የአሽከርካሪና ተሽካርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፤ የስም ዝውውር፣ እዳ እና እገዳ አገልግሎት ይሰጣል፤
2. የተሽከርካሪ አመታዊ ምርመራ በራሱ ወይም በህግ አግባብ ውክልና በሰጠው አካል ያከናውናል፤ ምርመራውን ያላለፉ ወይም በወቅቱ ያልተመረመሩ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እንዳይሰጡ ያደርጋል፤
3. አግባብ ባለው ህግ መሰረት የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ምትክ ይሰጣል፤ ህጋዊነቱን ያረጋግጣል፤
4. የተሽከርካሪ ስታንዳርዳይዜሽን፣ ምዝገባና ስረዛ፤ የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት ይሰጣል፤
5. የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የማሽከርከር ስልጠና የሚሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሥራ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ አግባብነት የሌለው ተግባር ሲፈጽሙ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤
6. በተሽከርካሪ ምርመራ አገልግሎት፣ በአሽከርካሪ ማሰልጠኛ፤ በጋራዥ፣ በጎሚስታ እና መሰል አገልግሎቶች ላይ ለሚሰማሩ ተቋማትና ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
7. የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ መረጃዎችን በተመራጭ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
8. ከአሽከርካሪና ከተሽከርካሪ ጋር ተያይዞ ያሉ አገልግሎቶችን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 50. የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ይሰራል፤ ደንብ መተላለፍ እንዲቀንስ ያደርጋል፤
2. ስለደንብ መተላለፍ የወጡ ሕጎች፣ ስለሚደረጉ ቁጥጥሮች እና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤
3. ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ሕገወጥ ግንባታን፣ በሕገ-ወጥ መንገድ መሬት መያዝን፣ መሬት መውረርን እና ሕገ-ወጥ የመሬት ይዞታ ማስፋፋት ተግባርን ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
4. ሕገወጥ የመንገድ ላይ ንግድ፣ የእንስሳትና የስጋ ዝውውር፣ ዕርድ፣ ሽያጭ እና ተያያዥ የሆኑ የደንብ መተላለፍ ተግባራትን ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
5. በክፍት እና ዝግ የመናፈሻ ቦታዎች፣ የመንገድ አካፋዮች፣ ዳርቻዎችና አደባባዮች የሚከናወኑ ሕገወጥ ተግባራትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
6. የትራፊክ እንቅስቃሴ እና ደህንነትን የሚያውኩ እና የሚጋርዱ በመንገድ ወይም በትራፊክ መብራት ላይ የሚከናወን ልመናን፣ በመንገድ ላይ የንግድ ዕቃዎችን ማስቀመጥ፣ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
7. በመንገድ ላይ ዛፍ ወይም አትክልት መትከል፣ ያለፈቃድ ድንኳን መጣል፣ ብየዳ ማድረግ፣ የተበላሸን ተሽከርካሪ ማቆም፣ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ መጠገን ወይም ማስጠገን፣ማጠብ ወይምማሳጠብን እንዲሁም ሌላ ማንኛውም የትራፊክ እንቅስቃሴን የሚያውክ ወይም ለአደጋ የሚያጋልጥ ተግባርን ከሚመለከታው አካል ጋር በቅንጅት ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
8. መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር፣ መቀየስ፣ በበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር መቁረጥን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
9. በመንገድ መብራት ምሰሶ፣ በድልድይ፣ በመንገድ ምልክት እና በእግረኛ የመንገድ መከላከያ አጥር ላይ ባነር፣ ማስታወቂያ እንዲሁም በሕገወጥ መንገድ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፍ ወይም መትከልን ወይም ማንጠልጠልን ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

10. በሕገ-ወጥ መንገድ ፈሳሽ እና የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽን ከጎርፍ ማስወገጃ መስመር ጋር ማገናኘትና መልቀቅ፣ ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ ማስወገድ፣ የማንሆሎችን ክዳን መክፈት፣ ፉካዎችን እና የጎርፍ ማስወገጃ መስመርን መድፈን ወይም ጉዳት ማድረስን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

11. በትምህርት ተቋማት ዙሪያ ፊልም ወይም ቪዲዮ ቤት፣ ጭፈራ ቤት፣ መጠጥ ቤት፣ ቁማር ቤት መክፈትን፣ ጫት ማስቃምን ወይም ሺሻ ማስጨስን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

12. በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ህብረተሰቡን የሚያውኩ ተግባራትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

13. አግባብ ባለው ህግ መሰረት በገንዘብ የሚያስቀጡ የደንብ መተላለፍ ተግባራትን የቅጣት ገንዘብ ይሰበስባል፣ ህገወጥ ድርጊት የተፈጸመባቸዉን ንብረቶች ይወርሳል፣ በህጋዊ መንገድ ይሸጣል ወይም መወገድ ያለባቸውን ያስወግዳል፤

14. ከተልዕኮው አንፃር በደንብ መጣስ ተግባሮች ላይ ቅድመ ጥናት ያደርጋል፣ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ይፈፅማል፤

15. በዚህ አንቀጽ ከተደነገጉት በተጨማሪ ሌሎች በሕግ የተደነገጉ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶችን ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

16. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመከላከልና የቁጥጥር ኦፊሰሩን፣ ባለሙያዉን፣ አመራሩን ከማዕከል እስከ ወረዳ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት በመመደብ ወይም በማዘዋወር ሊያሰራ ይችላል፤

17. የባለሥልጣኑን የፓራ ሚሊተሪ ሠራተኞች ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡፡

51. <u>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአካባቢ ጥበቃ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ አካባቢ እንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣ አግባብ ያላቸውን አካላት ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያስተባብራል፤
2. የአካባቢ ጥበቃ፣ የተፈጥሮ ሀብትና የዘለቄታ አጠቃቀም እንዲኖርና እንዳይባክን ተገቢ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ስለ አካባቢ ጥበቃ በተለያዩ መድረኮች፣ አደረጃጀቶች እና በመገናኛ ብዙሃን ትምህርት ይሰጣል፤
3. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ልማትን ተግባራዊ እንዲሆን ያስተባብራል፤

4. ከኢንዱስትሪ ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ ዝቃጭ፣ ተረፈ ምርት፣ ቆሻሻ በሕግ መሠረት መወገዱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
5. ታዳሽና አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች እና ቴክኖሎጂዎችን ያፈላልጋል፣ ያሻሽላል፤ ያሰርጻል፤ ያስፋፋል፤
6. ከተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ የአየር፣ የድምጽ እና የፍሳሽ ብክለትን በህግ መሰረት ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
7. የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ሌሎች አካባቢ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አካላት የብክለት መከላከል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
8. የከተማው የካባና ሌሎች ተቆፋሪ ማዕድናት ሥፍራዎች ያላቸውን የማዕድን ክምችት መጠን ይለያል፤ ለልማት ያዘጋጃል፤ ከአደጋ ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል፤
9. የካባ ማምረት ሥራ ለሚያካሂዱ ፈቃድ ይሰጣል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤
10. የተለያዩ ማዕድናት ቁፋሮ የተካሄደባቸውን ቦታዎች መልሰው የሚለሙበት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
11. የተለያዩ ዕፅዋት የሚተከሉበትን ቦታና የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ለመናፈሻ፣ ለደን፣ ለወንዝ ዳርቻና ለሌላ አረንጓዴ ቦታ ልማት በተከለሉ ቦታዎች ላይ የሚተከሉትን ዕፅዋት አይነት በሚመለከት ያማክራል፤ ያስተዋውቃል፤
12. ልተሞከሩና የማይታወቁ ከአካባቢ ጋር ተስማሚና ጠቃሚ የሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች በከተማው ማልማት ለሚፈልጉ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፤
13. .በመንግስትም ሆነ በግል የይዞታ ክልል የለሙ ዛፎችን ለመቁረጥ ሲፈለግ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከባለስልጣኑ ዕውቅናና ፈቃድ ውጭ እንዳይቆረጡ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
14. በአስተዳደሩ ይዞታ ስር የሚገኙ ጥብቅ የደን ቦታዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የጋራ መገልገያ አረንጓዴ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
15. በተፋሰስና በአረንጓዴ አካባቢዎች ልማትና አገልግሎት ዘርፎች መሠማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ነዋሪዎች ወይም ሌሎች አካላት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
16. ዓላማውን ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 52. የመንገዶች ባለስልጣን

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመንገድ ኔትዎርክን፣ የመንገድ ሥራን፣ የመንገዶችን አጠባበቅና አጠቃቀም ህግ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የመንገድና ድልድይ ዲዛይን ደረጃ ያወጣል፤ ያሻሽላል፤ የጥገና ስታንዳርድ ያወጣል፤ የመንገድ ደረጃ አመዳደብ መመሪያ ያወጣል፤ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
3. የመንገድና ድልድይ ዲዛይን ከመጽደቁ በፊት በትራንስፖርት ቢሮ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋል፤
4. የመንገድ እና የድልድይ ዲዛይን፣ ግንባታ፣ ጥገና ሥራዎችን በራስ አቅም ያከናውናል፤ እንዲከናወን ያደርጋል፤
5. ለመንገድ ሥራ የአዋጭነት ጥናት፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ፣ የመንገድ ዲዛይን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
6. ለመንገድ ሥራው የሚያስፈልገውን ቦታ አግባብ ባለው ህግ መሰረት እንዲለቀቅ ያደርጋል፤
7. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የመንገድ ዲዛይን የሚሰሩ፣ የግንባታ ቁጥጥርና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አማካሪዎችን፣ በመንገድ ግንባታዎች ላይ የሚሰማሩ ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን ዘዴ ይወስናል፤
8. ግንባታቸው የተጠናቀቀ መንገዶችና ሥራዎች በውሉ መሠረት በተፈለገው ጥራትና ደረጃ መከናወናቸውን በማረጋገጥ ይረከባል፤
9. የመንገድ ፕላን መሰረት አዲስ ለሚገነቡ ለእግረኛ መተላለፊያ መንገድ የሚያስፈልገውን የመሬት ስፋትና አሰራር፤ የመንገድ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎችን ክብደት፣ ዓይነት ወሰን፤ ለተለያዩ የመንገድ ተጠቃሚዎች የሚውሉ መንገዶችን ለይቶ ይወሰናል፤ የመንገድ ምልክቶችን ይተክላል፤
10. በዋና መንገዶች እና በመለስተኛ ዋና መንገዶች ግራ እና ቀኝ ዳርቻዎች፣ አካፋዮችና አደባባይ ላይ የአረንጓዴ ልማት ስፍራዎች ዲዛይን የመንገድ ግንባታ ፕላን አካል አድርጎ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ መትከያ ስፍራዎችን ዝግጁ ያደርጋል፤ የሚተከሉ የዛፍ ዓይነቶችና መጠን ይወሰናል፤ አግባብ ላለው አካል መረጃ ይሰጣል፤
11. የአካባቢውን የውሃ ፍሰት መጠን ያገናዘበ የመንገዶችን ፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓት ይገነባል፤ ያስገነባል፤ ይጠግናል፤ ያሻሽላል፤
12. መንገዶችን የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎቹን ጨምሮ ከደለል፣ ከሌላ ጉዳትና አለአግባብ ከመጠቀም ይጠብቃል፤ በመንገዶች ላይ የሚከሰቱ መሰናክሎችን ያስወግዳል፤ ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፤ በተገቢው መንገድ ያስተዳድራል፤

13. በመንገድ ላይ ለሚከናወኑ የተለያዩ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ቁፋሮዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፈቃድ ይሰጣል፤

14. በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ማናቸውንም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም በመንገድ ላይ የግንባታ ግብዓት ተረፈ ምርት የሚጥሉ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎችን ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

15. በህብረተሰቡ፣ በቡድን፣ በግል ወይም በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት ለሚሰሩ መንገዶች ስታንዳርድ ያወጣል፤ ፈቃድ ይሠጣል፤ ይቆጣጠራል፤ እንዳስፈላጊነቱም በሚወጣው መመሪያ መሠረት ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

16. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በኮብልሰቶን መሰራት የሚገባቸውን መንገዶች ይለያል፤ በዕቅድ ውስጥ ያካትታል፤ የኮብል ስቶን የሚጠርቡ ማህበራትን የአቅም ክፍተት በመለየት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

17. የመንገድ ላብራቶሪ ምርመራና ፍተሻ ሥራዎችን ያከናውናል፤ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

18. መንገዶችንና ድልድዮችን ይመዘግባል፣ መረጃ ይይዛል፤ መንገዶች አግባብ ባለው አካል እንዲሰየሙ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ይተገብራል፤

19. የመንገድ አካፋዮችና ዳርቻዎች፣ የመከለያ አጥሮች ደረጃ እና ዲዛይን ያዘጋጃል፤

20. ለጎርፍ የተጋለጡ የከተማ ክፍሎችን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ጥናት ያደርጋል፤ የመከላከያ ሥራ መሥራት የሚያስችል ዲዛይን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በህግ አግባብ ከሥራ ተቋራጮች እና ከአማካሪዎች ጋር ውል በመዋዋል ግንባታው እንዲከናወን ያደርጋል፤

21. በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሰረት ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፡፡

## 53. <u>የውሃና ፍሳሽ ባለሰልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ማስወገድ ፍላጎት ያጠናል፤ የውሃ አቅርቦት እና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ማስተር ፕላን፣ የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2. የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ማስወገድ ፍላጎትን የሚያሟሉ ፕሮጀክቶችን ይነድፋል፤ ፕሮጀክቶች በወጣላቸው ስታንዳርድ፣ ዕቅድና የውል ስምምነት መሠረት ተጠናቀው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

3. የውሃ መገኛ፣ የውሃ ማጣሪያ ጣቢያዎች፣ የማሰባሰቢያና መስመር ዝርጋታ ጥናቶችን ያካሂዳል፤
4. የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መሰረተ ልማት ዲዛይን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በተዘጋጁ ዲዛይኖች መሰረት አግባብ ባለው ህግ ያስገነባል፤ ያስተዳድራል፤
5. የአገልግሎት ክልል በሚመለከት አግባብ ካለው ክልላዊ መንግስት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ የውሃ መሰብሰቢያ ስፍራዎችን ይለያል፤ ስምምነት ላይ ሲደረስ ሥራ ላይ ያውላል፤
6. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ለውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ልማት ለሚለቀቅ ንብረት ተገቢውን ካሳ ይከፍላል፤ ይይዛል፤ ያስተዳድራል፤
7. የውሀ ምንጭ ሀብት ግድብ፣ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ምንጭ፣ የግድብ ተፋሰስ ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤
8. ባለስልጣኑ አጣርቶ የሚያቀርበውን ውሃ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አጠቃቀሙን ሊወስን ወይም ሊገድብ ይችላል፤
9. የውሃ ማጣራት፤ ማከፋፈል፤ መሸጥ፣ የፍሳሽ መስመር መዘርጋት፣ መስመር የማስቀጠያና የመገልገያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
10. የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎችን፤ የቅብብሎሽ ጣቢያዎችን ይገነባል፤ ያስገነባል፤ ያስተዳድራል
11. ለውሃው አቅርቦት እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ልማት ሥራ ማስፈጸሚያ የሚውል ገንዘብ ከተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ያፈላልጋል፤ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
12. ለውሃ ስርጭት እገዛ የሚያደርጉ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራዎችን ያከናውናል፤
13. በግል የውሃና ፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ሥራዎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሙያዎችና ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ የአጭር ጊዜ ስልጠናና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይቆጣጠራል፤
14. የፍሳሽ ቆሻሻን በተሽከርካሪ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ እና በማስወገድ ተግባር ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶች አግባብ ባለው ህግ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤
15. የባዮጋዝና የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረቻ ቦታዎችን ያዘጋጃል፤ ያመርታል፤ ያስተዳድራል፤
16. የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ማከናወን ለሚፈልጉ አካላት የቁፋሮ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይቆጣጠራል፤
17. የውሃ መስመሮችን እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮችን በየወቅቱ ያድሳል፤ በሚበላሹበትም ወቅት አስፈላጊውን ጥገና ያከናወናል፤ የውሀ ስርጭትን ያከናውናል፤

18. ውሃን ከምርት ጀምሮ ተጠቃሚው ጋር እስኪደርስ ድረስ ባሉ ሂደቶች የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ መጠበቁን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ፍሳሾች በተዘረጋ የፍሳሽ መስመርና በተሽከርካሪ ያስወግዳል፣

19. ፍሳሽን ያጣራል፣ የተጣራ የፍሳሽ ውሃንና ዝቃጩን መልሶ በመጠቀም በልዩ ልዩ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

20. የውሃ ቆጣሪ የማስመጣት ብቸኛና ልዩ ስልጣን ይኖረዋል፣ የቆጣሪና የላብራቶሪ ምርመራ ያካሂዳል፣ በምርመራው ውጤት መነሻነት ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣

21. ውሃና ፍሳሽን በተመለከተ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፣ ህብረተሰቡን በተለያየ የውሃና ፍሳሽ ሥራዎች እንዲሳተፉ ያስተባብራል፣

22. በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሰረት ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡፡

54. <u>የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ለአገልግሎቱ ሥልጠት የሚያግዝ ስልት ይቀይሳል፣ ይተገብራል፣
2. የመንገድ ትራፊክን ማሳለጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣
3. የመንገድ ትራፊክ ፍሰቱን በማሳለጥ ደህንነቱ የተጠበቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል የትራፊክ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
4. የትራፊክ ፍሰትና ደህንነትን ለማሻሻልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የመረጃ ሥርዓቱን በመጠቀም የትራፊክ ደህንነቱንና ፍሰቱን ይከታተላል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀናጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ በግብዓትነት ይጠቀማል፣
5. በትራንስፖርት አገልግሎት እና በትራፊክ ሥርዓት ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል፣
6. የትራፊክ ምልክቶችና ማመላከቻዎች፣ የመንገድ ላይ ቅቦች፣ የትራፊክ መብራቶች እና ሌሎች የትራፊክ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ይተገብራል፣ ያስተዳድራል፣
7. ከመንገድ ትራፊክ እንቅስቃሴ አንፃር ሊገነቡ የሚገባቸውን መንገዶች ይለያል፣ የመንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ዲዛይን ሲሰራ ወይም ሲያሰራ ትራፊኩን ከማሳለጥ አኳያ አግባብነቱን ይገመግማል፣ ያረጋግጣል፣

8. የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የጭነት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሻ ፈቃድ ቁጥጥር፣ የሞተር ብስክሌት እና ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
9. መንገድ ለመዝጋትና ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ወይም ከታለመለት ዓላማ ውጪ ለመጠቀም ለሚቀርብ ጥያቄ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ የመንገድ ላይ ኩነቶችን ያስተዳድራል፤ ህግን በሚተላለፉ ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
10. የትራፊክ ደንቦች መከበራቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ አግባብ ባለው ህግ ደንብ ተላላፊዎች ላይ እርምጃ ይወስዳል፤ የማስፈፀሚያ ስልቶችን ይዘረጋል፤ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤
11. የትራፊክ ፍሰትና ደህንነት ችግር ያለባቸውን መንገዶች፣ መጋጠምያዎችና አደባባዮችን በመለየት የማሻሻያ ሥራ እንዲሰራ ያደርጋል፤
12. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ክፍያ ያጠናል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. የአሽከርካሪዎችን የርቀት እይታ የሚጋርድ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳርና የአደባባይ ዕጽዋት እንደአስፈላጊነቱ በከተማው ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ መወገዳቸውን ወይም መመልመላቸውን ያረጋግጣል፤
14. የሕዝብ የብዙኃን ትራንስፖርት፣ አንቡላንስና የእሳት አደጋ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችና የመሳሰሉት የመንገድ ቅድሚያና ያልተቋረጠ የትራፊክ አቅጣጫ የሚያገኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፤
15. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት አጥንቶ አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን ያቀርባል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር ይተገብራል፤ በመንግስት የለሙ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችን ያስተዳድራል፤ በግልም ሆነ በመንግስት የለሙ የፓርኪንግ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ህግን በሚተላለፉ ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
16. በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ የሚጣል ቅጣት አግባብ ባለው ህግ ይሰበስባል፤
17. የፓርኪንግ ቦታ ግንባታ ወይም አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ የመንግስትና የግል ተቋማትና ግለሰቦች ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤
18. የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከል ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፡፡

55. <u>የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን</u>

ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. በቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የሚቀርበው መረጃ መሠረት በማድረግ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ የፊሲካልና የፋይናንሻል ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ያዳብራል፤ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. ለጋራ መኖሪያ ቤት ልማት የሚያስፈልግ የለማ መሬት ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ይረከባል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፤
3. ለሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የአካባቢ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል እንዲሁም የፕላን ስምምነት፣ የግንባታ ፈቃድና ግንባታቸው ሲጠናቀቅ የህንጻ መጠቀሚያ ፍቃድ ጥያቄ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ፤
4. የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን የታይፖሎጂ ዲዛይንና ዝርዝር ዲዛይን፤ ስፔስፊኬሽን እና የሥራ ዝርዝር ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ የተዘጋጁ ዲዛይኖችን ከግንባታ ሳይቶች ያጣጥማል፣ እንዲጣጣም ያደርጋል፤
5. የቤት ግንባታውን ለማዘመን የሚያስችሉ በዲዛይን ፣ በግብዓት እና የግንባታ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ አማራጭ የቤት ልማት ቴክኖሎጂዎችን ያጠናል፣ ሲፈቀድም ይተገብራል፤እንዲተገበር ያደርጋል፤
6. እንደ አስፈላጊነቱ ሰፊ የቤቶች ግንባታ ለማካሄድ የሚያስችሉ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ የግንባታ ግብዓትን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችንና ተጓዳኝ አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማትን ቢሮው ሲፈቅድ ያደራጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣
7. ለግንባታ ሳይቶችና ግንባታቸው ለተጠናቀቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚያስፈልገውን የመሠረተ-ልማት አቅርቦት እንዲሟላ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ መሟላቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል፤
8. እንዳስፈላጊነቱ ግንባታቸው ለተጠናቀቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በሳይት ውስጥ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ያስገነባል፤
9. አግባብ ባለው ህግ መሠረት ዲዛይንና ግንባታ የሚያከናውኑ አማካሪዎችንና ሥራ ተቋራጮችን ይመዘግባል፤ ይመለምላል፣ ውሎችን ያዘጋጃል፤ ይዋዋላል፤ ውሉንም ያስተዳድራል፤
10. የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በተገባ ውል መሠረት የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል ፤ ይተገብራል፣

እንዲተገበር ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤ በሚታዩ ጉድለቶችና ጥፋቶች ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ግንባታቸው ሲጠናቀቅ ርክክብ ይፈጽማል፤

11. በመንግስትና የግል አጋርነት እና ሽርክና የቤት ልማት ፕሮግራም የቤት ግንባታ ውሎችን ይዋዋላል፣ ውል ያስተዳድራል፣ የፕሮጀክት አፈጻጸምና አመራር ይከታተላል፤

12. ለጋራ መኖሪያ ቤት ልማት የሚያስፈልገውን ገንዘብ በከተማ አስተዳደሩ ዋስትና ይበደራል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ እንዲሁም አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ በማፈላለግ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

13. በቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡና በባንክ የሚቆጥቡ ነዋሪዎችን የቁጠባ ገንዘብ መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ የብድር ወለድ ምጣኔውን በተመለከተ ከአበዳሪ ጋር ድርድር ያደርጋል፤

14. የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ ሲተላለፉ የተገኘውን ገቢ፣ የተመለሰውን የብድር መጠን እና ወለድ በአግባቡ ይመዘግባል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ የብድር ዕዳው እየተቀናነሰ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ወቅታዊና መሠረታዊ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤

15. ከቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የሚላክለትን የጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊ ተመዝጋቢዎች መረጃን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ይይዛል፤ ያደራጃል፣

16. የተገነቡ፣ የተላለፉና ያልተላለፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መረጃ ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው ያስተላልፋል፤

17. ለመተላለፍ ዝግጁ የሆኑ የጋራ መኖሪያና ንግድ ቤቶችን በመለየት የማስተላለፊያ ዋጋ ያጠናል፣ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያጸድቃል፣ በዕጣ ወይም በምደባ ያስተላልፋል ፤የንግድ ቤቶችን በጨረታ ይሸጣል፤ አስፈላጊ ሰነዶች ለቤቱ ባለመብቶች እና ለሚመለከተው አካል ያስረክባል፤

18. ያልተላለፉ የጋራ መኖሪያና ንግድ ቤቶችን እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ በህገ-ወጥ መንገድ ከያዙት አካላት ያስለቅቃል፣ በህግም ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

19. በልማት፣ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት ቤቶች በሚፈርሱበት ወቅት ከቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ተጣርቶና ተረጋግጦ በሚቀርብለት መረጃ መሠረት ምትክ የጋራ መኖሪያ ቤት ያመቻቻል፣ ይመድባል፤

20. የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለተጠቃሚዎች ሲተላለፉ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች ህግ ለሚፈቀድላቸው አካላት በህጉ መሰረት የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

21. በመንግሥት በጀት ለኪራይ አገልግሎት የሚውሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ያስገነባል፤ ግንባታቸው ሲጠናቀቅ ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ያስረክባል ፤

22. በቦንድ ብድር ወይም በሌሎች የፋይናንስ አማራጮች ቤቶችን በማስገንባት የሽያጭና የኪራይ ተመን በማስጸደቅ ይሸጣል፤ ያከራያል፤ ገቢውን ይሰበስባል፤ የተሰበሰበውን ገቢ በመልሶ ማልማት ወይም ለዕዳ ማቀናነሻ እንዲውል ያደርጋል፣ ማስያዥያ አድርጎ ብድር ይበደራል፤

23. በተላለፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሣይቶች ላይ በቤቶች ልማት በይዞታነት የተመዘገቡ ክፍት ቦታዎች እንዲለሙ ያደርጋል፣ በሚመለከታቸው አካላት እንዲጠበቁ ክትትል ያደርጋል፡፡

56. <u>የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመሬት ይዞታን በተመለከተ የመብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት መረጃ ምዝገባ፣ ስረዛ፣ እድሳት፣ ማስተካከያና ሌሎች የመሬት ይዞታ አገልግሎቶችን በአግባቡ መሰጠታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤
2. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ለተመዘገቡ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መሰጠቱን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤
3. በሥልታዊ ዘዴ ወይም በአልፎ አልፎ ዘዴ የመሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሥራዎች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤
4. ሀገራዊ ደረጃን መሰረት ያደረገ የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፣
5. የመሰረታዊና የህጋዊ ካዳስተር ካርታ ያዘጋጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፤
6. የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃን በዲጂታል እና በወረቀት ይይዛል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ እንዲሁም መረጃውን ይጠቀማል፤ ጥሬና የተቀናጀ ወይም የተተነተነ መሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን ያሰራጫል፤
7. ወቅታዊ የከተማ መሬት፣ የፊዝካል መሠረተ ልማትና የማህበራዊ ተቋማት የስፓሻልና ስፓሻል ያልሆኑ መረጃዎችንና ጥናቶችን ከሚመለከታቸዉ ተቋማት ይሰበስባል፣ በጂ አይ ኤስና በካርቶግራፊ በማደራጀት ዳታ ባንክ ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፤
8. እንደአስፈላጊነቱ ከተማዋን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን እና ለተለያዩ ተቋማት የሚያገለግሉ የአየር ፎቶ፣ የሳተላይት ምስሎችና የራዳር ፎቶዎች የመሳሰሉ የሪሞት ሴንሲንግ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የግንባታዎች ፣ የመሬት አጠቃቀምና ሌሎች የከተማ ለውጦችን በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ውሳኔ እንዲሰጡበት ያስተላልፋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ጥሬ መረጃዎችን ለተለያዩ አካላት በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ይሰጣል፤

9. ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል ጋር በመሆን የከተማውን ህጋዊ ካዳስተር መረጃ ሥርዓት ላይ መደበኛ የሆነ የስጋት እና የደህንነት ቁጥጥር ያደርጋል፤
10. የህጋዊ ካዳስተር ቴክኖሎጂ ሥርዓትን እና የኔት ወርክ መሰረተ-ልማትን ያሻሽላል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤
11. በህግ መሰረት የሕጋዊ ካዳስተር መረጃን ለህዝብ ክፍት ያደርጋል፤
12. ተግባሩን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ውሳኔም ይሰጣል፤
13. በሰጠው የምዝገባ ማስረጃ ምክንያት በቅን ልቦና ጉዳት ለደረሰበት ሶስተኛ ወገን በፍርድ ቤት ተጠያቂ ሆኖ ሲገኝ ካሳ ክፍያ ይከፍላል፤ ለሚከፍለው ካሳ ክፍያ የሚውል የዋስትና ፈንድ በከተማው አስተዳድር እንዲቋቋም ክትትል ያደርጋል፤
14. የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ሀገራዊ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ያስተክላል፣ እንዲናበቡ እና እንዲዘምኑ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤
15. በሦስተኛ ደረጃ የሚተከል የመሬት የመቆጣጠሪያ ነጥቦችን የማብዛት ሥራ ይሰራል፤
16. መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀትና ለማሠራጨት እንዲሁም የአድራሻ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ ለማስተዳደር እና የቤት ቁጥር ለመስጠት የሚያገለግል የህግ ማዕቀፎችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ በሚመለከታቸዉ አካላት ያስጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤ እንዲተገበር ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣል፤
17. ለአድራሻ ሥርዓት የሚሆኑትን የመንገድ፣ የፓርሴልና የቤት ቁጥር በመስጠት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማደራጀት የአድራሻ ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ያዘመንናል፤ ያስተዳድራል፤
18. የመሬት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የአድራሻ ሥርዓትን በሚመለከት በፌደራልና በከተማው አስተዳደር የሚወጡ ህጎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
19. ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ሠራተኞችን ያስተዳድራል፡፡

57. <u>የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

1. የከተማዋን ሁለንተናዊ ጽዳት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ሥራዎችን ያከናውናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
2. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የከተማው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብ፣ አጓጓዝና አወጋገድ የህዝብ ጤናን በማይጎዳና የአካባቢ ብክለትን በማይፈጥር መንገድ ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ይዘረጋል፤ ይተገብራል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

3. በህብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከትና የባህሪይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ የትምህርትና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በየደረጃው ያከናውናል፤ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችንም ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያስተባብራል፤
4. የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ሥራዎችን ለመተግበር በከተማ ደረጃ የወጡና የፀደቁ ፖሊሲና ህጎች በየደረጃው እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
5. የጽዳት ማህበራት እና የግል የጽዳት ድርጅቶች በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ሥራዎች የሚሳተፉበትን አማራጮች በማጥናት እንዲተገበር ያደርጋል፤
6. ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ የሚቀንስበትንና የሚለይበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ የደረቅ ቆሻሻ የመልሶ መጠቀምና ማስወገድ ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
7. ለአገልግሎቱ የሚወጣው ወጪ በተገልጋዮች የሚሸፈንበትን የታሪፍና የክፍያ ሥርዓት አጥንቶ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. የግል ባለሀብቶችና የግል ጽዳት ድርጅቶች የሚያቀርቡትን የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ይገመግማል፤ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቅትና የሥራ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤
9. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ማዕከላትንና ስፍራዎችን ያስተዳድራል፤ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የማሻሻያ ሥራዎችን በማከናወን የማስወገጃ ቦታው በህዝብ ጤና እና በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማያስከትል መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
10. የመልሶ መጠቀሚያ ማዕከላትና የማስወገጃ ቦታ የደረቅ ቆሻሻ በክብደት ሚዛን የሚመዘንበትንና ትክክለኛ መጠኑ የሚታወቅበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ መረጃዎችን መዝገቦ ይይዛል፤ ያሰራጫል፤ እንዲሁም የከተማዋን የደረቅ ቆሻሻ አጠቃላይ ሁኔታ ከመረጃው ተነስቶ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን መረጃዎች በማደራጀት ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ ያቀርባል፤
11. የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማስቀመጫ ቦታዎችን በከተማው የተለያዩ አቅጣጫዎች በማጥናት እንዲገነቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
12. የመልሶ መጠቀምና የቀልዝ ወይም የብስባሽ ማዳበሪያ ማዕከላትን በማስፋፋት ደረቅ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን፣ ጠቃሚ ውጤት የሚያስገኝበትን የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች በማጥናት እንዲተገበሩ ያደርጋል፤ ውጤታቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
13. መልሶ መጠቀሚያ ማዕከላትና ማስወገጃ ቦታ የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ በማጥናት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ይተገብራል፤

14. የአዲስ ሳኒተሪ ላንድፊል እና ከቆሻሻ የኃይል ማመንጫ ቦታ መረጣ፣ የጥናትና የማልማት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
15. የደረቅ ቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎችን እንዲሁም ማሽነሪዎችን ያሰማራል፣ ያስተዳድራል፤
16. ዓላማውን ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 58. <u>የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በከተማ አስተዳደሩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይመዘግባል፤ መመዝገቡን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤
2. የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች የነዋሪዎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
3. የክብር መዝገቦች ዝግጅትና ስርጭትን፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓት አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር ይሰራል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ የክብር መዝገቦች ለሁሉም የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ጽህፈት ቤቶች መሰራጨታቸውን ያረጋግጣል፤
4. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አስፈላጊነትን አስመልክቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ ይፈጥራል ወይም እንዲፈጠር ያደርጋል፤
5. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የጥራትና የሽፋን ደረጃ ለመገምገምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ መሠረት የተሰበሰቡ መረጃዎችን አግባብ ላለው የፌደራል አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤
7. በቴክኖሎጂ በመታገዝ የዲሞግራፊ እና የባዮሜትሪክ የሰዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ አገልግሎት ይሰጣል፣ ያስተዳድራል ፣ ይቆጣጠራል፤
8. መንግስታዊ ተቋማት፣ ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚደረገው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት የተሟላ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፤
9. የዲጂታል አገልግሎትን በከተማዋ ለማሳለጥ የግለሰብ የመረጃ መብትን በጠበቀ መልኩ የተመዝጋቢዎችን መረጃ እንደ አስፈላጊነቱ ለተቋማት ያጋራል ደህንነቱን ያስጠብቃል፤ ይቆጣጠራል፡፡

59. <u>የምገባ ኤጀንሲ፤</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የተማሪዎች ምገባ፣ የመማሪያ ቁሳቁስ እና የትምህርት መርጃ መሳሪያ ድጋፍ ማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ይዘረጋል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፤
2. በቅድመ መደበኛ፣ በመጀመሪያ ደረጃ እና እንደአስፈሊጊነቱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የምገባ ተግባር መከናወኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
3. የተማሪዎች ምገባ፣ መማሪያ ቁሳቁስ፣ ትምህርት መርጃ መሳሪያ እና ደንብ ልብስ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶችና የተማሪዎች መረጃ ከትምህርት ቢሮ ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
4. በመንግስት ትምህርት ቤት የሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ግብዓት፣ ለተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ እና የተማሪ ደንብ ልብስ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
5. በተማሪዎች ምገባ፣ መማሪያ ቁሳቁስ፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያ እና በተማሪ ዩኒፎርም ደንብ ልብስ ድጋፍ በሚመለከት ከተማሪ ወላጆች፣ ከመንግስታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤
6. የከፋ የምግብ ችግር ያለባቸው ህጻናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የአዕምሮ ህመምተኞች እና መሰል የህብረተሰብ ክፍሎች ምገባ ማከናወን የሚያስችል ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይተገብራል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፤
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተጠቀሱ የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ ከሴቶች፣ ሕጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ይሰበስባል፤ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (6) ለተጠቀሱ የህብረተሰብ ክፍሎች የምግብ፣ የገንዘብ እና ሌሎች ግብዓቶችን የሚደግፉ አካላትን ይለያል፤ ድጋፍ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ድጋፍ የሚያደርጉ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ያበረታታል፤ ዕውቅና ይሰጣል፤
9. የምገባ ኘሮግራሙ ከሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራም ጋር በማቀናጀት እንዲፈፀም ያደርጋል፣
10. የምገባ ፕሮግራሞች በተጠቃሚዎች ጤንነት፣ ንጽህና ጥበቃና የሥርዓተ ምግብ መሻሻል ላይ ያተኮረ መሆኑን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤

11. የምገባ ተጠቃሚዎች ያሉባቸው ማህበራዊ ችግሮች እንዲፈቱላቸውና ከድጋፉ እንዲወጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
12. የምግብ ማዘጋጃ እና መመገቢያ ህንጻ ያስገነባል፣ ተገቢውን ግልጋሎት እየሰጠ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
13. ከተልዕኮው አኳያ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ጥናቱ በጥቅም ላይ እንዲውል ይከታተላል፤
14. የምገባ ማዕከላትን በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

60. <u>**የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ**</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ማምረቻ፣ ማሳያ፣ መሸጫ ሼድና ህንጻ መገንባት እንዲችል ከሚመለከተዉ አካል የለማ መሬት ይረከባል፤ እንዲሁም ካርታ የሌላቸው ነባር ይዞታዎች እና አዲስ የሚሰጡ ቦታዎችን ካርታ እንዲሰራላቸው ያደርጋል፤
2. ለአዳዲስ የመስሪያ ቦታ ግንባታ አዳዲስ የዲዛይን ሥራዎች እንዲከናወኑ ዲዛይን ከሚያዘጋጀው አካል ጋር በጋራ የዲዛይን ሥራ እንዲሰራ ያደርጋል፤
3. ለኢንተርፕራይዝእና ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚውል የመሥሪያ ቦታ ከሥራና ክህሎት ቢሮ እና ከኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ፍላጎት ይቀበላል፤ ይደለድላል፤ በከንቲባው ያስጸድቃል፤
4. ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙባቸውን የማምረቻ፣ ማሳያ፣ መሸጫ ሼዶች፣ ህንፃዎች በኢንዱስትሪ መንደሮች፣ በክላስተር ማዕከላትና በገበያ ማዕከላት በማደራጀት ያስገነባል የመሠረተ ልማት አውታሮችም እንዲሟላላቸው ያደርጋል፣
5. ቀድመው የተገነቡትንም ሆነ አዲስ ለሚገነቡ የመስሪያ ቦታ ማዕከላትን ስታንዳርድ ያወጣል፣ ሲፀድቅ ይተገብራል፣ ይቆጣጠራል፤
6. የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚዎች ለሆኑ ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ ማሳያ፣ እና መሸጫ ቦታ በውል ያስተላልፋል፣ የመጠቀሚያ ኪራይ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤
7. በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ለኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ወይም የሚዘጋጁ የመስሪያ ቦታዎችን ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤
8. የመስሪያ ቦታ አሰጣጥ እና ማስተላለፍ የአሰራር ሥርዓት ጥናት ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. ዕድሳት እና ጥገና የሚያስፈልጋቸው መስሪያ ቦታዎችን በጥናት በመለየት የእድሳት እና የጥገና ሥራ ያከናውናል፤

10. በህገ-ወጥ መንገድ የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ማዕከላት ተላልፈው ሲገኙ የተላለፈላቸውንም ሆነ የሚያስተላልፉ አካላት ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
11. የመስሪያ ቦታዎች ሲተላለፉ ተጠቃሚዎች ከተዋዋሉበት የሥራ ዘርፍ አላማና ተግባር ውጪ እንዳያውሉ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አውለው ሲገኙም የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፤
12. በመስሪያ ቦታ ልማትና አስተዳደር ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፤ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ውጤቱንም ተግባር ላይ ያውላል፤
13. የክላስተር ማዕከላት ልማት ከኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ እና ወቅታዊ መሆኑን በየጊዜው ያረጋግጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በመፈተሽ እንዲስተካከል የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ተግባር ላይ ያውላል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡
14. በመስሪያ ቦታ ውስጥ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች በመስሪያ ቦታ ልማትና አስተዳደር ተግባራት ላይ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ያደራጃል፤
15. ለሚያደራጃቸው ኮሚቴዎች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤ የአፈጻጸም ማኑዋል ያዘጋጃል፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን በማሳወቅ ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ደደርጋል፣
16. በግል፣ በመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ለኢንተርፕራይዞችና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታዎች እንዲገነቡ ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤
17. ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታዎችን ችግሮች በጥናት በመለየት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ለይቶ ያጠናል፣ ይቀምራል፣ ይተገብራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤
18. ነባርመስሪያ ቦታዎችን እና አዲስ የሚገነቡ መስሪያ ቦታዎችን በክላስተር ጽንሰ ሀሳብ መሰረት ያደራጃል፣ ተግባር ላይ ያውላል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
19. በመስሪያ ቦታ ማስተላፍና አስተዳደር ዙሪያ የሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎችን ምለሽ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤
20. ክፍትና አዲስ የተገነቡ የመስሪያ ቦታዎችን መረጃ በየጊዜው በማጣራት ለከንቲባው ያሳውቃል፤
21. ለመካከለኛና ለከፍተኛ ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በስታንዳርድ መሠረት ያስገነባል፤ አስተዳደራዊ ሥራውን በተመለከተ የአሰራር ሥርዓት ያጠናል ወይም ያስጠናል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

61. <u>የመንግስት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት</u>

አገልግሎቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ዝርዝራቸው በአግልግሎቱ መመሪያ የሚወሰኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶችና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተገለፀው ቢኖርም በመንግስት ለሚከናወኑ የግንባታ ሥራዎች ግዥ ግንባታውን እንዲያስፈፅም ስልጣን በተሰጠው አካል ተፈፃሚ ይሆናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ሲያውል፡-
   ሀ) የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገዱ ተግባር አግባብ ባለው ህግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
   ለ) ግዥ የተፈጸመላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንዲያውቁት ያደርጋል፤
   ሐ) የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ግዥ፤ ከተማዊ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚ እንዲደርስ ያደርጋል፤
   መ) ልዩ ሙያዊ እውቀት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው መንግስታዊ ተቋማት ሙያዊ ተግባር በመጠየቅ ይተገብራል፡፡
4. ግምታቸው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ በከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት ስር ያሉ ንብረቶች እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፤
5. ለመንግስት የልማት ድርጅቶችና ለግሉ ዘርፍ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
6. ለከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ግዥን በተመለከተ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

62. <u>የማህበራዊ ትረስት ፈንድ</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበራዊ ትረስት ፈንድ በተቋቋመበት ሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ሥራውን ይቀጥላል፡፡

63. <u>ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል</u>

ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል በተቋቋመበት ሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ሥራውን ይቀጥላል፡፡

64. <u>የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ</u>

አካዳሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማው እና የሃገሪቱን የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ የአካዳሚውን የትምህርትና ስልጠና መርሀ-ግብር ይቀርፃል፤ ሞጁሎች ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያዉላል፤
2. የከተማው አስተዳደር አመራርና ባለሙያ የትምህርትና ስልጠና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤
3. የተቋማትን፣ የአመራርንና የባለሙያን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሚረዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሰራል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. ቤተ መፃህፍትን በማደራጀት የትምህርትና ስልጠና ሂደቱን ይደግፋል፤ ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎችን ያደራጃል፤
5. ለስልጠናው አግባብነት ያላቸው የስልጠና አሰጣጥ፣ የምዘናና ግምገማ ሥርዓቶችን ይነድፋል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. ከመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ወይም የግል ድርጅቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ለአመራርና ባለሙያ የሥልጠና፣ የምክርና የማህበረሰብ አገልግሎት ይሰጣል፤
7. ሰልጣኞች ስልጠናቸውን ሲጨርሱ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የስልጠና ዉጤታማነት ጥናት ያካሂዳል፣ ለሚመለከተዉ አካልም ሪፖርት ያቀርባል፣ ከጥናቱ በመነሳት የተሻሉ የአሰራር ስልቶችን ይቀይሳል፤
8. ቦርዱ በሚያፀድቀው የምልመላ መስፈርት መሰረት ሰልጣኞችን ይቀበላል፤ የዕለት ተዕለት ግንባታቸውን በመመዝገብ ይከታተላል፤
9. በቦርዱ ሲፈቀድለት የከተማ አስተዳደሩን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የሚፈታ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም ያሳትማል፣ ያሰራጫል በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
10. የአካዳሚውን የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ ለማሻሻል የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

11. የተለያዩ ትምህርታዊ ሴሚናሮችን፣ ወርክ ሾፖችን፣ ኮንፈረንሶችንና አውደ ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል፤ ጥሪ ሲደረግለትም ይካፈላል፤
12. ከሌሎች አቻ ተቋማት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸዉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር ግንኙነትና ትብብር ይፈጥራል፣ ምርጥ ተሞክሮ ይለዋወጣል፤ ከነዚህ አካላት ጋር በመተባበር ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤
13. የሥራ አመራር ሥልጠና፣ የምክር አገልገሎትና የጥናት ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ገቢ የሚያገኝባቸዉን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ ለሚሰጠዉ ትምህርትና ስልጠና አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፡፡ የአገልግሎት ክፍያው ቦርዱ በሚያፀድቀው መጠን መሰረት ይሆናል፤
14. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የበጀት ስርዓቱን በመጠበቅ በሚሰበስበው ገቢ ይጠቀማል፡፡

## 65. <u>የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽህፈት ቤት</u>

ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሆኖ እስኪቋቋም ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽህፈት ቤት በተቋቋመበት ህግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ሥራውን ይቀጥላል፡፡

## 66. <u>የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት</u>

ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ የትላልቅ ግንባታዎች ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ሆኖ እስኪቋቋም ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት በተቋቋመበት ህግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ሥራውን ይቀጥላል፡፡

## 67. <u>ስለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን አደረጃጀትና አሰራር በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 96/1996 መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 68. <u>ስለከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅቶች</u>

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅቶች በተቋቋሙበት ህግ መሰረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡-
   ሀ) የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት፤
   ለ) የቄራዎች ድርጅት፤
   ሐ) የኤግዚቢሽን ማዕከልና ገበያ ልማት ድርጅት፤
   መ) የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር፤
   ሠ) የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት፤
   ረ) የኮንስትራክሽን ዲዛይን፣ ግንባታና ማማከር ድርጅት፤
   ሰ) የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን፤

ሸ) አዲስ አበባ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት፣

ቀ) የቲያትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት፣

በ) የንግድ ሥራዎች ድርጅት፣

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የልማት ድርጅቶች ስምና አደረጃጀት ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ሊሻሻል ወይም ሊቀየር ይችላል፣

3. ልማት ድርጅቶቹ ቀጥተኛ የሥራ ግንኙነት ካላቸው የአስፈጻሚ አካላት ጋር የመንግሥት ፖሊሲ ዓላማን በሚያሳኩበት ሁኔታ በቅንጅት ይሰራሉ፡፡

69. <u>ስለከተማው አስተዳደር ጤና ተቋማት፣ ኮሌጆችና ማዕከላት</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚተዳደሩ የጤና ተቋማት፣ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ማዕከላት በየራሳቸው ህጎች መሰረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለ ክፍለ ከተማ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የክፍለ ከተሞች አከላለል፣ ወሰንና ተጠሪነት</u>

70. <u>የክፍለ ከተማ የአከላለል መሠረት</u>

የክፍለ ከተማ አከላለል የቆዳ ስፋትን፣ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥን፣ የነዋሪ ብዛትን፣ የልዩ ልዩ አገልግሎት ተደራሽነትና የሀብት ስርጭትንና የአስተዳደር አመችነትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

71. <u>ክፍለ ከተማ ወሰን</u>

የክፍለ ከተማ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ የአከላለል ካርታ ላይ ተለይቶ በተገለፀው መሠረት የተወሰነው ይሆናል፡፡

72. <u>የክፍለ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነት</u>

የክፍለ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነት ለክፍለ ከተማው ነዋሪውና ለከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለክፍል ክፍለ ከተማ አስፈጻሚ አካላት

### 73. የክፍለ ከተማ አደረጃጀት

የከተማውን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕጎች  በክፍለ ከተማው የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት፡-

1. ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣
2. ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣
3. የክፍለ ከተማ ካቢኔ፣
4. የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ፣
5. ሌሎች አስፈጻሚ አካላት፣

ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፣ ካቢኔ፣ ሥራ አስኪያጅ

### 74. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

በቻርተሩ አንቀጽ 34 እንደተደነገገው፡-

1. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከክፍለ ከተማ ምክር ቤት አባላት ውስጥ ይመረጣል፤ የሥራ ዘመኑም የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፤
2. የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤትና  ለከተማው ከንቲባ ሆኖ ክፍለ ከተማውን ይመራል፤
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የክፍለ ከተማ ካቢኔ አባላትን ከምክር ቤት አባላት ወይም የምክር ቤት አባላት ካልሆኑት መካከል መርጦ ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት በማቅረብ ሹመታቸውን ያፀድቃል፤
   ለ) የክፍለ ከተማው ዓመታዊ ዕቅድና የበጀት ድልድል ሃሳብ በክፍለ ከተማው ካቢኔ ከተመከረበት በኋላ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት ያቀርባል፣ የክፍለ ከተማውን  የገቢ ማሰባሰብ በበላይነት ይመራል፤
   ሐ) የክፍለ ከተማውን ካቢኔ ይሰበስባል፤
   መ) በክፍለ ከተማው ሕግና ሥርዓትን ያስከብራል፤ የክፍለ ከተማውን የፀጥታ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ከክፍለ ከተማው አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ ችግር ሲያጋጥም ለከተማው ከንቲባ ያሳውቃል፤

ሠ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት በክፍለ ከተማው ካቢኔ እንዲገመገም ያደርጋል፤ ውጤቱን ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና ለከተማው ካቢኔ ሪፖርት ያደርጋል፤

ረ) በብሔራዊና በሕዝብ በዓላት ሥነ-ሥርዓቶች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ክፍለ ከተማውን ይወክላል፤

ሰ) ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለከተማው ከንቲባና ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፤

ሸ) በክፍለ ከተማው ምክር ቤትና በከተማው ከንቲባ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 75. የክፍለ ከተማው ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ

ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የክፍለ ከተማው ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፡-

1. የክፍለ ከተማው ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከክፍለ ከተማው ምክር ቤት አባላት ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጪ ሊመረጥ ይችላል፤
2. የክፍለ ከተማ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፡፡
3. የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይራል፤
4. በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 76. ስለክፍለ ከተማ ካቢኔ ሥልጣንና ተግባር

በቻርተሩ አንቀጽ 36 እንደተደነገገው፡-

1. የክፍለ ከተማው ካቢኔ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና በጋራ ለሚወስነው ውሳኔም ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ይሆናል፤
2. የክፍለ ከተማው ካቢኔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በክፍለ ከተማው ዕቅድና የበጀት ድልድል ሃሳብ ላይ ይመክራል፤

ለ) በክፍለ ከተማው ውስጥ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የከተማው የበላይ አካላት ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) በክፍለ ከተማው ምክር ቤትና በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚሰጡት ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 77. ስለክፍለ ከተማ ካቢኔ አባላት

1. የክፍለ ከተማው ካቢኔ ተጠሪነት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና በጋራ ለሚወስነው ውሣኔ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት ሆኖ የክፍለ ከተማው ካቢኔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣
   ሀ) የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤
   ለ) የከተማ ካቢኔ አባልየሆነ አስፈጻሚ አካል በክፍለ ከተማ ደረጃ ከተደራጀ የክፍለ ከተማው ካቢኔ አባል ይሆናል፤
   ሐ) ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደአስፈላጊነቱ በክፍለ ከተማ ካቢኔ በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የክፍለ ከተማ ሌሎች ኃላፊዎች፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ተራ ፊደል (ለ) ሥር የተጠቀሰው አስፈጻሚ አካል ኃላፊ በክፍለ ከተማ ካቢኔ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ኃላፊ በተተኪ አባልነት በክፍለ ከተማ ካቢኔ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

## 78. ስለ ክፍለ ከተማ ካቤኔ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

የክፍለ ከተማው ካቢኔ የስብሳባ ሥነ-ሥርዓት ካቢኔው በሚያወጣው ውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 79. የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

በቻርተሩ አንቀጽ 37 እንደተደነገገው የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ፡-

1. ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
2. ዕቅድና በጀት ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤
3. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለከተማው ሥራ አስኪያጅና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል፤
4. በቻርተሩ የተሰጡትን ሌሎች ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 80. የክፍለ ከተማ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

ክፍለ ከተማው ከከተማው አግባብ ያለው አስፈጻሚ አካል ሥልጣንና ተግባር አኳያ በተዋረድ በተደራጀ ወይም በሚደራጅ አስፈጻሚ አካል የሥራ መስክ ተከፋፍሎ የሚከናወኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክፍለ ከተማው የሚገኙ ወረዳዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

2. የክፍለ ከተማውን አጠቃላይ ዕቅዶች፣ መርሐ-ግብሮችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፤ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤
3. ፖሊሲ፣ ሕግ፣ ደረጃና የአስተዳደሩ የበላይ አካላት ውሣኔዎች በክፍለ ከተማው ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
4. የክፍለ ከተማው ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን ያረጋግጣል፤
5. የተፈቀደለትን በጀት ይደለድላል፤ በሥራ ላይ ያውላል፤ አፈጻጸሙ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት መሆኑን ይከታተላል፤
6. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ግብር፤ ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤ የክፍለ ከተማው ገቢ የሚያድግበትን ሁኔታ ያጠናል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. የክፍለ ከተማው አስፈጻሚ አካላት ሥራን ይመራል፤ ያስተባብራል፤
8. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
9. የክፍለ ከተማውን የመንግሥት ሠራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤
10. በክፍለ ከተማው ውስጥ የሕዝብን ተሳትፎ ያሳድጋል፤ የብዙሃን ማህበራትን አቅም ይገነባል፤
11. አነስተኛ ነጋዴዎችን፤ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን፣ ሥራ ፈላጊዎችን እና ሌሎች አካላት በማህበር እንዲደራጁ ድጋፍ ይሰጣል፣ አሠራራቸውንም ይቆጣጠራል፤
12. የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ይተገብራል፡ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
13. የመንግስትና የግል የትምህርት ቤቶችን እና የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤
14. በክፍለ ከተማው የመንግሥት ፖሊሲና ሕጐች እንዲሁም የአስተዳደሩ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲተዋወቁ ያደርጋል፤
15. ታሪካዊ ቅርሶችን ይጠብቃል፤ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ሥነ-ጥበብ እንዲበለጽጉ ያደርጋል፤
16. የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ያስተዳድራል፤ ስፖርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያስፋፋል፤ ወጣቶች ተገቢውን ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
17. በልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል፤
18. የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በደማቸው ውስጥ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያለባቸው ሰዎች የእኩል እድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

19. ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ተግባራዊ ያደርጋል፤ የበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን ያከናውናል፤ በክፍለ ከተማው የሚገኙ የአስተዳደሩን ጤና ጣቢያዎችንና ክሊኒኮችን ያስተዳድራል፣ የግል ክሊኒኮችን ይቆጣጠራል፤ ኤች አይ. ቪ. ኤድስን ለመከላከል የሚንቀሳቀሱ ተቋማትን ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
20. የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ለነዋሪው እንዲዳረሱ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤ ተገቢውን ጥበቃና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የትራፊክ ደህንነትን ያስጠብቃል፤
21. ሕገ ወጥ ተግባራትን ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
22. ሕገወጥ ግንባታዎችን ይከላከላል፤ ያስወግዳል፤ በክፍለ ከተማው ባለቤትነት ሥር ያሉ ቤቶችን ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤
23. የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ ስልጠናዎች ይሰጣል፤ ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር ዕውቀትና ክህሎት እንዲቀስሙ ያደርጋል፤ ያበረታታል፤ የንግድ ሥራ ክህሎት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ያመቻቻል፤
24. የጥቃቅንና አነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሠጣል፤
25. የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩበትን የሥራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የሙያዊ ድጋፍና ክትትል፣ የብድር፣ የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎትና የገበያ ትስስር ያመቻቻል፣ የመስሪያና መሸጫ ቦታ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
26. ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ነባር የመስሪያ ቦታ የሆኑ ህንጻዎች፣ ሼዶች፣ ተለጣፊ ሱቆች እና ኮንቴነሮች እንዲሁም በመንግስት፣ በግልና በተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተገነቡ መደብሮችን ያስተዳድራል፤
27. በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ይሰጣል፣ የሙያ ምክር አገልግሎትን ያስፋፋል ፣ ክፍት የሥራ መደቦች ይመዘግባል፤ ሥራና ሠራተኛ ያገናኛል፤
28. የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ሌሎች አካባቢ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አካላትን ይቆጣጠራል፤ የአካባቢ ንጽህና እና ውበት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤
29. የመሬት ልማትና አስተዳደር በሚመለከት፡-
    ሀ) በህግ የሚቀመጠውን የአሰራር ስርአት ተከትሎ መብት ላልተፈጠረላቸው ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት በቋሚ መዝገብ በመመዝገብ

ለባለይዞታው ይሰጣል፤ ማህደራቸውን ያደራጃል፤ ከሕግ ውጪ የተሰጠ የቦታ ይዞታ ወይም የቤት ባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ያግዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ይሰርዛል፤

ለ) የቦታ ይዞታ እና/ወይም የቤት ባለቤትነት ማህደሮችን ያደራጃል፤ ይጠብቃል፣ የአዳዲስ ይዞታ ካርታ ኮፒዎችን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

ሐ) የይዞታ ሰነዶችን በማደራጀት ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸውን ተቀብሎ በወቅቱ በማስተካከል ያስረክባል፤

መ) መደበኛ የይዞታ አገልግሎቶችን (ይዞታ መክፈል፣ ይዞታ መቀላቀል፣ የነባር ይዞታዎች አገልግሎት ለውጥ፣ ካርታ ኮፒ፣ የስመ ንብረት ዝውውር፣ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ህጋዊነት ማረጋገጥ፣ ዋስትና ምዝገባ ስረዛ፣ዕግድ ምዝገባ ስረዛ፣ የይዞታ ማካተት፣ ወሰን ማመላከት፣ ልዩ ልዩ የይዞታ ማስረጃ መስጠት፣ ከካሳ ሥራዎች ውጪ ያሉ የህንፃ/የቤት ግምት) ያከናውናል፣ አፈጻጸሙንም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤ በሚሰጠው ግበረ-መልስ መሰረት አስፈላጊን ማስተካከያ ያደርጋል፣ የተሰጡ አገልግሎቶችን በሙሉ በመሰረታዊ ካርታ ያደራጃል፣ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

ሠ) የመልሶ ማልማት፣ የከተማ ንድፍ፣ አማራጭ የመሬት አቅርቦት፣ እና ሌሎች ጥናቶች ሲከናወኑ መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ህዝብ ያወያያል እንዲሁም ጥናቶቹ ሲፀድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) ለልማት በሚለቀቀው መሬት ላይ ላለው ንብረት በህግ መሠረት መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ካሳ ይተምናል፤ እንዲተመን ያደርጋል፤ የካሳ ክፍያ ይፈጽማል፤ ምትክ ቦታ ይወስናል፣ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅ ያስተላልፋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ካሣ ክፍያ የተፈፀመባቸውን ንብረቶች እንዲነሱ ያደርጋል፤

ሰ) ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት ዝርጋታ የሚውል መሬት ወሰን ያስከብራል፤ የቅየሳና የሽንሻኖ ሥራዎች ያከናውናል፤ ቦታዎቹን ለልማት ዝግጁ ያደርጋል፤ ለመሬት ዝግጅት የሚያስፈልግ በጀትና የአፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሸ) ለግንባታ ተረፈ ምርት መድፊያነት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን ከልሎ ያስተዳድራል፤ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት በተገቢው የተደፋ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ቀ) ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬት፣ በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን፣ ባንክ የተደረጉ ክፍት መሬቶችን ወይም

ይዞታዎችን ይመዘግባል፤ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል፤ የቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፤ ለህገወጥነት እንዳይጋለጡ ለደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ያስረክባል፤

በ) የለማ መሬትን በመመዝገብ ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር ይሰጣል፤ በጨረታ እና በምደባ የሚተላለፉ ቦታዎችን ይለያል፤ ቦታው ለተጠቃሚ እስከሚተላለፍ ድረስም የመከላከልና የመጠበቁን ሥራ ያከናውናል፤

ተ) በክፍለ ከተማው አስተዳደር ወሰን ውስጥ ያለውን የመሬት ሃብት እና የአሰራር ጥራት ኦዲት ያደርጋል፤ በኦዲት ግኝቱ መሠረት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ቸ) ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች በምደባ፣ በጨረታ፣ ለምትክ እና ለጊዜያዊ መጠቀሚያ የተላለፉ ቦታዎችን በመስክ በመገኘት ያስረክባል፣ የሊዝ ውል ያዋውላል፣ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት ይሰጣል፤

ኀ) ለልዩ ልዩ የግንባታ ሥራዎች ሊያገለግሉ የሚችሉ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች በመዋቅራዊ ፕላኑ መሠረት ከልሎ ይይዛል፤ ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሚሰጥ የማዕድን ማውጫ ፈቃድ መሠረት በጊዜያዊነት መሬቱን በሊዝ ሲተላለፍ ቦታውን ያስረክባል፤ የቦታዎቹ ጠቀሜታ ሲያበቃም ተከታትሎ በመረከብ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

ነ) አግባብ ባለው ህግ ለህጋዊ ባለይዞታዎች የዋጋ ለውጥ የሌለባቸውን የሊዝ ይዞታዎች የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

ኘ) በሊዝ ህግና ውል መሠረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፣ በሊዝ ውላቸው መሰረት ግንባታ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ አግባብ ባለው ሕግና በውሉ በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ ግንባታ ካልተጀመረ ወይም ካልተጠናቀቀ በሊዝ ህጉ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

81. <u>የክፍለ ከተማ አስፈጻሚ አካላት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪ የሆኑና የክፍለ ከተማው አስፈጻሚ አካለት ባልተማከለ መርህ መዋቅራዊ የሥራ ክፍፍል በሚወሰነው መሠረት የአስፈጻሚ አካላት ተዋረዳዊ አደረጃጀት አካል ሆነው ይደራጃሉ፤

2. የክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ወይም የሌላ አስፈጻሚ የሥራ ክፍል፡-

   ሀ) በከተማ ደረጃ ለከንቲባ ተጠሪ የሆነ አስፈጻሚ አካል በክፍለ ከተማ ከተደራጀ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል፤

ለ) በከተማ ደረጃ ለከተማ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆነ አስፈጻሚ አካል በክፍለ ከተማ ከተደራጀ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፤

ሐ) በከተማ ደረጃ የተደራጁ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት በክፍለ ከተማ ከተደራጁ ተጠሪነታቸው በከተማ ደረጃ ያለውን ተጠሪነት ሥርዓት ይከተላል፤

መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም የክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፤

3. በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለማስፈጸም በጸደቀ ወይም በሚጸድቅ መዋቅራዊ አደረጃጀት ተዋረዳዊ ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ) የእቅድና በጀት ዝግጅት፣ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ የሠራተኞች ውስጥ ዝውውርና የደረጃ ዕድገትን ጨምሮ ሌሎች ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በሥራው መስክ ለሚመለከተው ቢሮ ተጠሪ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ማዕከል ተከትሎ በሥሩ የሚደራጁትን ሌሎች ጽህፈት ቤቶች፣ ዳይሬክቶሬቶች ወይም የሥራ ክፍሎች በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤

ለ) እያንዳንዱ ጽሕፈት ቤት ወይም በክፍለ ከተማው ደረጃ የሚቋቋም የአስፈጻሚ አካል ኃላፊ፣ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፤

ሐ) የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤቶች ከሚያስተባብሯቸው አስፈጻሚ አካላት ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ የከተማው ካቢኔ በሚያጸድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ከንቲባው በሚያወጣው መመርያ ይወሰናል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እና በሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች የሥራ ሁኔታ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ የተደራጁ የክፍለ ከተማ አስፈጻሚ ተቋማት የራሳቸውን በጀት ጥያቄ አዘጋጅተው ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባሉ፤ ሲፈቀድላቸው በህግ አግባብ ሥራ ላይ ያውላሉ፤ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ ወረዳ

## ምዕራፍ አንድ

## ስለወረዳ ተጠሪነት፣ አስፈጻሚ አካላት

82. **የወረዳ ተጠሪነት**

የወረዳው አስተዳደር ተጠሪነት ለወረዳው ነዋሪና ለክፍለ ከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡

83. **አደረጃጀት**

የከተማውን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕጎች በወረዳው የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት፡-

1. የወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤
2.. ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ
3.. የወረዳ ካቢኔ፤
4. የወረዳ ሥራ አስኪያጅ፤
5. ሌሎች አስፈጻሚ አካላት፤

ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ዋና ሥራ ሥራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ካቢኔ፣ ሥራ አስኪያጅ

84. **የወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚ**

1. የወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከወረዳ ምክር ቤት አባላት ውስጥ ይመረጣል፤ የሥራ ዘመኑም የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፤
2. የወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤትና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ወረዳውን ይመራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የወረዳ ካቢኔ አባላትን ከምክር ቤት አባላት ወይም የምክር ቤት አባላት ካልሆኑት መካከል መርጦ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ሹመታቸውን ያፀድቃል፤
   ለ) የወረዳው ዓመታዊ ዕቅድና የበጀት ድልድል ሃሳብ በወረዳው ካቢኔ ከተመከረበት በኋላ ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፣ የወረዳውን የገቢ ማሰባሰብ በበላይነት ይመራል፤
   ሐ) የወረዳውን ካቢኔ ይሰበስባል፤

መ) በወረዳው ሕግና ሥርዓትን ያስከብራል፤ የወረዳውን የፀጥታ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ከወረዳው አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ ችግር ሲያጋጥም ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያሳውቃል፤

ሠ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት በወረዳው ካቢኔ እንዲገመገም ያደርጋል፤ ውጤቱን ለወረዳው ምክር ቤት እና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያደርጋል፤

ረ) በብሔራዊና በሕዝብ በዓላት ሥነ-ሥርዓቶች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ወረዳውን ይወክላል፤

ሰ) ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለክፍለ ከተማው ሥራ አስፈጻሚና ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፤

ሸ) በወረዳው ምክር ቤትና በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 85. <u>የወረዳ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ</u>

ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የወረዳው ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፡-

1. የወረዳ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከወረዳ ምክር ቤት አባላት ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጪ ሊመረጥ ይችላል፤
2. የወረዳ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፡፡
3. ከወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
4. የወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በማይኖርበት ወቅት ተክቶት ይሰራል፡፡

## 86. <u>የወረዳ ካቢኔ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የወረዳ ካቢኔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
   ሀ) በወረዳው ዕቅድና የበጀት ድልድል ሃሳብ ላይ ይመክራል፤
   ለ) በወረዳው ውስጥ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የከተማው የበላይ አካላት ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
   ሐ) በወረዳው ምክር ቤትና በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚሰጡት ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
2. የወረዳው ካቢኔ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

## 87. <u>የወረዳ ካቢኔ አባላት</u>

1. የወረዳ ካቢኔ ተጠሪነት ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና በጋራ ለሚወስነው ውሣኔ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ የወረዳ ካቢኔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣
   ሀ) የወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤

ለ) የክፍለ ከተማ ካቢኔ አባላት የሆኑ አስፈጻሚ አካላት በወረዳ ደረጃ ከተደራጁ ኃላፊዎቻቸው፤

ሐ) ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደአስፈላጊነቱ በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የወረዳው ሌሎች ኃላፊዎች፤

2. የወረዳ ካቢኔ አባል በካቢኔው ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ኃላፊ በተተኪ አባልነት በወረዳው ካቢኔ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

88. <u>የወረዳ ካቢኔ የስብሰባ ስነ ሥርዓት</u>

የወረዳው ካቢኔ የስብሰባ ሥነ-ሥረዓት የወረዳው ካቢኔ በሚያወጣው ውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡

89. <u>የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅና ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የወረዳው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈጻሚ በመሆን ይሠራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳው ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በወረዳው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ስሉጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ እንዲሆን ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የወረዳው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሠራተኞችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፤

ሐ) ከወረዳው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሰጪ አካላት ኃላፊዎች የተውጣጣና በከተማ ሥራ አስኪያጅ በሚወሰነው መሠረት የሚሠራ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፤ ይመራል፤

መ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ሕጐችና ውሣኔዎችን በወረዳው ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይከታተላል፣

ሠ) ስለሥራው አፈጻጸም ለክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅና ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወቅታዊና ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

ረ) ከክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅና ከወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

90. <u>የወረዳ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር</u>

ወረዳው ከክፍለ ከተማው አግባብ ያለው አስፈጻሚ አካል ሥልጣንና ተግባር አኳያ በተዋረድ በተደራጀ ወይም በሚደራጅ አስፈጻሚ አካል የሥራ መስክ ተከፋፍሎ የሚከናወኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የወረዳውን በጀትና ዕቅድ በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው አስተዳደር ያቀርባል፤

2. የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ግብር ይሰበስባል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ክፍያዎች ይሰበስባል፤
3. የወሳኝ ኩነትና የነዋሪዎች ምዝገባ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶች ይሰጣል፤
4. ነዋሪዎች በህብረት ሥራ ማህበር እንዲደራጁ ያበረታታል፤ ያደራጃል፤
5. ወረዳዎች የልማትና የአገልግሎት መስጫ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
6. የህብረተሰቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ በማጠናከር በልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን ያስተባብራል፤
7. የወረዳውን የመንግሥት ሠራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ያሰናብታል፤
8. በወረዳ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
9. የአካባቢው የልማት ሥራዎች የከተማውን ፕላን፤ የግንባታ ሕጐችንና ደረጃዎችን ጠብቀው መሠራታቸውን እንዲሁም ሕገ ወጥ ግንባታዎችን ይቆጣጠራል፤
10. ሕገ ወጥ ድርጊቶች እንዳይካሄዱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ፀጥታ ሥራዎችን ይከታተላል፤ ነዋሪውን በኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲሳተፉ ያደርጋል፤
11. ነዋሪው የአካባቢውን ጽዳት እንዲጠብቅና እንዲያስውብ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
12. የነዋሪዎችን ተሳትፎ ለማጐልበት የተለያዩ ብዙሃን ማኀበራትና ማኀበራዊ ተቋማት እንዲደራጁ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤
13. የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሠጣል፤ በሥራ ዕድል ፈጠራና በዕደጥበብ ሥራ ላይ የተሰማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በማኀበር እንዲደራጁ ያበረታታል፤ ያደራጃል፤
14. የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩበትን የሥራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የሙያዊ ድጋፍና ክትትል፣ የብድር፣ የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎትና የገበያ ትስስር ያመቻቻል፣ የመስሪያና መሸጫ ቦታ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
15. የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ፣ እድሳት እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ የንግድ እንቅስቃሴውን ይቆጣጠራል፤
16. የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲያድግ፣ የህብረተሰቡ ማህበራዊ ችግሮች እንዲፈቱ ህብረተሰቡን በማስተባበር ይሰራል፤
17. አፀደ ሕፃናትንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ መሠረተ-ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
18. የመሬት ልማትና አስተዳደርን በሚመለከት፡-

ሀ) ለመብት ፈጠራ ሥራ የባለይዞታዎች ማህደራትን ያደረጃል፣ ለክፍለ ከተማ ይልካል፤

ለ) የሕንፃ ግብር እና የቦታ ኪራይ ማስከፈያ ሰነድ በማዘጋጀት የቤት ግብር ተመን አስልቶ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤

ሐ) የጂ.አይ.ኤስ እና ሲ.አይ.ኤስ የተጠየቁ የመረጃ እርማት አጣርቶ ለክፍለ ከተማው ምላሽ ይሰጣል፤

መ)የከተማ ማደስ ሥራዎች በሚሰሩበት ወቅት የወረዳው አስፈጻሚ አካላት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል፤

ሠ) ክፍት የመንግስት ቦታዎችን ይለያል፣ በመሬት ባንክ እንዲመዘገብ ያደርጋል፣ በመሬት ባንክ የተመዘገቡ ቦታዎችን እንዲጠበቁ ለደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት መረጃ ያስረክባል፣ ክትትል ያደርጋል በህገወጦች ተወሮ ሲገኝ እንዲለቀቅ ያስደርጋል፣

ረ) የሊዝ አፈጻጸም ክትትል ያደርጋል፣ በሊዝ ውላቸው መሰረት ያላለሙትን ይለያል ያስተላልፋል፤

19. ተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎችን፣ አነስተኛ ፓርኮችንና መዝናኛ ሥፍራዎችን ይጠብቃል፤ ይቆጣጠራል፤

20. የወረዳውን የተደራጀ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃ ይይዛል፤ ለሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ያቀርባል፡፡

91. <u>ስለወረዳ አስፈጻሚ አካላት</u>

1. እያንዳንዱ ወረዳ በከተማው ካቢኔ በጸደቀ ወይም በሚፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ሥልጣንና ተግባራቸው የሚወሰንላቸው አስፈጻሚ አካላት ይኖሩታል፤

2. ወረዳዎች በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችላቸው ሌሎች የሥራ ክፍሎችና እንደአስፈላጊነቱም ነዋሪውን የሚያሳትፉ የበጐ ፈቃደኞች ኮሚቴዎች፣ እና የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ማዕከላት በከተማው ካቢኔ በጸደቀ ወይም በሚጸድቅ መዋቅራዊ አደረጃጀትና የሥራ ድርሻ ዝርዝር መሠረት ለማደራጀት ይችላሉ፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደራጅ እያንዳንዱ ጽሕፈት ቤት በአጠቃላይ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ ይሆናል፤

6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ቢኖርም የወረዳ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለክፍለ ከተማው የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት ይሆናል፤

7. የዕቅድና በጀት ዝግጅት የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ የሠራተኞች የውስጥ ዝውውርና የደረጃ ዕድገትን ጨምሮ ሌሎች ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ደግሞ በሥራው መስክ ለሚመለከተው የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ቢሮዎችና የሚያስተባብሯቸው ሌሎች አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ተከትሎ

በሥሩ የሚደራጁትን ሌሎች ጽሕፈት ቤቶች ወይም ሌሎች የሥራ ክፍሎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

8. የወረዳ ጽሕፈት ቤቶች ከሚያስተባብሯቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር እና ጽሕፈት ቤቶቹ በአንድ ላይ ደጋፊ የሥራ ሂደቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ የከተማው ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በከንቲባው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤
9. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) እና በሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎችና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች እንዲሁም የአስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች የሥራ ሁኔታ በካቢኔው በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

92. <u>ስለ ቦርድ፣ አማካሪ ምክር ቤት፣ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ምክክር መድረክ</u>

1. ካቢኔው ለአስፈፃሚ አካላት እና ለሌሎች የከተማው ተቋማት የሥራ አመራር ቦርድ፣ አማካሪ ምክር ቤት፣ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም የምክክር መድረክ በደንብ ሊያቋቁምላቸው ይችላል፤
2. የከተማ አስተዳደሩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፣ የልማት ድርጅቶች ቦርድ እና በሥራ ላይ ያሉ የከተማው አስተዳደር ቦርዶች በተመለከተ አግባብነት ያላቸው ህጎች ድንጋጌ የተጠበቀ ነው፡፡

93. <u>አስፈፃሚ አካል፣ የልማት ድርጅት ስለ ማደራጀትና ማቋቋም</u>

1. ለከተማው ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑት እና በከተማው ምክር ቤት በሚሾሙ ኃላፊዎች የሚመሩ አስፈፃሚ አካላት ሳይጨምር ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት አዲስ አስፈፃሚ አካል እንዲሁም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የልማት ድርጅት የማቋቋምና የማደራጀት ሥልጣን ተሰጥቶታል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተቋቋመ አስፈጻሚ አካል በዚህ አዋጁ አንቀጽ 16 የተደነገገውን የወል ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

94. <u>የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀትና አሰራር ስለመወሰን</u>

ካቢኔው አስፈላጊነቱን ሲያምንበት የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 95. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ካቢኔው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 96. ስለ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤት

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለከተማ ምክር ቤት ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅ የተደነገገው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

### 97. ከፍርድ ቤት ውጭ የመዳኘት ስልጣን የተሰጣቸው አካላትን ስለማደራጀት

ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ በቻርተሩ አንቀጽ 40 የተጠቀሱትን አስተዳደራዊ የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላትን አደረጃጀትና አሰራር የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

### 98. የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 የተላለፉ መብትና ግዴታዎች እንደአግባቡ በዚህ አዋጅም የሚቀጥሉ ይሆናል፤
2. የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ መብትና ግዴታ እንደአግባብነቱ ለኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፣ ለሥራና ክህሎት ቢሮ ወይም የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ተላልፏል፤
3. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ መብትና ግዴታ ለሥራን ክህሎት ቢሮ ተላልፏል፤
4. የፕላንና ልማት ኮሚሽን መብትና ግዴታ ለፕላን ልማት ቢሮ ተላልፏል፤
5. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ መብትና ግዴታ ለመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ተላልፏል፤
6. የምግብና መድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን መብትና ግዴታ ለምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ተላልፏል፤
7. የህብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ መብትና ግዴታ ለህብረት ሥራ ኮሚሽን ተላልፏል፡፡

99. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ ያልተካተቱ አስፈጻሚ አካላት ከዚህ አዋጅ ጋር ባልተቃረነ መልኩ በተቋቋሙበት ህግ ሥራቸውን ይቀጥላሉ፤
2. በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤
3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 101 ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ መሰረት የአደረጃጀት ማሻሻያ እሰከሚደረግ ድረስ በከተማ፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ተደራጅተው በመሥራት ላይ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በተደራጁበት ህግና አግባብ ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

100. <u>ስለተጠያቂነት</u>

በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ኃላፊነቱን ያልተወጣ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ አግባብነት ባለው ህግና አሰራር ተጠያቂ ይሆናል፡፡

101. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሠን የወጣ አዋጅ ቁጥር 74/2014 ከነማሻሻያው፡፡

102. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የከተማው አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

103. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ ህዳር 15 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 15 ቀን 2016 ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**